አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነጹሁፍ እና ፎክሎር ክፍል


ትምህርት የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# በሲዳማ ክልል ከ2013 እስከ 2014 ዓ/ም የተዘጋጁ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ፍተሻ


በ

እናኑ ተስፋዬ


ጳጉሜ 2015

አዲስ አበባ

# በሲዳማ ክልል ከ2013 እስከ 2014 ዓ/ም የተዘጋጁ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ፍተሻ

**አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ**

**የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ ስነጹሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት**

**የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር**

**ለተግባራዊ ሥነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት**

**በ**

**እናኑ ተስፋዬ**

**ጳጉሜ 2015**

**አዲስ አበባ**

## መታሰቢያነቱ

በታሪክ ለማይረሳው ትውልድ ሁሌ ሊዘክረው የሚገባው ሀገርንከጠላት (ከወራሪዎች) ለመጠበቅ በተሰለፉበት ለተጨፈጨፉት ለመከላከያ ሰራዊት በየቦታው ለተገደሉት እና ከቀያቸው ተፈናቅለው ለተንከራተቱት ኢትዮጵያውያን ይሁንልኝ፡፡

# አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ
# የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

በሲዳማ ክልል ከ2013 እስከ 2014 ዓ/ም የተዘጋጁ የስምንተኛ ክፍል

የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ፍተሻ

**የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ**

| | | |
|---|---|---|
| _________________ | _________________ | _________________ |
| አማካሪ | ፊርማ | ቀን |
| _________________ | _________________ | _________________ |
| ፈታኝ | ፊርማ | ቀን |
| _________________ | _________________ | _________________ |
| ፈታኝ | ፊርማ | ቀን |

# ምስጋና

በቅድሚያ ሁላችንንም ፈጥሮ የሚያኖረን ትምህርቱንና ጥናቴን ስሠራ ጤናና ዕድሜ ሰጥቶኝ ምንም ችግር ሳይኖር ለዚህ ያደረሰኝ እግዘብሄር የተመሰገነ ይሁን፡፡

በመቀጠል የድህረ ምረቃዐ ትምህርቴን ጀምሬ እስካጠናቅቅ ድረስ ያስተማሩኝን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል መምህራኖቼን ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ እንዲሁም ይህንን የትምህርት እድል እንዳገኝ ሁኔታዎችን ላመቻቹልኝ ለሲዳማ ክልል ትምህርት ቢሮና ለጥናቱ የሚያስፈልግ የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲን አመሰግናለው፡፡

በተለይ ከሁሉም አብልጬ የላቀ ምስጋናዬን የማቀርበው መምህሬ እና አማካሪዬ ለሆኑት ለ ዶክተር ጌታቸው እንዳላማው በመልካም ባህሪያቸው እና በዳበረ ሙያዊ ምክራቸው ያለመሰልቸት ስህተቶቼን እያረሙ ፣ እያበረታቱ እና ተስፋ እየሰጡ ለዚህ ውጤት በማብቃታቸው ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡

የእኔን መማር የራሱ በማድረግ ለእኔ ነጻነት በመስጠት የአብራካችንን ፍሬዎች በመንከባከብ እንደ ወንድም፣ እናትና አባት በመሆንየረዳኝንውድ ባለቤቴን እንግዳ ሼና እና ሳይማሩ ያስተማሩኝን እናትና አባቴን ውድ ወንድሜን ዶ/ር ጸጋዬ ተስፋዬን አመሰግናለሁ፡፡ በመቀጠልም እኔ ስማር እና ይህን ጥናት ስሰራ የእናትነትን ፍቅር በወጉ ሳያገኙ እነርሱም ሳያስቸግሩኝ በትዕግስት ላስጨረሱኝ ውድ ልጆቼ እዩኤል እና ናሆም እንግዳን አመሰግናለሁ፡፡ እንዲሁም ጥናታዊ ጽሁፌን ከፕሮፖዛል ጀምሮ እስክጠናቀቅ በመተየብ የተባበረችኝን መዓዛ አዴማ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

በመጨረሻም ለዚህ ጥናት ግብዓት የሚሆኑትን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በመስጠት ለተባበራችሁኝ ለደቡብ ክልል ትምህርት ጽ/ቤት፣ለሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቤቶች ጽህፈት ቤት የስራ ሀላፊዎች እና ባልደረቦቼበሙሉ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

## ማውጫ

ማውጫ ቁጥር

ምስጋና ..... i

ምዕራፍአንድ ..... 1

1.መግቢያ ..... 1

1.1.የጥናቱ ዳራ ..... 1

1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ..... 2

1.4.የጥናቱ አስፈላጊነት ..... 3

1.5.የጥናቱ ወሰን ..... 3

ምዕራፍ ሁለት ..... 4

ክለሳ ድርሳናት እና ተዛማጅ ጥናቶች ..... 4

2.1.ጽንሰ ሀሳብ ..... 4

2.1.1.የቋንቋ ፈተና ምንነት ..... 4

2.1.2.የቋንቋፈተናዓላማ ..... 4

2.1.3.የቋንቋ ፈተና ባህሪያት ..... 5

2.1.4.የቋንቋ ፈተና አስፈላጊነት ..... 5

2.1.5.የቋንቋ ፈተና አይነቶች ..... 6

2.1.5.1.የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና ..... 7

2.1.5.2 የደረጃ መለኪያ ፈተና ..... 7

2.1.6.የጥሩ ፈተና ባህሪያት ..... 11

2.1.6.1 ተገቢነት ..... 12

2.1.6.2.የተገቢነት ዓይነቶች ..... 12

2.1.6.3.የይዘት ተገቢነት ..... 13

2.1.6.4.በችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ውስጥ የይዘታዊ ተገቢነት አስፈላጊነት ..... 13

2.1.6.5.የፈተና ልየታ ሰንጠረዥ የይዘት ተገቢነትን ለመጠበቅ ያለው ጠቀሜታ ..... 14

2.1.6.6.የችሎታ መለኪያ ፈተና ይዘት አመራረጥ ...... 14

2.1.7.የቋንቋ ፈተና እና የቋንቋ መማርያ መፅሐፍ...... 15

2.1.8የቋንቋ ፈተና የይዘት ተገቢነት ደረጃን መጠበቂያ መንገዶች...... 16

2.1.9.የቋንቋ ፈተና የይዘት ተገቢነት መገምገምያ ስልቶች...... 16

2.2.የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ...... 17

ምዕራፍ ሶስት ...... 19

3.የጥናቱ ንድፍ እና ዘዴ...... 19

3.1.የጥናቱ ንድፍ ...... 19

3.2. የጥናቱ የመረጃ ምንጮች ...... 19

3.3. የናሙናአመራረጥ...... 19

3.3.1 የፈተናዎችናሙናአመራረጥ ...... 19

3.3.2 የክልል ናሙና አመራረጥ ...... 19

3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ...... 20

3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ...... 20

ምዕራፍ አራት...... 21

4.የመረጃ ትንተና...... 21

4.1.የመረጃ ምንጮች አጭር ቅኝት...... 21

4.1.1.የመርሀ ትምህርቶች እና የመማሪያ መጽሀፍት ቅኝት...... 21

4.1.2.ለ7ኛና 8ኛክፍል አማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀ የመርሀ ትምህርት ይዘቶች...... 21

2.1.3.የፈተናዎችቅኝት ...... 22

4.2. በ2013 እና በ2014 ዓ.ም ሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ የ8ኛ ክፍል ፈተናዎች ከመርሀ ትምህርት ጋር ያላቸው ግንኙነት...... 23

4.2.1.(መናገር እና ማዳመጥ) ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ እና በክልላዊ ፈተናዎች መካካል ያለው ግንኙነት (ዝምድና)...... 24

4.2.2.በማንበብ ክሂል ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ እና በክልላዊ ፈተናዎች መካካል ያለው ግንኙነት (ዝምድና)...... 25

4.2.3.በመፃፍ ክሂል ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ እና በክልላዊ ፈተናዎች መካካል ያለው ግንኙነት (ዝምድና) ........ 27

4.2.4.በሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ እና በክልላዊ ፈተናዎች መካካል ያለው ግንኙነት(ዝምድና) ........ 29

4.2.5.በአፍልቆት፣ መተርጎም እና ቃላትን የማጥናት ፈተና ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ እና በክልላዊ ፈተናዎች መካካል ያለው ግንኙነት(ዝምድና) ........ 30

4.2.6.የዘውግ እና ሥነጽሁፍ አላባውያን ፈተና ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ እና በክልላዊ ፈተናዎች መካካል ያለው ግንኙነት(ዝምድና) ........ 31

4.3.በሁለቱም ፈተናዎች የቀረቡ የፈተና ጥያቄዎች ከፈተና መርሆች አንጻር ያላቸው ጠንካራና ደካማ ጎን ........ 34

4.3.1.ደካማጎኖች ........ 34

4.3.2.በፈተናዎቹ ውስጥ የተገኙ ጠንካራ ጎኖች ........ 39

ምዕራፍ አምስት ........ 40

ማጠቃለያ እና አሰተያየት ........ 40

5.1.ማጠቃለያ ........ 40

5.2.አስተያየት ........ 42

ዋቢጽሁፎች ........ 44

አባሪ 1 ........ 47

አባሪ 2 ........ 62

አባሪ 3 ........ 69

ማረጋገጫ ........ 80

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሲዳማ ክልል ከ2013 እስከ 2014 ዓ/ም የተዘጋጁ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ፍተሻ ላይ ነው፡፡ የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ሰነድ ፍተሻ በመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ የጥናቱ ናሙናዎች ወይም የክልልና የፈተናዎች አመራረጥ የተመረጡት በአመቺ ንሙና ዘዴ ሲሆን የተመረጡት የመረጃ ምንጮች በ2013 ዓ/ም እና 2014 ዓ/ም ለ8ኛ ክፍል የተሰጡ ክልል አቀፍ ፈተናዎች በዐብይ የመረጃ ምንጭነት ሲያገለግሉ በአጋዥነት ደግሞ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል መርሀ ትምህርቶች ናቸው፡፡ ከዚህ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡት መረጃዎች አይነታዊን በዋናነት መጠናዊን በአጋዥነት በመጠቀም ትንተናው ተከናውኗል፡፡ የመርሀ ትምህርቶችን ተዛምዶ ለመፈተሽ መረጃዎችን በቁጥርና በመቶኛ በማስላት በገለፃ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ የፈተናዎች የይዘት ተገቢነት በተመለከተ በገላጭ አይነታዊ አተናተን ስልት በመጠቀም በፈተናው ውስጥ የቀረቡትን 120 ጥያቄዎች በመፈተሽ የሚታይባቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን በማውጣት ትንተናው ተካሂዷል፡፡ በትንተናውም የተገኙት ውጤቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡ ፈተናዎችሁ ከመርሀ ትምህርቶች ጋር ያላቸውን ዝምድና በሚመለከት በሁለቱም ዓመተ ምህረቶች የቀረቡትን የፈተና ጥያቄዎች መርሃ ትምህርትን ሽፋን ከማዳረስ አንፃር ተመጣጣኝ አይሁን እንጂ በሁሉም ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች መርሀ ትምህርቱን ለማዳረስ ጥረት ተደርጓል፡፡ የመናገርና የማዳመጥ ክሂል ፈተና ከመርሃ ትምህርቱ አንፃር ተደራሽነቱ ውስን ነው በመሆኑም የመርሀ ትምህርትን ሽፋን ከመጠበቅ አንፃር የጥያቄዎቹ ፍትሀዊነት ወይም ተደራሽነት ጉድለት ተስተውለዋል፡፡ እነኚህ ችግሮች ወደፊት መስተካከል ቢቻል የተሸለ እንደሚሆን በአስተያየት ላይ ተጠቁሟል፡፡

# ምዕራፍአንድ

# መግቢያ

## 1.1.የጥናቱ ዳራ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎች የተማሪዎችን የማዳመጥ፤የመናገር፣የማንበብናየመጻፍ ክሂሎች ማጎልበትና የሥነ ጽሁፍና የሥነ ልሣን ዕውቀት ማዳበር ናቸው፡፡ የእነዚህን ዓላማዎች መሳካትና አለመሳካት ለማወቅ የተዘጋጁ ፈተናዎችን ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ወይም ተዛምዶ መታየት/መፈተሽ/አለባቸው፡፡

ይህን በተመለከተ Dubin&Olishtain (1986) እንደገለጹት መርሀ ትምህርት በውስጡ የትምህርቱን ዓይነት አስመልክቶ የሚቀርቡትን ዓላማዎች፣ይዘቶችን፣መርጃ መሣሪየዎችና የመገምገሚያ ሥልቶችን ሥርዓት ባለው መንገድ ተቀናጅቶ የሚቀርብና ለመማር ማስተማሩ የተዘጋጀ የትምህርት ዕቅድ ነው፡፡ ከዚህ አገላለጽ በመነሳት ፈተና አንድ ሰው ምን እንደሚያውቅ ወይም አንድ ነገር እንዴት እንደሚፈጸም የሚረዱበት ዘዴ መሆኑን እና ከመማር ማስተማሩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተማሪዎችን ለመገምገምና ለመመዘን ወሳኝ የሆነ ክንውን መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

የቋንቋ ትምህርት መርሀ ትምህርት፣በሚቀርበው ትምህርት ውስጥ የማስተማሪያ መሣሪያ ዝግጅትን እና የቋንቋ መማር ማስተማርን ማጎልበት አለበት፡፡ ከዚህም አንጻር የዕለተ ተዕለት ህይወትንና ልምድን የሚያሳዩት የተለያዩ ጽሁፎችን ያካተተ የተማሪዎቹን ታሪካዊ ዳራ የቃኘ የመማር ማስተማሪያ ሰነድ/መጽሀፍት/መዘጋጀትአለበት (Tomlinson 2008)፡፡

ፈተና የመማርማስተማር ሂደትን ለመገምገም የሚያስችሉ ጠቃሚ መረጃዎችን የሚሰጥ መሳሪያእንደሆነ Bachman (1990) ገልጸዋል፡፡በመሆኑም የቋንቋ ትምህርት ዓላማ የታለመለትን ግብ መምታት አለመምታቱንና ተማሪዎች በየደረጃቸው የተፈለገውን የብቃት ደረጃ ላይ መድረስ አለመድረሳቸን የሚረጋገጥበትመንገድ ፈተናነው፡፡የቋንቋ ፈተናን Alderson (2003) እንደሚከተለው ገልጸዋል የቋንቋ ፈተና ለተማሪው በየወቅቱ በትምህርቱ የሚያመጣውን ለውጥ እና በቋንቋው የሚኖረውን የአጠቃቀም ብቃት ወይም ችሎታ ለመፈተሽ የሚጠቅም ስልት ነው፡፡ በቋንቋ ፈተና የመናገር፣ የማዳመጥ፣ የማንበብ፣ የመጻፍ፣ የሥነልሳንእና የሥነጽሁፍ እውቀት በመማመር ማስተማሩ ሂደት ምን ደረጃ ላይ እንደደረሱየሚለካበት የችሎታ መለኪያ ነው፡፡

ፈተና መለካት የሚገባውን የትምህርት ይዘት በሚገባ ለመለካት ማሟላት የሚገባውን ባህሪያት አሟልቶ መገኘት አለበት፡፡አንድ ፈተና ተገቢ ነው የምንለው በመማር ማስተማሩ ሂደት

የተለማመዱትን የትምህርት ልምዶች ወይም ይዘቶች ከተማሪዎቹ እውቀት እና ክህሎት ጋር በማገናኘት የትምህርት ይዘቶቹ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የተማሩበትንመንገድ መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ሲሆን ነው፡፡በመሆኑም የቋንቋ ምሁራን መፈተንን ከመማር ማስተማር ጋር ተያያዥነት ያላቸው እና አንዱን ካንዱ ለይቶ መመልከት እንደማይቻል (Heaton 1988)ይገልጻሉ፡፡

## 1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የፈተና ጥራት እንዳይኖር ከሚያደርጉ መንስዔዎች አንዱ በፈተናዎች ላይ የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች በመርሀ ትምህርቶች ውስጥ ካሉ ይዘቶች ጋር ያላቸው ዝምድና አናሳ መሆን ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም Hughes (1989) እንደገለጹት "አንድ ፈተና ይዘታዊ ተገቢነት ከሌለው በትምህርት ሂደት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ፈተናው በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ሊኖሩ ለሚገቡ ይዘቶች አስፈላጊውን ትኩረት በመስጠት የፈተናውን መስፈርቶች በማሟላት ማዘጋጀትን ይጠይቃል፡፡" ከዚህ አንፃር የፈተናውን ሚዛናዊነት ለመጠበቅ ከተፈተኑ በኋላ በመለካትና በመገምገም የተገኘውን ውጤት ለወደፊቱ ማሻሻያ በሚያስገኝ ሁኔታ መቅረብ አለበት፡፡

አጥኚዋ ክልላዊ ፈተና ላይ በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱ የፈተና ጥያቄዎች ከመርሀ ትምህርት ጋር ያላቸው የይዘት ተገቢነት ፍተሻ በሚል ርዕስ ጥናት እንድታካሄድ ካነሳሷት ምክንያት አንዱ በሥራ ሂደት ላይ ያጋጠሚት የፈተና ጥራት መጓደል ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ክልሉ አዲስና ክልላዊ ፈተና ከጀመረ ገና ለሁለተኛ ጊዜ ብቻ በመሆኑ እና በዚህ ርዕስ ዙሪያ የተሰራ ጥናት እና መረጃ ባለመኖሩ የተዘጋጀውን ፈተና ፈትሾ ለቀጣዩ ማሻሻያ ለማድረግ በማሰብ ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሲዳማ ክልል ከ2013 እስከ 2014 ዓ/ም የተዘጋጁ የስምንተኛ ክፍል የአማረኛ ቋንቋ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ፍተሻ ነው፡፡ በዚህ መሠረታዊ ዓላማ ስር የሚከተሉት ንዑስን ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

- የቋንቋ ክሂሎችና የዕውቀት ዘረፎች በመርሀ ትምህርቶች የተሰጣቸውን ሽፍን መሰረት በማድረግ በ2013 ዓ/ም እና በ2014 ዓ/ም በተሰጡት ፈተናዎች ውስጥ ያገኙትን ውክልና በመመርመር የይዘት ተገቢነታቸውን መፈተሽ፤
- በ2013 ዓ/ም እና በ2014 ዓ/ም ለ8ኛ ክፍል የተዘጋጁ የመልቀቂያ ፈተናዎች የችሎታ መለኪያ እንዲሆናቸው መጠን የችሎታ መለኪያ ፈተና መርሆችን መከተል፤ አለመከተላቸውን መፈተሽ፤

## 1.4.የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፣

- የፈተና አዘጋጆች በቀደምት ፈተናዎች ላይ ከሚገኙ የትምህርት ይዘቶች አንጻር ከማዘጋጀት ይልቅ በመርሀ ትምህርቱ ላይ የተገለጹትን ይዘቶችያካተቱ ችሎታ መለኪያ ፈተና ማዘጋጀት አስፈላጊ እንደሆነ ጥቆማ ይሰጣል፣
- በመርሀ ትምህርቱና በፈተናው ውስጥ የሚገኘውን ተዛምዶ ችግርም ካለ ችግሩን ስለሚጠቁም ለክ ልሉሥርዓተትምህርትን እናመርሀትምህርትንለሚያዘጋጁባለሙያዎችፍንጭይሰጣልተብሎይታሰባል፡፡
- ከዚህ ጥናት ርዕስ ጋር በተመሳሳይ ወይም በተዛማጅ ጥናት ለመሰራት ለሚፈልጉየትምህርት ባለሙያዎች እንደመነሻ ሀሳብና ተዛማጅ ጽሁፍ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 1.5.የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ትኩረት አድርጎ የተነሳው ከ2013 እስከ 2014 ዓ/ም በሲዳማ ክልል ለ8ኛ ክፍል የተሰጡ ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ፈተናዎቹ ለክፍሉ ከተዘጋጀው መርሀ ትምህርት ጋር ያላቸውን የይዘት ተገቢነታቸውን ብቻ የመፈተሽ ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት
# ክለሳ ድርሳናት እና ተዛማጅ ጥናቶች

## 2.1.ጽንሰ ሀሳብ

### 2.1.1.የቋንቋ ፈተና ምንነት

የቋንቋ ፈተና ምንነትን በተመለከተ በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ የሚያስችሉ አስፈላጊ የሆኑ ጥቆማዎችን የሚሰጥ መሳሪያ መሆኑን የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸውን ሀሳብ ሠንዝረዋል፡፡ በመሆኑም የተወሰኑት ያሉትን እንደሚከተለው እናያለን፣ Baker (1989) "ተማሪዎች በሚማሩት ትምህርት ብቃታቸው የሚለካበት፣ ስንፈታቸው እና ብርታታቸው የሚፈተሽበት፣ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ብቃት የሚለካበት መንገድ አንዱ ፈተና ነው፡፡ በመሆኑም ፈተና በቋንቋ ትምህርት መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ መምህራንም ሆኑ የትምህርት ባለሙያዎች ስለተማሪዎች መማር ሂደት ፍተሻ ከሚያደርጉበት መንገድ አንዱ ፈተና ነው" በማለት ገልጸዋል፡፡

ከላይኛው ገለጻ የምንረዳው ፈተና የመማርማስተማር ሂደት እና ይዘት የመምህሩ ብቃት አና የዕቅድ ግብ መምታት የሚፈተሽበት የትምህርት መሳሪያ መሆኑን ነው፡፡

ለተማሪው በየጊዜው በቋንቋ ትምህርት የሚያደርገውን መሻሻልና ሀሳብን በማስተላለፍ በቋንቋ አጠቃቀሙ ብቃት ያለው መሆኑን ለመመዘን የሚረዳ ነው፡፡የተማሪው ቋንቋ አጠቃቀሙ ከፍ ማለቱን እና በአስተሳሰቡ ከቋንቋ ትምህርት ዓላማ አንጻር ያለበትን ደረጃም ይፈትሻል (Alderson 2003)፡፡ይህ ማለት የተማሪውን የቋንቋ ብቃት የሚፈተሽበት(የሚገመገምበት )እንደሆነ ነው፡፡

### 2.1.2.የቋንቋ ፈተና ዓላማ

የቋንቋ ፈተና አላማ እንደተፈታኙ የትምህርት ደረጃ እና ዓይነት ይለያያል፡፡ ፈተናዎች የሚዘጋጁት የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችን ለመፈተሽ ሲሆን በዓይነታቸውም ሆነ በአቀራረባቸው አንድ ዓይነት ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ ፈተና የራሱ የሆነ ይዘት እና ዓላማ አለው (Madson 1983)::

ፈተና ሲዘጋጅ ተማሪው እንዲሆንና እንዲያውቅ መርሀ ትምህርትን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀው ዓላማ ግብ መምታቱን መለያ የመማር ማስተማር ዕቅድ አካል ነው፡፡ይህንን በተመለከተ Ur. (1996) እንደ ገለጹት የቋንቋ ፈተና ተቀዳሚ ዓላማ ተማሪው እንዲማር የተፈለገውን ዓላማ ምን ያህል እንደሚያውቅ እና እንደሚተገብረው ለማወቅ ነው፡፡

ስለፈተና ይዘትና ዓይነት ያለው (2009) ሲገልጹ የፈተናዎችን ይዘትና በተለይም ዓይነት የሚወስነው ዋናው ነገር ፈተናዎቹ የተዘጋጁበት ዓላማ ነው፡፡

በአጠቃላይ የቋንቋ መሠረታዊ ዓላማም በቋንቋ አማካኝነት ተግብቦትን መፍጠር መቻል ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የቋንቋ ፈተና አላማ ለክፍሉ የተዘጋጀውን መርሀ ትምህርት መሠረት በማድረግ የተማሪዎችን የመናገር፣የመጻፍ፣የማንበብና የማዳመጥ ክሂሎችን እንዲሁም የሰዋስውና የሥነ ጽሁፍ ዕውቀት ብቃት እንደሚፈትሽ ነው፡፡

## 2.1.3.የቋንቋ ፈተና ባህሪያት

የቋንቋ ትምህርት ፈተናዎች አንድን አካል ለመለካት ሲታሰብ አፅንኦት ተሰጥቷቸው ትዕዛዛቸው፣ ይዘታቸው፣አቀራረባቸው የጥሩ ፈተና አዘገጃጀት ባህሪን ተላብሰው መዘጋጀት አለባቸው፡፡ አንድ ፈተና ጥሩ የሚሆነው የአስተማማኝነት፣ የትክክለኛነት፣ ተገቢነትና የተተገባሪነት ባህሪን አሟልቶ ሲገኙ እና የሚዘጋጁ ፈተናዎች አንድን ተፈታኝ ለመመዘን ስቀርቡ ትኩረት ተሰጥቷቸው ትዕዛዛቸው፣ ይዘታቸው፣ አቀራረባቸው የጥሩ ፈተና አዘጋጃጀት ባህሪን ተከትለው ሲቀርቡ ነው በማለት (Harrison 1983፡10-12) እና (Brown1994፡153-154) ይገልፃሉ፡፡

አንድን የትምህርት ዓይነት ፈተና ለማዘጋጀት የጥሩ ፈተና ባህሪያትን ወይም መመዘኛ መስፈርቶችን ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡

በጥሩ ፈተና ባህሪያት ላይ ምሁራን እንደሚከተለው ሀሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡ ለአብነት

Harrison (1983)፣ Bachman (1990) እና Hughes (2003)የጥሩ ፈተና ባህሪያትን ሶስት ናቸው በማለትየሚከተሉትን አስተማማኝነትን፣ ተገቢነት እና ተተግባሪነትን ዘርዝረዋል፡፡ዝርዝር መገለጫቸውን በሌላ ክፍል እናያለን፡፡

## 2.1.4.የቋንቋ ፈተና አስፈላጊነት

Bachman (1990:54) የቋንቋ ፈተና የሚከተሉት ሁለት ዋና ዋና ጠቀሜታዎች እንዳሉት በመግለፅ አስፈላጊነቱን ያስረዳሉ፡፡

ሀ. በትምህርት መርሀ- ግብር ትግበራ አውድ ውስጥ ትምህርታዊና አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ለመስጠት እንደ መረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡

ለ. በቋንቋ ፅንሰ ሀሳቦችና ትውረቶች አውድ ውስጥ ለቋንቋ ለመዳና ለቋንቋ ትምህርት ምርምር በሚያስፈልግበት ጊዜ ለችሎታ( ባህሪ )መለያ አመላካች ሆኖ ያገለግላል፡፡

በአጠቃላይ ከምሁራኑ ገለፃ መረዳት እንደሚቻለው የቋንቋ ፈተና የተማሪዎችን የቋንቋ ዕድገት ለውጥ

ለማወቅ፣ ተማሪዎች ለማበረታታት፣ በትምህርት ጊዜ የሚያጋጠሙ ችግሮች ለመለየት፣ የተማሪዎች ችሎታ ለመፈተሽ፣ ተማሪዎችን በችሎታቸውና እንደየዝንባሌያቸው ለመመደብ እንዲሁም የተማሪዎች የዕውቀት ደረጃን ለመወሰን እጅግ አስፈላጊ መሆኑ ነው፡፡

ስለዚህ የተማሪዎችን ትምህርት ለመገምገም፣የመምህራን የማስተማር ሒደት ለመፈተሽና የማስተካከያ እርምጃዎችን ወስዶ የቋንቋ ትምህርቱን ስኬታማና ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ ፈተና እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡

### 2.1.5.የቋንቋ ፈተና አይነቶች

ፈተናዎች የትምህርቱንዓላማዎች በሚመለከት መፈተን ይቻላል፡፡ነገርግን የሚፈትኑበት ዓላማ መለያየት ለፈተና ዓይነቶቹ መለያየት መንስዔ መሆኑን ምሁራን ይስማሙበታል፡፡

ለምሳሌ Harrison (1983) ፈተናዎችን በፈርጅ ፈርጃቸው ለመመደብ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን አስመልክተው ሲገልጹ ፈተና የምንፈትንበትን ዋና ዓላማማወቅ የፈተናውን አይነት እንድናውቅ ያስችለናል በማለት ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪ ያለው (2009፡19) በበኩላቸው "የፈተናዎችን ይዘት እና ዓይነት የሚወስነው ዋናው ነገር ፈተናዎቹየተዘጋጁበት ዓላማ ነው" በማለት በይነዋል፡፡

የቋንቋ ፈተና በቋንቋ መማር ማስተማር ክንውን ውስጥ የተለያዩ ጥቅሞችን ሊሰጥ ይችላል፡፡ በመሆኑም የፈተናዎቹ ይዘትና አቀራረብ የተለያየ ገጽታ ይኖረዋል፡፡ የተለያዩ ምሁራን የቋንቋ ፈተናን ከተለያዩ መስፈርት አኳያ በመገንዘብ በአይነት በአይነት ይደለድሉዋቸዋል፡፡

Caroll (1980:74) ፈተና የሚሰጥበትን ጊዜ አስመልክቶ የቅድመ ትምህርት ፈተና ወይም የቅድመ ችሎታ መለኪያ፣ብቃት መወሰኛ፣ የትምህርት ጊዜ ፈተና ወይም ለውጥን፣ ጥንካሬና ድክመት መለኪያ ወይም ሂደታዊ እንዲሁም ድህረ ትምህርት ፈተና ወይም ማጠቃለያ ፈተና፣ዕድገትን ማሳያ በማለት ይከፍሉታል፡፡ በመቀጠል Hughes (1989፡10) እና Harrison (1983፡9) ደግሞ የቋንቋ ፈተናን ከሚዘጋጅበት ዓላማ አኳያ የቅድመ ችሎታ መለኪያ፣ የደረጃ መለኪያ ፣ የጥንካሬና ድክመት መለኪያ እና የችሎታ መለኪያ ፈተና በማለት በአራት መድበዋል፡፡

ሲጠቃለል ምሁራኑ የቋንቋ ፈተናን የተለያዩ መስፈርቶችን በማስፈርበዓይነት ዓይነት በመክፈል የተለያየ የየራሳቸውን አመለካከትሰጥተዋል፡፡ ለፈተናዎች ዓይነትመለያየት በመንስዔነትየሚጠቀሰው ፈተናዎቹ የተዘጋጁበት ዓላማና ወቅት የተለያየ በመሆኑ ነው በማለት ምሁራኑ ያስረዳሉ፡፡ ብሆንም ከእያንዳንዱ መስፈርት አንጻርአንድ የሚያደርጋቸውን ባህርያትን በመለየት ለተፈለገው አላማ መገልገል እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት በዋናነት የሚጠቀሱ የፈተና አይነቶችንለመመልከትተሞክሯል፡፡

#### 2.1.5.1.የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና

የቅድመ ችሎታ ፈተና ከስሙ አንጻር እንኳን ስናይ ተማሪዎች ገና ያልተማሩት ወደፊት ግን ቢማሩት ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉ እንደሆነ ለመፈተሽ የሚዘጋጅ የፈተና ዓይነት ነው፡Heaton (1975:164) ፣Harrison (1983:4) የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና ተማሪዎች የተማሩትን የቋንቋ ትምህርት ዕውቀት የሚለካ ሳይሆን ያላቸውን የተፈጥሮ ዕውቀትለመለካትእንደሚያገለግል ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪ Brown (1994:285) የቅድመ ችሎታ ፈተና“ የአንድን ሰው አጠቃላይ ዕውቀት እና ብቃት ለማወቅ እንዲሁም የወደፊቱን ሁኔታ ለመወሰን የሚዘጋጅ ፈተና ነው” በማለት ገልጸዋል፡፡

ከዚህ ገለጻ የምንረዳው ነገር ቢኖር አንድ ትምህርት ለተፈታኞች ከመቅረቡ በፊት ተማሪዎችን እንደ ቋንቋ ችሎታቸውና ዕውቀታቸው በተለያየ ቦታ ለመመደብ የሚያስችል በመጀመሪያ በነሱ ሂሊና ውስጥ ያለውን የቀደመ ዐውቀት ልክ ለማወቅ የሚፈተኑት ፈተና ነው፡፡

#### 2.1.5.2 የደረጃ መለኪያ ፈተና

የደረጃ መለኪያ ፈተና በተፈታኞች መካከል ያለውን የውጤት ልዩነት ላይ የሚመሰረት ሳይሆን የአንድ ግለሰብ የዕውቀትና ብቃት ደረጃ የሚያሳይ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን እንደሚከተለው ገልጸዋል፡-

የደረጃ መለኪያ ፈተና ሲዘጋጅ መሰረት የሚያደርገው የቋንቋ ንድፈ ሀሳቦችን ሲሆን ለዚሁም ትኩረት የሚያደርገው በቋንቋ ይዘት ላይ ነው፡፡ ይኸውም የቀረበው ፈተና አጠቃላይ ወይም ሁለገብ የቋንቋ ችሎታ የሚጠይቁ ነጥቦችን ያካተተ ነው(Bachman 1990:71)፡፡በተጨማሪ Brown(1994:258) እንደሚገልፁት የደረጃ መለኪያ ፈተና ተማሪዎች በአንድ የተወሰነ ነገር ላይ ያላቸውን ብቃትየሚያመለክትሆኖ ዋና ጉዳዩ በተገኘው ውጤት ደረጃ መስጠት ነው፡፡

ከብያኔዎቹ አንጻር መገንዘብ የሚቻለው የደረጃ መለኪያ ፈተና እና የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና ተቀራራቢነት እንዳላቸው ነው፡፡ይህን በተመለከተምAlderson(1995፡2) ሲገልጹ የደረጃና የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ተማሪዎችንበተወሰነ ምድብ ውስጥ ለማካተት የሚያስችሉ በመሆናቸው እና ከመደበኛ የትምህርት ሂደት በፊት የሚዘጋጁ በመሆናቸው ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል ይላሉ፡፡

ከላይ የተጠቀሰው ከምሁራኑ አገላለጽ አንፃር ሁለቱም ለተለያየ ዓላማ የሚውሉ የተለያዩ የፈተና ዓይነቶች መሆናቸውን ነው የሚያስገነዝቡን ይኸውም የብቃት ደረጃ መስጫ እና ችሎታ መለኪያ ዞርዞሮ ብቃትም ተለካ ደረጃም ተሰጠ ጭብጡ የተማሪውን የእውቀት መጠን ለማወቅ ነው፡፡

#### 2.1.5.3 የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና

የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ብለን የምንፈርጀው የቋንቋ ፈተና መደበኛ ያልሆነ ፈተና ሲሆን

መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚያዘጋጁት ፈተና ነው፡፡በዚህ ፈተና የመምህራንና የተማሪዎች እንዲሁም የትምህርት መሳሪያዎች ወይም ግብአቶች ጥንካሬና ድክመት ይፈተሸል (Rivers 1968:288)፡፡

Hughes (1995:13) እንደሚገልፁት ደግሞ የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና መምህራን በተለያዩ ጊዜያት ለተማሪዎቻቸው የሚያቀርቡት ሲሆን ተማሪዎች በየትኛው የትምህርት ክፍል ላይ ተጨማሪእገዛ እንደሚያስፈልጋቸውለመለየትየሚዘጋጅ የፈተና ዓይነት ነው፡፡

የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የታዩትን ችግሮች በመለየት ውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲኖርአስተዋጽኦ የሚያደርግ ነው፡፡የዚህ ፈተና ትኩረት በተማሪዎች ላይ የሚታየውን የቋንቋ ችግር በተከታታይ መፍትሔ በመስጠት ተገቢ የሆነ የማስተማሪያ ዘዴና መሳሪያ ለመለየት ወሳኝ ነው (Bachman 1990:6፣ Harrison 1983:6፣ Brown 1994:259)::

ከብያኔዎች መገንዘብ እንደሚቻለው የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና በመማር ማስተማር ወቅት የሚፈጠሩ ችግሮችን በመለየት ለቋንቋ ትምህርቱ ድጋፍ የሚሰጥ፣ መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች በሂደት ላይ የሚገኘውን ትምህርታዊ ሂደቶችንየሚገመግሙበት እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የጥናቱ የትኩረት ነጥብ የሆነው የፈተና አይነት ዘርዘር ባለ መልኩ ለማየት ተሞክሯል፡፡

## 2.1.5.4.የችሎታ መለኪያ ፈተና

የችሎታ መለኪያ ፈተና ተማሪው የተመረውን የትምህር ዓላማ ምን ያህል እንደተረዳ እና ተግባር ላይ እንዳዋለ ለማወቅ የሚያስፈልግ መሳሪያ እንደሆነ (Bachman 1990:170) ገልጸዋል፡፡በተጨማሪ Alderson(1995:12)በመርሀ ትምህርቱ እና በመማሪያ መጽሀፉ መሠረት ተማሪዎች ቀደም ሲል የተማሩትን ትምህርት ተመርኩዞ የሚፈተኑት ፈተና እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡የችሎታ መለኪያ እና የመርሀ ትምህርት ዝምድናን በተመለከተ ተማሪዎችበትምህርት ቤት ውስጥ እውቀትና ክህሎት መማር እንዳለባቸው፣ የትምህርት እቅዱ ግብ እንዲመታ ምን ዓይነት የትምህርት ልምዶች ወይም ይዘቶች መቅረብ እንዳለባቸው እና የመማር ማስተማር ሂደቱ እንዴት እንደሚከናወን የሚያመለክት ሠነድ ነው (Ur. 1996) ::

በተጨማሪMadsen (1983) የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች የብዙ ጊዜ የክፍል ውስጥ ክንውኖች መታያ ስለሆኑ መርሀ ትምህርቱን የሚያመለክቱ መሆን አለባቸው፡፡በሌላ አባባል የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች መርሀ ትምህርቱን መሠረት በማድረግ መዘጋጀታቸው በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የሚገኙ ይዘቶች በፈተናው ውስጥ እንዲካተቱ በማድረግ የሚፈለገውን ዕውቀት ለመፈተሽ ያግዛል፡፡

### 2.1.5.4.1.የችሎታ መለኪያ ፈተና ምንነት

Heaton (1975:163) ብዙውን ግዜበዓመቱ መጨረሻ እና አጋማሽ የሚሰጡ የትምህርት ቤት ፈተናዎች እንዲሁም ማንኛውም በብሔራዊ ደረጃ ተዘጋጅተው አንድ ተማሪ የተወሰነ የትምህርት መርሀ-ግብር ማጠናቀቁን ወይም የተወሰነ ዕውቀት ማግኘቱን ለመገንዘብ የሚዘጋጁ ፈተናዎች የችሎታ መለኪያ ፈተና መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡

የችሎታ መለኪያ ፈተና አጠቃላይ ዓላማ ተማሪዎች በተማሩት ቋንቋ አማካኝነት በመቀበልና በማፍለቅ ክህሎት መጠቀም መቻላቸውን ለማረጋገጥ የሚቀርብ ነው፡፡ ይህ አይነቱ ፈተናም በክፍል ውስጥ ከሚሰጠውና በማስተማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ከተከተተው ትምህርት ይዘት በቀጥታ የሚገናኝ መሆን አለበት በማለት ይገልፃሉ (Weir 1990:5)፡፡

ይሁን እንጂ ሁለቱም የተለያዩ መሆናቸውን ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ Alderson et al (1995:12) ይህን አስመልክተው ማብራሪያ ሲሰጡ "ይህ የፈተና አይነት ከጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና ጋር በአብዛኛው ተመሳሳይነት አለው፡፡ ቢሆንም የጥንካሬ እናድክመት መለኪያ ፈተና በውስን የቋንቋ ክሂሎች እናየዕውቀት ዘርፎች ላይ ተማሪው የሚያሳየውን ለውጥ የሚፈተሽበት ነው" ብለዋል፡፡ በማከልም Harison (1983:5) "የችሎታ መለኪያ ፈተና የአጠቃላይነት ባህሪ ያለውና የመማር ማስተማርን ሂደት ተከትሎ የሚመጣ ሲሆን የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና ግን በዝርዝር እና ውሱን ሁኔታዎች ላይአጽንኦት በመስጠትየተለያዩ መልመጃዎችን ጭምር ያካተተ በትምህርት ክንውን ላይ የሚተገበር ነው በማለት ልዩነቶቹን ያስገነዝባሉ፡፡

ከላይ የተገለጹትን አባባሎች ስናጠቃልል የችሎታ መለኪያ ፈተና ተማሪዎችበውስን የጊዜ ገደብ የቀረበለትን የትምህርት ልምድ ወይም ይዘት ምን ያህል እንደተረዳየምንፈትሽበት እና በተማረው ትምህርትየተረዳውን የዕውቀትና ክህሎት ለውጥ የምንገመግምበት የፈተና አይነት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በተማሪው ላይ የሚጠበቀውን የባህርይ ለውጥ ለመመልከትእና አጠቃላይ የመማር ማስተማር ሂደቱን ለመገንዘብተጠባቂ የሆኑአካዳሚያዊ እርምጃዎችን ለመወሰድ በግብአትነትየሚያገለግልነው፡፡

- **የዚህ ጥናት ትኩረት የአንድን ትምህርት መርሀ-ግብር መጠናቀቅን ተከትሎ በሚሰጠው ክልላዊ ፈተና ላይ የይዘት ተዛማጅነት ወይም ተገቢነቱ ከመርሀ ትምህርቱ አንጻር በመሆኑ ከዚህ ቀጥሎ የሚሰጡ ሀሳቦች ይህንኑ መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡**

### 2.1.5.4.2..የችሎታ መለኪያ ፈተና እና የመርሀ ትምህርት ዝምድና

የቋንቋ መርሀ ትምህርት ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ የትኛውን እውቀት እና ክህሎት መማር እንደሚገባቸው ፤ በዕቅዱ መሠረት የትምህርት ውጤት ወይም ለውጥ ለማምጣት ምን ልምዶች ወይም ይዘቶች ሊዘጋጁ እንደሚገባ፤የመማር ማስተማር ተግባር እንዴት እንደሚከናወን እና

እንደሚገመገም የሚጠቀምመመሪያ ነው(Ur 1996)፡፡የችሎታ መለኪያ ፈተና ደግሞ ከመማር ማስተማር ጋር ጥብቅ ቁርኝት ስላለው በዝግጅት ጊዜ መሰረት የሚያደረገውበተግባር ላይ ባለ መርሀ ትምህርት እና መማሪያ መጻህፍት ላይ እንደሆነ Hughes (1989) ያስገነዝባሉ፡፡ በመሆኑም የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች መርሀ ትምህርቱን መሠረት በማድረግ  የሚዘጋጁ በመሆናቸው ቀጥተኛ ዝምድናይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡

በመሆኑም በችሎታ መለኪያ ፈተና ዝግጅት ጊዜ የሚዘጋጁ ጥያቄዎች ተማሪዎችየተማሩትን የትምህርት ልምድ ወይም ይዘት ያካተተ መሆን አለበት፡፡ Madsen(1983) እንደአብራሩ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች የብዙ ጊዜ የክፍል ውስጥ ክንውኖች መከሰቻዎች በመሆናቸው መርሀ ትምህርቱን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ በሌላ አገላለጽ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች መርሀ ትምህርቱን ተመርኩዘው መሰናዳታቸው በመርሀ ትምህርቱ የቀረቡ ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ባለቤትነትእንዲላበሱ ከማድረጉም በላይ የሚፈለገውን እውቀት ለመፈተሽ  ያግዛል፡፡

የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች  የተነሱበትን አላማ ከግብ እንዲያደርሱ በቀረበው መርሀ ትምህርት ላይ መመስረት አለባቸው፡፡ይህን ሀሳብ  Harrison (1989) እንደሚከተለው ይገልጹታል፡-

> ተማሪዎች በቀረበው ትምህርት ላይ ያላቸውን እውቀት ለማወቅ በመርሃ ትምህርቱ ላይ ሊመሰረት እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡ ይህም ማለት የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ተማሪዎች ክፍል ውስጥ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል ተገንዝበዋል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ዓላማ አድርገው ከመዘጋጀታቸው የተነሳ ተማሪዎች ለተወሰኑ ጊዜያት የተማሩትን የቋንቋ ትምህርት በሚያንጸባርቅ መንገድ መዘጋጀት አለባቸው፡፡ በመሆኑም የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች የረጅም ጊዜ የክፍል ውስጥ ተግባራት መገለጫዎች በመሆናቸው መርሃ ትምህርቱን የሚያንጸባርቁ መሆን አለባቸው፡፡

## 2.1.5.4.3.የችሎታ መለኪያ ፈተና እና የመማሪያ መጽሀፍ ዝምድና

የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ከመማር ማስተማር ጋር  ግንኙነት ስላላቸው ለዝግጅታቸው መነሻ የሚያደርጉት በሂደት ላይ የሚገኘውን ትምህርት፣ መርሀ ትምህርትንና የማስተማሪያ መጻህፍትንእንደሆነቀደም  ሲል ተገልጿል፡፡ ይህን በተመለከተ Richard and Rodgers(1996) እንደገለጹት በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚከናወነው የመማር ማስተማር ዓላማ ከቋንቋው መርሀ ትምህርት ርዕሰ ጉዳይ ጋር የሚዛመድ መሆን አለበት ይላሉ፡፡ ይህም በመርሀ ትምህርትና በመማሪያ መጻህፍት መካከል ያለውን ግንኙነትያመለክተናል ካሉ በኋላ የመማሪያ መጻህፍትም በመርሀ ትምህርቱ የተዘረዘሩትን  የትምህርት ልምዶች ወይም ይዘቶችንመነሻ ማድረጋቸው በችሎታ መለኪያ ፈተናና በመርሀ ትምህርቶች መካከል ያለውን ግንኙነትየሚያመለክተን በመሆኑ በመማሪያ መጽሀፍና በችሎታ መለኪያ ፈተና መካከልም ግንኙነት ያለ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ምሁራኑም የችሎታ መለኪያ ፈተና መርሀ ትምህርቱን እና መማሪያ መጽሀፉውስጥ የሚገኙየትምህርት ልምዶችን ወይም

ይዘቶችን መነሻ ማድረግ አለባቸውየሚለው ብያኔያቸው በችሎታ መለኪያ ፈተናና በመማሪያ መጻህፍት መካካል ያለውን ግንኙነት ያመለክተናል (Alderson 1995)፡፡

በዚህ ጥናት ሊታይ የተፈለገው ዋናው ቁምነገር የሲዳማ ክልል አዲስ እንደመሆኑ መጠን ክልላዊ ፈተና አዘጋጅቶ መፈተን ከጀመረ ገና ሁለት ጊዜ ብቻ ነው የፈተነው ፤በዚህ ጥናትም ሊፈተሸ የተፈለገው ይሄው ሁለት ጊዜ የተፈተኑትን ፈተና ጥያቄዎች የይዘት ተገቢነት መፈተሽ ዋና አላማው በመሆኑ ለችሎታ መለኪያ ተብለው የቀረቡትን ፈተናዎች ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን ተዛምዶ ሲፈትሽ ከጥሩ ፈተና ባህሪያት መካከል ለጥናቱ ተገቢ ይሆናሉ ተብሎ የታሰቡትን ርዕሰኦችበመቀጠል ይብራራሉ፡፡

## 2.1.6.የጥሩ ፈተና ባህሪያት

ፈተና የታሰበለትን ወይም የታቀደለትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሲፈለግ የጥሩ ፈተና መገለጫ ባህሪያትን ማሟላት አለበት፡፡ፈተና ያሰፈለገበት ዋና ምክንያት የመማር ማስተማሩ ሂደት ጥንካሬ እና ድክመትን፣የተማሪዎችን የዕውቀት እና የክህሎት ሽግግርን እና የመምህራን የዕውቀት እና የማስተማር ብቃትን በመፈተሽ ውሳኔ የሚሰጥበት ነው፡፡ በመማር ማስተማር ሂደት ፈተናዎች ጥሩ መመዘኛ መሆናቸውን ለመፈተሽ መስፈርት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ይህን በተመለከተ ያለው(2009፡195) እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡"የፈተና መስፈርቶች በውል ካልታወቁ አስተማማኝነትና ትክክለኛነት ያለው ፈተና አይገኝም "በማለት ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪ Bachman (1990) እንደሚከተለው ዘርዝረዋል፡፡ ተተግባሪነት፣ተገቢነት ፣አስተማማኝነት፣እ ውናዊነትእና ዋሽባክ (Wash Back) በማለት በአምስት ከፍለውታል፤ሆኖም ግን በተለያየ አገላለጽ በምሁራኑ ይገለጽ እንጂ ግላጼያቸው መሰረታዊ ለውጥ ወይም ልዩነት ያለው አይደለም፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረቡት የፈተና መመዘኛ መስፈርቶች መካከል ለጥናቱ ተስማሚ የሚሆነው ተገቢነት ነው፡፡ በተተኳሪ ፈተናዎቹ ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች ይዘት ከመርሀ ትምህርቱ አንጻር ያለውን ግንኙነት ለመፈተሽ ትኩረቱን በተገቢነት መመዘኛ መስፈርት ላይ ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም ከፈተና መመዘኛ መስፈርቶች ውስጥ አስተማማኝነት ፈተናው ለተመሳሳይ ተማሪዎች በተደጋጋሚ ተፈትነውት ይገኛል ተብሎ በሚታሰበው የውጤት ተመሳሳይነት ላይ የሚያነጣጥር ሲሆን፤ ተተግባሪነት ደግሞ ከፈተና አዘገጃጀት፣ዝግጅትና አስተዳደር ጋር የሚያያዝ በመሆኑ የዚህ ጥናት አላማ አይደሉም፡፡ በመሆኑም በተገቢነት ዙሪያ ሰፋ ያለ ትንታኔ ይቀርባል፡፡

### 2.1.6.1 ተገቢነት

ተገቢነትበሁሉም ምሁራን የጥሩ ፈተና ባህሪ መለያ ሆኖ ቀርቧል Bachman (1990፡25) "አንድን ፈተና ለመተንተን ዋናው መለኪያ ተገቢነት ነው፤በመሆኑም በፈተናው ጠቀሜታ ላይ ተመስርተው የሚሰጡ ማጠቃለያዎች ወይም ውሳኔዎች ላይ መድረሱን የሚያመለክት ነው" በማለት ያብራራሉ፡፡ Alderson (1995፡1) ተገቢነትን ሲገልጹ "አንድ ፈተና ለተዘጋጀለት ዓላማ ተገቢ ሆኖ መገኘት አለበትካሉ በኋላ ተገቢነት የሚረጋገጠው እንዲመዘን የተፈለገውን ጉዳይ ከመዘነበት አንጻር መሆን አለበት ነው፡፡"

ከላይ ስለተገቢነት በምሁራኑ የተገለጸው ፈተናን ለመተንተን ወይም ለመጠቀምየሚያስችል መስፈርት መሆኑን በመግለፅ መለካት የተፈለገውን ችሎታ በትክክል መለካት መቻሉን የሚመለከት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

ከምሁራኑ አገላለጽ ለመገንዘብ የሚቻለው ተገቢነት ያለው ፈተና ለማዘጋጀት የፈተናውን ዓላማ መወሰን አስፈላጊ ነው፡፡ አንድ ፈተና ማሟላት የሚገባውን ሁሉአሟልቶ ከተገኘ ከጥሩ የፈተና ባህሪያት አንዱ የሆነውን የተገቢነት መስፈርት አሟልቷል ማለት እንችላለን፡፡

### 2.1.6.2..የተገቢነት ዓይነቶች

Heaton (1988፡159) የተገቢነትን ዓይነቶችን በአራት ይከፍሉታል እነርሱም ገጻዊ ተገቢነት ይዘታዊ ተገቢነት፣ንድፈ-ሐሳባዊ ተገቢነት እና ቀመራዊ ተገቢነት በማለት ያስቀምጧቸዋል፡፡ በተጨማሪ Hughes (1989) ይዘታዊ ተገቢነት፣ገጻዊ ተገቢነት፣መስፈርት ተኮር ተገቢነት እናንድፈሀሳ ባዊተገቢነትበማለትበአራትይከፍሏቸዋል፡፡

እንደ ምሁራኑ አባባል የችሎታ መለኪያ ፈተናዎችን ተገቢነት ለመፈተሽ ሁለት የተገቢነት ዓይነቶችን ተመራጭ አድርገዋል፡፡ እነርሱም የይዘታዊ ተገቢነት እና ገጻዊ ተገቢነት ናቸው ካሉ በኋላ Hughes (1989) ሁሉም የተገቢነት ዓይነቶች በመማር ማስተማር ሂደቱ አስፈላጊ ቢሆኑም ይዘታዊ ተገቢነት ተመራጭ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

በዚህ ጥናት ላይ የሚቀርበው በሲዳማ ክልላዊ መንግስት ከ2013 እስከ 2014 ዓ.ም የስምንተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት እና ለዚህ ክፍል የተሰጡ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ያላቸውን የይዘት ተዛምዶ ወይም ተገቢነትን ፍተሻ ስለሆነ ወደ ትኩረት አቅጣጫ በቀጥታ ለመግባት የይዘት ተገቢነትን የሚመለከቱ ሀሳቦች ቀጥሎ የሚቀርቡ ይሆናል፡፡

### 2.1.6.3. የይዘት ተገቢነት

Alderson (1995) እንደገለጹት ይዘታዊ ተገቢነት አንድ ፈተና በአንድ የትምህርት ዓይነት ውስጥ በተካተቱ ይዘቶች አማካይነት ናሙና ሆኖ የመዘጋጀት ችሎታ ምን ያህል ነው? የሚለውን የሚገመግም ነው፡፡በተጨማሪ Heaton (1988፡160) የይዘት ተገቢነትን ሲገልጹ የአንድ የተወሰነ ትምህርት ዓላማና ይዘት በፈተናው ውስጥ ወካይ በሆኑ ናሙናዎች መቅረቡን የሚመለከት ነው፡፡ መርሀ ትምህርትን መሠረት በማድረግ የፈተናው አይነት፣ የትምህርት ዓላማና ይዘት ተያያዥነት ያላቸው በመሆኑ በክፍል ውስጥ የሚገኙትን የትምህርት ይዘቶች በናሙናነት የሚወክሉ የፈተና ጥያቄዎች ከተዘጋጁ ይዘታዊ ተገቢነታቸውንያረጋግጣሉ፡፡

የቋንቋ ፈተና የይዘት ተገቢነት የሚኖረው በፈተና የቀረቡት ጥያቄዎች በመማሪያ መጻህፍቱና በመርሃ ትምህርቱ የቀረቡትን ዝርዝር ይዘቶች ወካይ በሆነ ናሙና ማቅረብ ሲችሉ ነው ካሉ በኋላ በትምህርት ቤት ደረጃና በብሄራዊ ደረጃ የሚዘጋጁ ፈተናዎች ተማሪዎች በቀረበላቸው ትምህርት ያላቸውን የቋንቋ ክሂልና እውቀት ግንዛቤ ለመለካት የሚዘጋጁ በመሆናቸው የተማሪዎችን ትምህርት መሰረት ማድረግ እንዳለባቸው (Bachman 1990 እና Brown 1994) ያስረዳሉ፡፡

ከምሁራን አገላለጽ የምንረዳው በቋንቋ ፈተና ውስጥ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ከይዘታዊ ተገቢነት አንጻር ስንመዝን በትምህርት ይዘቱ ለቀረቡት የትምህርት ልምዶች ወይም ርዕሶች ከመርሀ ትምህርቱ አንጻር ምን ያህሉ ጥያቄ ተካቷል ወይም ቀርቧል የሚለውን ከመመዘን አንፃር ነው፡፡የክልላዊ ፈተና ይዘትም በተለይ በችሎታ መለኪያ ፈተና ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተማሯቸውን ይዘቶች እና መርሀ ትምህርቱን መሰረት ያደረጉ መሆን እንዳለባቸው ነው፡፡

### 2.1.6.4.በችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ውስጥ የይዘታዊ ተገቢነት አስፈላጊነት

Weir(1990-25) ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቶች ላይ ለሚዘጋጁ ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች አጽንኦት ይሳጣሉ፡፡የችሎታ ማረጋገጫ ፈተናዎች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ያሉ ይዘቶችን የሚያንጸባርቁና ስለተማሪዎች ብቃት ተገቢውን ውሳኔና መረጃ የሚሰጡ ናቸው::ማንኛውም ፈተና ይዘታዊ ተገቢነት ከሌለው በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡ስለዚህ ፈተናው በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ለሚገኙት ይዘቶች አስፈላጊውን አጽንኦትበመስጠትየፈተናውን መስፈርቶች ማሟላቱን ይገመግማል በማለት ገልጸዋል፡፡

ከዚህ ገለጻ የምንረዳው በችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ውስጥ የናሙና አወሳሰድ ብርቱ ጥንቃቄየሚያስፈልገው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፤ሁሉንም የትምህርት ልምዶች ወይም ይዘቶች በፈተና ላይ ማዘጋጀት ቢከብድም ወይም የማይቻል ቢሆንም ለክፍሉ ደረጃ የቀረቡት የትምህርት ይዘቶች እንደአስፈላጊነት ደረጃቸው ናሙና እንዲኖራቸው ማድረግ ተገቢ መሆኑንና ይህንን

ለማከናወንምመርሀ ትምህርቱን እና ይዘቶችን መሠረት ያደረገ የፈተና እቅድ ወይም ንድፍ (መስፈርት) መኖር እንዳለበት ያስረዱናል፡፡

### 2.1.6.5.የፈተና ልየታ ሰንጠረዥ የይዘት ተገቢነትን ለመጠበቅ ያለው ጠቀሜታ

Hughes (1989)አንድ ፈተና ይዘታዊ ተገቢነቱ እንዲጠበቅ ከተፈለገ የፈተናው ዝግጅት በፈተናው እቅድ ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት እንዳለበት ገልጸዋል፡፡በተመሳሳይ Bachman (1995) የፈተና ንድፍሲዘጋጅመጀመሪያ መሰራት ያለበትየፈተና ልየታ ሰንጠረዥመሆን አለበት፡፡ ከዚያም የፈተና ንድፍ በመጠቀም የሚቀርብ የፈተና አይነትና ቅርጽ ከመርሃ ትምህርቱ ይዘት ጋር እንዲገናኝ ያደርጋል በማለት ይገልጻሉ፡፡

ከላይኛው አባባል የምንረዳው በፈተናው መካተት ያለባቸው ይዘቶችን ሁሉ ለማካተትና ዝርዝር የመማር ማስተማር ዓላማዎችን ለመተግበር፣ ለመተንተንና ለመገምገም የፈተና ልየታ ሰንጠረዥ ማዘጋጀት አስፈላጊ እንደሆነ ነው፡፡

### 2.1.6.6. የችሎታ መለኪያ ፈተና ይዘት አመራረጥ

ቀደም ሲል እንደተገለፀው የችሎታ መለኪያ ፈተና ተማሪዎች እንዲማሩት የቀረበላቸውን ትምህር ምን ያህል እንደገባቸው ለመፈተሽ ይቻል ዘንድ በመማሪያ መፅሐፉ የተዘጋጁት የትምህርት ይዘቶችንበመመርኮዝ የሚቀርብ ፈተና ነው፡፡ Alderson et al (1995:12) እንደገለፁት የችሎታ መለኪያ ፈተና ለትምህርትነት የቀረበውን መማርያ መጽሐፍ መሰረት በማድረግየሚሰናዳ እና የመማር ማስተማሩ መርሀ-ግብር ሲጋመስ ወይም ሲጠናቀቅ ለተማሪዎች የሚቀርብ የፈተና ዓይነት ነው፡፡

የችሎታ መለኪያ ፈተና በመርሀ ትምህርቱ ንኡስን ክፍሎች ዝርዝር ላይ ማለትም በመማሪያ መፅሐፍ እና በማስተማሪያ መሳሪያዎች ላይ ተመስርቶ የሚዘጋጁ የፈተና አይነቶችመሆናቸውን (Hughes1989:10) ይገልፃሉ፡፡በመቀጠልም ተማሪዎች የተማሩትን ነገር በመፈተናቸው ጠንካራ ጎን ብኖርምየማስተማሪያ መሳሪያዎች በአግባቡ ካልተዘጋጁ እና የፈተናው ይዘት አመራረጥ ችግር የሚኖርበት ከሆነ በመመማር ማስተማሩ ሂደት ላይአሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር በመሆኑ ደካማ ጎን እንደሚኖረው ገልጸዋል፡፡

የችሎታ መለኪያ ፈተና በአንድ መደበኛ የትምህርት መርሀ ግብር ውስጥ በመርሀ-ትምህርቱ የተጠቆሙትና በመማሪያ መፅሐፍ በዝርዝር የሰፈሩትን የትምህርት ይዘቶች በትምህርት ዘመኑ አጋማሽ ላይ አልያም በአመቱማጠቃለያ የሚተገበር የፈተና አይነት ነው (Finochiaro and Brumfit 1986:186)፡፡

ከላይ ያሉት ምሁራን የገለጹበት መንገድ ቢለያይም የችሎታ መለኪያ ፈተና በመማርያ መፅሐፍ ውስጥ ከሚገኙት ምዕራፎች እና የቋንቋ መርሀትምህርት ይዘቶች የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችን በዝርዝር ለመግለጽበዕቅድ የተዘጋጁ በመሆናቸው በፈተና ናሙና አመራረጥ ላይ አጽንኦት ሊደረግባቸው እንደሚገባቸው ነው፡፡በመማርያ መፅሐፍ ውስጥየሚገኘው ይዘት ለቋንቋ ትምህርት ዓላማ ግብ መምታት እና አለመምታት መንስዔ በመሆን የራሱ አሰተዋጽኦ ሊኖረውም እንደሚችል ነው፡፡በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ወይም ተገቢነታቸውን ያሟሉ ፈተናዎችን ለማዘጋጀት የሚቻለው ሁሉም በትምህርትነት የቀረቡት ይዘቶች በትክክለኛና ወካይ ናሙና ተመርጠው በፈተናው ውስጥ መቅረብ ሲችሉ ነው፡፡ ይህን ለመተግበር የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ መጠቀም ተመራጭ መንገድ እንደሆነ ከምሁራኑ ገለጻ እንረዳለን፡፡

### 2.1.7.የቋንቋ ፈተና እና የቋንቋ መማርያ መፅሐፍ

የቋንቋ መማርያ መፅሐፍ ሥርአተ ትምህርቱን መሰረት በማድረግ በታቀደው የቋንቋ መርሐ ትምህርት ውስጥ የተቀመጡትን ዓላማዎችን እና ርዕሰ ጉዳዮችን በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማሩ ሂደት ሊከናወኑ የሚችሉ የትምህርት መሳርያዎች ናቸው፡፡

እሄን አስመልክቶ Nunan (1994፡98) የመማሪያ መፃሕፍትና የመርሀ ትምህርት ግኑኝነት አስመልክተው ሲገልፁ የቋንቋ መማርያ መፅሀፍ ያለምንም ችግር መርሀ ትምህርቱ በግልጽ የሚንጸባረቅበት እና በተግባር የሚታይበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የቋንቋ መርሀ ትምህርት ከሥርዓተ ትምህርት የሚፈልቅ ውስን የቋንቋ ትምህርት እንዴት ማስተማር እንደሚቻል የሚጠቁም፣ የትምህርቱን ዓላማ፣ ይዘት፣ አቀራረብ፣ ጊዜና ግምገማን የሚያመለክት ሰነድ ሲሆን የመማር ማስተማር ሂደትን አቅጣጫ ጠቋሚ እና ትግባራ የሚከናወነውበመማርያ መፅሀፉ ነው(Cunnings worth1995:53)፡፡

ከምሁራኑ ገለጻ የምንረዳው የቋንቋ መማርያ መጽሐፍ እና በመርሀ ትምህርቱ የተገለጹትን ክፍል ውስጥ ተግባራዊ የሚሆኑትን የትምህርት ዓላማዎች ውጤታማ ለማድረግ ሚናው ከፍተኛ ነው፡፡ በመማርያ መፅሀፍ አማካይነት የሚተገበረውን የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት በመርሀ ትምህርቱና በሥርዓተ ትምህርቱ የተዘጋጁትን የትምህርት ዓላማዎች ግብ በመምታት ለውጤት የሚያደርስአንደሆነ እና በመምህሩና በተማሪው መካከል የሚደረገው የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውን የቋንቋ መፅሀፉን መሰረት ያደረገ እንደሆነ፣ የመማርያ መፅሀፍ ደግሞ ስርዓተ ትምህርቱን እና መርሀ ትምህርቱን መሰረት ያደረገ እንደሆነ ነው፡፡ በቋንቋ መማርያ መፅሀፉ ውስጥ ያሉት የትምህርት ዓላማዎች ግብ መምታታቸውበመርሀ ትምህርቱ የተቀመጡትን ዓላማዎችን ማሳካት እንደሆነ ነው፡፡

### 2.1.8.የቋንቋ ፈተና የይዘት ተገቢነት ደረጃን መጠበቂያ መንገዶች

የቋንቋ ፈተናን ጠንካራ ጎን ለመወሰንየይዘት ተገቢነት በማዘጋጀት አና የተዘጋጀውንም በመፈተሽተገቢነትን ያሟላ መሆኑን እና አለመሆኑን በመገምገም መፈረጅ እንደሚገባ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ለአብነት Weir (1990:25) ላይ እንደገለጹትየይዘት ተገቢነትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ መመሪያዎችን እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ፡፡ እነሱም፡-

- መጠየቅ የሚገባቸው የተተኳሪው የይዘት ክፍሎች በፈተናው ጥያቄዎች ውስጥ ተመጣጣኝ ውክልና እንዲኖራቸውየሚፈተሹበት የባህሪ ክፍል ሰርዓታዊ በሆነ መንገድ መተንተን አለበት፡፡
- ፈተናው ሲዘጋጅ አጽንኦትሊሰጠው የተፈለገው ይዘት በሚገባና በተሟላ መንገድ በቅድሚያ መገለፅ አለበት፡፡
- እያንዳንዱን የባህሪ ክፍል በፈተናው ከሚኖራቸው ድርሻ አኳያየሚወከሉበትን አሰራር በመከተል ፈተናው መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

Gronlunad (1981:69) ፈተና ሲዘጋጅ የይዘት አመራረጥ ላይ አጽንኦት ስለማይሰጥ የፈተናዎች የይዘት ተገቢነት አብዛኛውን ጊዜ ጥያቄ ሲፈጥር እንመለከታለን፡፡ስለዚህ የፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ደረጃን ለማስጠበቅ ስርዓታዊ ስልተ ትግበራዎችንእና በብዛት አስፈላጊ የሆነውን የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ ማዘጋጀትይገባል፡፡ይህ የፈተና ይዘት መወሰኛ ባለሁለት ረድፍ ሰንጠረዥ ለመፈተን የሚፈለጉ የትምህርት ልምዶችንና እነዚህን የሚወክሉ ጥያቄዎችን የሚያመለክት የፈተና ዕቅድ ማመልከቻ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ የፈተናውን ግብ ምን እንደሆነ፣ለመፈተን ከተፈለጉ የቋንቋ ክሂሎች እና የዕውቀት ዘርፎች ምን ያህል ጥያቄዎች እንደሚያስፈልጉ መረጃ የሚሰጥ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

### 2.1.9.የቋንቋ ፈተና የይዘት ተገቢነት መገምገምያ ስልቶች

በፈተና መካተት የሚገባቸው የይዘት ክፍሎች ተተንትነው ከቀረቡ በኃላ የቀረበው ፈተና ያለው የይዘት ተገቢነት ደረጃ ለማወቅ የተለያዩ ዘዴዎችንመጠቀም ይቻላል፡፡ ይህን በተመለከተ Weir (1990:25) እያንዳንዳቸው ተማሪዎች የሚመልሱዋቸው የፈተና መልሶች አስቀድሞ ትኩረት ከተሰጣቸው የባህሪ ክፍሎች ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት እና ያላቸውን ዝምድና በመመልከት የፈተናውን የይዘት ተገቢነት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

በተመሳሳይ Alderson, et al (1995:193) ከዚህ ስልት ጋር ምስስሎሽ ያላቸውን የማረጋገጫ

ስልቶች እንደሚከተለው ገልፀዋል፡-በቅድሚያ ተማሪዎች የተፈተኑት ፈተና ይዘት ከተማሩትና በመርሀ ትምህርት ወይም መማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ካለው ይዘት ጋር ያለውን ቀጥተኛ ዝምድና የማነፃፀር ስልት፡፡በመቀጠል የፈተናው የይዘት ተገቢነትን በተመለከተ የጽሁፍ መጠይቆችን በማዘጋጀት መምህራን፣የዘርፉ ባለሙያዎችና የተግባራዊ ስነ- ልሳን ሊቃውንትን በማስሞላት መረጃ መሰብሰብ እና ቃለ መጠይቅ በማዘጋጀት መልሳቸውንመውሰድ የሚሉ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ተስፋዬ ሸዋየ (1981)፣Madson (1983)፣እና Brown (1996)ጥሩ ፈተናን ለማዘጋጀት የሚከተሉትን የፈተና አዘገጃጀት መርሆች መከተልና መገንዘብ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል፡፡ ማንኛውም ፈተና የሚያዘጋጅ ሰው ፈተናውን የሚያዘጋጅበትን ምክንያት ማወቅ አለበትካሉብኋላ ከዚህመርሀ የተነሳ የፈተናው ይዘት፣መጠን እና ቅርፅ በቂ መረጃ እንደሚኖር እንደሚከተለው ይጠቁማል፡፡

- ለፈተና የሚዘጋጁ ጥያቄዎች በሚፈለጉት ባህርይ እና በተሰጠው ትምህርት ላይ የተመሰረቱ መሆን አለባቸው፡፡
- የችሎታ መለኪያ ፈተና በክፍል ውስጥ ከቀረበው ትምህርት ጋር ሊዛመድ ይገባል፤ጥያቄዎቹም ሲዘጋጁ ወካይ በሆነ መልኩ ሊተገበር ይገባል፡፡
- የፈተና ጥያቄዎች ሲዘጋጁ ፈተናው የቀረበላቸውን ተማሪዎችችሎታ የሚመጥን እና በተፈታኞችም መካከል ያለውን የዕወቀት ልዩነት በግልጽ የሚያመለክት መሆን አለበት፡፡
- የሚቀርበው ፈተና የጊዜ ብዛትን ብቻ ማዕከል ያደረገ ሳይሆን የትምህርት ይዘት ትክክለኛነት እና ተዓማኒነት ለመረዳት የጥያቄዎቹ ብዛትም አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በመጨረሻም ተማሪዎች ከፈተናው ብዙ ሊረዱ የሚችሉ ነገሮች መኖር እንዳለባቸው እና መምህራንም ከተማሪው ፈተና መልስ በመነሳት ማስተካከል የሚገባቸውን የመማር ማስተማር ሂደቶችን መተግባር እና መለወጥ እንደሚችሉ ይጠቁማል፡፡

## 2.2.የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በርካታ ምሁራን በፈተና ላይ ጥናት አካሂደዋል፡፡ ይካሄድ እንጂ አብዛኛዎቹ ያጠኑት ስለ ፈተናዎች ግምገማ፣ የፈተናዎች አቀራረብ እና የመማሪያ መጽሀፍ ዝምድና፣የፈተናዎች የይዘትና አቀራረብ ንጽጽር፣ ፈተናዎች ውስጥ የሰዋስው ጥያቄዎች የይዘት እና አቀራረብ ዝምድና ግምግማ (ፍተሻ)፣ በፈተናዎች ውሰጥ የክሂሎች ጥያቄ አዘገጃጀትና አቀራረብ፣ በፈተናዎች ውስጥ የቃላት አፈታተን (አጠያየቅ) ፍተሻ እና የቋንቋ ፈተናዎች ከመርሀ ትምህርት ጋር ያላቸው የይዘት ተዛምዶ ፍተሻ (ግምገማ) ናቸው፡፡ አጥኚዎቹን ከተተኳሪ ጥናታቸው ጋር ስናቀናጃቸው ለአብነት ያህል፡- ታረቀኝ (1993) ‹‹ሀገር አቀፍ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ከ5ኛ-8ኛ ክፍል የአማርኛቋንቋ መርሀ ትምህርት ጋር ያለው ዝምድና›› የሚል ጥናት አካሂዷል፡፡ በጥናቱ ይዞት ከተነሳው ተተኳሪ ክፍል፣ ርዕስ፣ ዓላማ፣ የመረጃ ምንጭና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ አንፃር ይዛመዳሉ፡፡

ልዩነታቸው ጥናቱ የሚካሄድበት  ቦታ፣ዓ.ም እና የተማሪው ዳራነው፡፡

ራሔል (2001)‹‹ከ1995 እስከ 2000 ዓ.ም. ድረስ በቀረቡት የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መልቀቂያ ፈተናዎች የመድብለ ቃላት አፈታተን ›› በሚል ርዕስ ላይ ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ በሰሩት ጥናታዊ ጽሑፍ ላይዓላማው በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መልቀቂያ ፈተናዎች ውስጥ የሚገኙ የቃላት ፈተናዎች የቀረበበትን መንገድ መፈተሽ ነው፡፡ይህ ጥናት በፈተና ላይ የተሰራ ቢሆንም ካተኮረበት ዓላማ እና ይዘት እዲሁም የክፍል ደረጃ አንፃር ልዩነት አላቸው፡፡

በርነሽ (2003) ‹‹በ2001 ዓ.ም.እና በ2002 ዓ.ም.የ8ኛ ክፍል ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤት ከጾታ አንጻር በሰሜን ወሎ ዞን በተመረጡ አራት የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ እርከን ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት፡፡በሚል ርዕስ ለማስተርስ ድግሪ ማሟያጥናታዊ ጽሑፍ አቅርባለች፡፡ የጥናቱዓላማ በአማራ ክልል በ2002 እና በ2003 ዓ.ም. የ8ኛ ክፍል ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውጤትን ከጾታ አንጻር በማነጻጸር መተንተን ነበር፡፡ የጥናቱትኩረት የፈተና ውጤትን ከፆታ አንጻር ማነጻጸር ነው፡፡ስለዚህ የበርነሽ ጥናት በዓላማ፣ በይዘት፣ከቦታ እና ከጊዜ አንጻር ከዚህኛው ጥናት ጋር ይለያያሉ፡፡

አበበች(2004)‹‹ከ1998-2003 ዓ.ም.በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች ተዘጋጅተው የቀረቡ የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የሰዋሰው ጥያቄዎች ግምገማ›› በሚል ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ ጥናትአካሂደዋል፡፡ የጥናቱ ዋና ትኩረት1998-2003 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል በተሰጡት ክልል አቀፍ የሰዋስው ጥያቄዎችን አቀራረብ መፈተሽ ነው፡፡ከዚህ አንጻር አጥኝዋ በጥናቷ ግኝት እንደገለጸችው ለጥናቱ በናሙናነት የተወሰዱት የሰዋስው ጥያቄዎች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥያሉእንደሆነና አንዳንድ ይዘቶች በፈተናው እንዳልተካተቱ አመልክታለች፡፡የአበበች ጥናት ከዚህኛው ጥናት ጋር መርሀ ትምህርት፣ በክፍል ደረጃ እና የፈተና ግምገማ መሆኑ አንድ ሲያደርጋቸው ትኩረቱ ሰዋስው ላይ ብቻ በማነጣጠሩ አይመሳሰሉም፡፡በጥቅሉ አብዛኛዎቹቀደምት የጥናት ስራዎች የክፍል ደረጃ፣ጥናቱ የተካሄደበት ዘመን እና አካባቢ እንዲሁም በተማሪዎቹ ዳራ  ከዚህኛው ጥናት ጋር ያለያያቸዋል፡፡የተወሰኑት ግን  የፈተናውን አጠቃላይ ብቃት በጥቅል መገምገም ወይም የይዘት ተገቢነቱን  ከመርሀ ትምህርት እና ከመጽሀፉ አንጻር በመገምገም ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ፣ ይህ ጥናት ግን የፈተናዎቹን የይዘት ተገቢነት እና ዝምድና ከመርሀ ትምህርቱ ጋር በመገምገም ላይ ብቻ ተወስኖ በመካሄዱ ከሌሎቹ ይለያል፡፡በአጠቃላይ ይህ ጥናት ክልሉ አዲስ የተዋቀረ ከመሆኑ አንጻር የራሱን ክልላዊ ፈተና ከጀመረ ገና ሁለት ጊዜ ነው የፈተነው ለጥናቱ በመረጃ ምንጭነት የዋሉትም እነኚሁ ሁለቱም በመሆናቸው ከላይ የተጠቀሱት ሁሉም ጥናቶች ለጥናቱ እንደመነሻ  አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ንድፍ እና ዘዴ

### 3.1.የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው ለጥናቱ በተመረጠው በሲዳማ ክልል ለ8ኛ ክፍል በተሰጡት ክልል አቀፍ ማጠቃለያ ፈተናዎች ከመርሀ ትምህርቶች ጋር ያለው ዝምድና እና የይዘት ተገቢነት ግምገማ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን በዋናነት መጠናዊ የምርምር ዘዴን በአጋዥነት ተጠቅሟለች፡፡

በፈተናዎች ውስጥ የቀረቡትን የቋንቋ ክሂሎችንና የዕውቀት ዘርፎች ዝርዝር ይዘቶች ከፈተና አዘገጃጀት መርሆዎች አንፃር፣ ከመርሃ ትምህርቶች የተገኙ መረጃዎችን በመመርመር በቁጥርና በመቶኛ ተሰልተው በገለጸ መልክ በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

### 3.2. የጥናቱ የመረጃ ምንጮች

የዚህ ጥናት ዋናትኩረት ከ2013 እስከ 2014 ዓ.ም በሲዳማ ክልላዊ መንግስት ለ8ኛ ክፍል የተሰጡ ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ከመርሀ ትምህርት ጋር ያላቸው የይዘት ተዛምዶ መፈተሽ ወይም መገምገም ስለሆነ ከስምንተኛ ክፍል ትምህርት መሸጋገሪያ ወይም ለማጠናቀቂያ በሁለቱም ዓመተምህረት የተሰጡ ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች እና የሰባተኛ እና የስምንተኛ ክፍል መርሀ ትምህርቶች ናቸው፡፡

### 3.3. የናሙና አመራረጥ

#### 3.3.1 የፈተናዎች ናሙና አመራረጥ

የናሙና አመራረጡ ሂደት አጥኚዋ በአሁኑ ሰዓት በተመረጠው የክፍል ደረጃ እያስተማረች ያለች ለትምህርቱ እና ለፈተናው በቅርብ የምትገኝ በመሆኗ፣እንዲሁም ክልሉ አዲስ በመሆኑ ክልላዊ ፈተናም ሲሰጥ ገና ጀማሪ ወይም ሁለት ጊዜ ብቻ በመሆኑ ጥናቱም የሚካሄደው በእነኚው በሁለቱ ብቻ በመሆኑ አመቺ የንሞና ዘዴን ተጠቅማለች፡፡

#### 3.3.2 የክልል ናሙና አመራረጥ

የጥናቱ ዓላማ ቀደም ሲል እንደተገለጸው የ8ኛ ክፍል ክልል አቀፍ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ላይ በመሆኑ አጥኚዋ ተገቢ መረጃዎችን በቅርብ ለማግኘት አመቺ የሆነውን አዲሱን የሲዳማ ክልልንበአመቺ የንሞና ዘዴ መርጣለች፡፡

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

አጥኝዋ ምርምሩን በምታካሂድበት ወቅት እንደምርምሩ አይነትና ባህሪ የመረጃ መሰብሰቢያው ይለያል፡፡ ስለዚህ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማም በሲዳማ ክልል ከ2013 እስከ 2014 ዓ.ም የተዘጋጁ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ፍተሻ ነው፡፡ በመሆኑም ባለፈ የፈተና ሰነዶች ላይ ትኩረት የሚያደርግ በመሆኑ በዋናነት ለዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሰነድ ፍተሻ በመሆን አገልግሏል፡፡ በዚህ መሰረት በ2013 ዓ/ም እና በ2014 ዓ/ም በሲዳማ ክልል የተሰጡ ክልላዊ ፈተናዎች በዐብይ ሰነድነት፣ለሰባተኛ ክፍልና ለስምንተኛ ክፍል የተዘጋጁት አማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርቶች፣ መማሪያ መፅሐፍና የመምህሩ መምሪያ ደግሞ በአጋዥ ሰነድነት አገልግለዋል፡፡

## 3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ

ይህን ጥናት ለማጥናት በሥራ ላይ የዋለው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተገኙትን መረጃዎች ዓይነታዊእና መጠናዊ የመረጃ አተናተንስልትን በመጠቀም ግምገማው ተከናውኗል፡፡ ጥናቱ ፈተናዎቹ ውስጥ የተዘጋጁትን የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች አራቱ ክሂሎች እና ሁለቱ የዕውቀት ዘርፎች (መናገር፣ማዳመጥ፣መጻፍ እና ማንበብ እንዲሁም ሥነጽሁፍና ሥነልሣን) ከመርሀ ትምህርት ጋር ያላቸውን ተዛምዶ ከፈተና አዘገጃጀት ባህርይ እና መርሆዎች አንጻር ከፈተናዎቹ በሚገኙ መረጃዎች መሠረት  በመቶኛ በማስላት በፐርሰንት ተተንትነው የገላጭ ስልትን በመከተል ትንታኔ ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና

በምዕራፍ አራት አጥኚዋ የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ እንዲያስችላት ከሰነዶቹ ያገኘችውን መረጃዎች አቅርባለች፡፡ባለፉት ምዕራፎች እንደተመለከትነው የዚህ ጥናት ትኩረት እና ዓላማ በሲዳማ ክልላዊ መንግስት ከ2013 እስከ 2014ዓ.ም የስምንተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርትእና ለዚህ ክፍል የተሰጡ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ያላቸውን የይዘት ተዛምዶ ወይም ተገቢነት መፈተሽበመሆኑ በዚህ ክፍል ሁለት ነገሮች እናያለን፡፡የመጀመሪያው የፈተናውን እና የመርሀ ትምህርቱን ግንኙነት በመቀጠል የፈተናውን ተገቢነት (ጠንካራና ደካማ ጎን)፡፡

## 4.1.የመረጃ ምንጮች አጭር ቅኝት

### 4.1.1.የመርሀ ትምህርቶች እና የመማሪያ መጽሀፍት ቅኝት

ለዚህ ጥናት ከተመረጡት ሰነዶች መካከል በአማራ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ የተስማማ በ2007 ዓ.ም የተዘጋጁ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የተማሪ መጽሀፍና የመምህሩ መምሪያ ተካተውበታል፡፡ በተመረጡት ክፍሎች ላይ በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች በአስር ምዕራፎች ተደራጅተው ቀርበዋል፡፡እያንዳንዱ ምዕራፍ የራሱ የምንባብ ይዘት ሲኖረው በያንዳንዱ ምንባብ ደግሞ ሶስት ርዕሰ-ጉዳዮችና አራት አራት ምንባቦች አሉት፡፡ለመማር ማስተማሩ ሂደት የተመደቡት ተግባራት በተለያዩ ደቂቃዎች ቢመደቡም ለእያንዳንዱ ምዕራፍ ሶስት ሶስት ሳምንታት ተመድቦላቸዋል፡፡የመጽሐፎቹን ይዘት ለመሸፈን በአጠቃላይ ሰላሳ ሳምንታትተመድበዋል፡፡በነኚህ ሳምንታት ውስጥ ለክፍል ትግበራ የተሰየመው በዓመት ዘጠና ክፍለጊዜ ነው፡፡በመጽሀፎቹ ውስጥ የምንባብ ይዘቶቹና ርዕሰ ጉዳዮቹ ተማሪዎች በቋንቋው እንዲናገሩ፣ እንዲያዳምጡ፣እንዲያነቡና እነዲጽፉ እንደመነሻ ያገለግሏቸዋል፡፡ቢሆንም የዚህ ጥናት ትኩረት በመርሀ ትምህርቱእና በፈተና ላይ በመሆኑ የመርሀ ትምህርቱን ይዘቶች መነሻ ያደርጋል፡፡

### 4.1.2..ለ7ኛና 8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀ የመርሀ ትምህርት ይዘቶች

ጥናቱ ከሚያተኩርባቸው ሰነዶች አንዱ በዋናነት ለስምንተኛ ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጁ የመርሀ ትምህርት ይዘቶች በፈተና አወጣጥ ላይ ያላቸው ግንኙነት መፈተሽ ወይም መገምገም ሲሆን ከሰባተኛ ክፍል ጋር የተከታታይነት አና የተለጣጣቂነት ብቻ ሳይሆን በአብዛኛው የመመሳሰልም ግንኙነት ስላላቸው የሰባተኛ ክፍሉን በአጋዥ መረጃነት መጠቀሙ አስፈላጊ ነው፡፡በመሆኑም የመርሀ

ትምህርቱን ይዘት መመልከት ተገቢ ነው፡፡ስለዚህ ቀጥሎ በተገለጸው ሰንጠረዥ የሁለቱንም ክፍል እንመለከታለን፡፡

### 2.1.3.የፈተናዎች ቅኝት

የዚህ ጥናት መረጃ መሠረት ከሚያደርግባቸው ጉዳዮች/መሣሪያዎች/ዋነኛው እና አንደኛው በሲዳማ ክልል አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በተዘጋጀው የ2013 እና 2014 ዓ.ም የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ይዘት ላይ ነው፡፡ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና የተዘጋጀው ለእያንዳንዱ ዓ.ም 60፣60 ጥያቄዎችን ነው፡፡ስልሳዎቹም ጥያቄዎች ከመርሀ ትምህርቱ አንፃር ምንምን እንዳካተቱ ከመርሀ ትምህርቱ በመቀጠል በቅደም ተከተል በሠንጠረዥ እናያለን፡፡

### ለ7ኛና 8ኛ ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመርሀ ትምህርቱ የተዘጋጁ የቃላዊ ክሂል/መናገርና ማዳመጥ/ዝርዝር ይዘቶች

ቃላዊ ክሂሎች፣ ማዳመጥና መናገር፡-በምዕራፉ የምንባብ ይዘትና ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተመስርቶ የቀረበን ምንባብ አዳምጦ በመረዳት፣ በምንባቡ መሠረት በቃልና በጽሑፍ ተግባራት ላይ በመሳተፍ ሀሳብን አደራጅቶ በንግግር በማቅረብ ላይ ያተኩራል፡፡ በዚህ ሥር ከሚካተቱት ይዘቶች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

## 4.2. በ2013 እና በ2014 ዓ.ም ሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ የ8ኛ ክፍል ፈተናዎች ከመርሀ ትምህርት ጋር ያላቸው ግንኙነት

እያንዳንዱ ምዕራፍ የሦስት ሳምንት የትምህርት ይዘቶች እንዲይዙ ተደርጓል፡፡ በያንዳንዱ ሳምንት 40፣ 40 ደቂቃ ያላቸው ሦስት ክፍለ ጊዜያት አሉ፤ የትምህርት ይዘቶቹ ይህንኑ መሠረት አድርገው የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ለመማር ማስተማሩ ሂደት የተመደቡት ተግባራት በተለያዩ ደቂቃዎች ቢመደቡም ለእያንዳንዱ ምዕራፍ ሶስት ሶስት ሳምንታት ተመድቦላቸዋል፡፡ የመጽሐፎቹን ይዘት ለመሸፈን በአጠቃላይ ሰላሳ ሳምንታት ተመድበዋል፡፡ በነኚህ ሳምንታት ውስጥ ለክፍል ትግበራ የተሰየመው በዓመት ዘጠና ክፍለ ጊዜ ነው፡፡ ይህ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ሳምንታዊ የትምህርት አቀራረብ በመርሀ ትምህርቱ (በመምህሩ መምሪያ ላይ) የሚገኘው ክፍለጊዜ በዓመት 3600 ደቂቃዎች ወይም 60 ሰዓት ለቃላዊ ክሂል(መናገርና ማዳመጥ)፣ ለማንበብ፣ ለመጻፍ፣ ለሰዋስው፣ ለአፍልቆት/ መተርጎም/ ቃላትን ማጥናት እንዲሁም ለዘውግ (ድርሳናት) እና ሥነጽሁፍ  አላባውያን ስንት ስንት ደቂቃዎች ወይም ሰዓት እንደተሸነሸነላቸው በማየት ፈተናዎቹ ከመርሀ ትምህርት ጋር ያላቸውን ግንኙነትቀጥሎ በሚገኘው ሠንጠረዥ ጠቅለል አርገን ባጭሩ እናያለን፡፡

**በመርሀ ትምህርቶቹ እና በፈተናዎቹ መካከል ያለው ግንኙነት**

| ዝርዝር ይዘት | ዓመታዊ የክፍለጊ ዜብዛት( ድልደላ) | መቶኛ | የ2013 ፈተና ጥያቄ ብዛት | በመቶኛ | የ2014 ፈተና ጥያቄ ብዛት | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| መናገር | 5 | 5.6% | 9 | 15% | 8 | 13.3% |
| ማዳመጥ | 4 | 4.4% | 3 | 5% | 3 | 4.99% |
| ማንበብ | 33 | 36.7% | 11 | 18.3% | 10 | 16.7% |
| መጻፍ | 24 | 26.7% | 16 | 26.7% | 6 | 10% |
| ሰዋስው | 9 | 10% | 10 | 16.7% | 9 | 15% |
| አፍልቆተ/መተርጎም/ ቃላትን ማጥናት | 15 | 16.6% | 8 | 13.3% | 15 | 25% |
| የዘውግ(ድርሳናት) ሥነጽሁፍ አላባውያን | | | 3 | 5% | 9 | 15% |
| ሲጠቃለል | 90 | 100% | 60 | 100% | 60 | 100% |

አጥኚዋ በ2013 እና በ2014 ዓ.ም ሲዳማ ብሄራ ዊክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮአማርኛእንደሁለተኛቋንቋ የ8ኛ ክፍል ፈተናዎች ከመርሀ ትምህርት ጋር ያላቸው ግንኙነት በምታጠናው የፈተና ይዘቶች ውስጥ የተገኙ አራቱ የቋንቋ ክሂሎች እና ሁለቱ የዕውቀት ዘርፎች የተሰጣቸውን ውክልና ከመርሀ ትምህርቱ ዝርዝር ጋር በማስከተል እያንዳንዳቸውን ከላይ በሰንጠረዥ ተመልክተናል፡፡ሠንጠረዡ ውስጥ የተጠቀሰው ጥቅል መረጃ በመሆኑ የፈተናውን ውክልና ከመርሀ ትምህርቱ አንጻር ያላቸውን ግንኙነት ወይም ዝምድና እንደቅደም ተከተላቸው በገለጻ እንደሚከተለው እናያለን፡፡

### 4.2.1. መናገር እና ማዳመጥ ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ እና በክልላዊ ፈተናዎች መካካል ያለው ግንኙነት (ዝምድና)

በቅድሚያ ከላይ ከሠንጠረዡ እንዳየነው ለቃላዊ ክሂል በመርሀ ትምህርቱ የተሰጠው ሽፋንና በሁለቱም ዓመተምህረት ፈተና ያገኙት ውክልና በቅድሚያ ከአጠቃላይ 90 ክፍለጊዜ በጋራ 9 ክፍለጊዜ( 10%)ሲሆን በነጠላ ሲሆን መናገር በቁጥር 5( 5.6% )ክፍለጊዜ ማዳመጥ 4 (4.4%) ነው፡፡በሁለቱም ዓመተምህረት በፈተና ያገኙት ውክልና ከ60ው ጥያቄ በ2013 12(20%) ሲሆን ማዳመጥ ከ12 ጥያቄ 3(5%) መናገር 9ጥያቄ(15%)በዓመት ነው፤በመርሀ ትምህርቶቹ ውስጥ የተሰጣቸው የክፍለጊዜ ውክልና በሠንጠረዡ ላይ በመርሀ ትምህርቱ ላይ ነጣጥሎ ባለማስቀመጡ ቃላዊ ክሂል ባለው መሰረት በጋራ ተቀመጡ እንጂ በተናጥል የክፍለጊዜ መጠናቸው ንግግር 5(5.6%)ማዳመጥ 4(4.4%) ነው፡፡በመሆኑም ከክፍለ ጊዜ አንጻር የተሰጣቸው የፈተና ውክልና ተመጣጣኝ ነው ነገር ግን በተናጠል ስናይ ለማዳመጥ ኪሂል ያለው የፈተና ሽፋን ከ12 ጥያቄ 3 ብቻ መሆኑ ለማዳመጥ ክሂል ትኩረት አለመሰጠቱን ያመለክታል፡፡

የ2014 ዓመተምህረቱን ደግሞ ስናይ ቃላዊ ክሂል በመርሀ ትምህርቱ መሠረት የተሰጠው የክፍለጊዜ ሽፋን ከ2013 ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ የፈተናውን ውክልና ብቻ እንደሚከተለው እናያለን፣ለቃላዊ ክሂል ከ60 ጥያቄ በ11 ጥያቄ የተወከሉ ሲሆን በተናጠል ስናይ መናገር በ8ጥያቄ(13.3%) ማዳመጥ በ3 ጥያቄ(4.99%)ተወክለዋል፡፡ በ2014 ዓመተምህረትም ከክፍለ ጊዜ ሽፋን አንጻር በጋራ ያላቸው የፈተና ቁጥር ተመጣጣኝ ነው ሆኖም ግን በተናጠል ስናይ ለመናገር 8ጥያቄ ሲሆን ለማዳመጥ ክሂል 3 ጥያቄ ብቻ መሆኑ ሚዛናዊነት የጎደለ ይመስላል፤ለክሂሉም ትኩረት አለመደረጉን ያመለክታል፡፡

ከመርሀ ትምህርት አንጻር የእያንዳንዱን ጥያቄ አወጣጥ ብንመለከት የ2013ቱበአብዛኛው መመሪያዎችን መሰረት አድርጎ በዝግጅትና አቀራረብ ላይ ያተኮሩ ናቸው ለአብነት ከጥያቄ 6

እስከ 9 የውይይት መመሪያን የተመለከተ ሲሆን ከጥያቄ 10 እስከ 12 ደግሞ የክርክር መመሪያ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ከአጠቃላይ ከቃላዊ ክሂል 12ቱ ጥያቄዎች 3ቱ ማደመጥ፣ሁለቱ የንግግር ትግበራ፣7ቱ የክርክር እና የውይይት መመሪያ ወይም የፅንሰ ሀሳብ ጥያቄዎች በመሆናቸው የቃላዊ መርሀ ትምህርቱን ይዘት በተገቢው ሁኔታ ፈተናው አልዳሰሰውም፡፡የ2014ቱም ከ11ዱ ጥያቄዎች 3ቱ የማዳመጥ ጥያቄዎች 5ቱ ስለክርክር መመሪያ(አዘገጃጀትና አቀራረብ) የሚጠይቁ የጽንሰ ሃሳብ ጥያቄዎች ሲሆኑ ቀሪዎቹ የማስተዋል ጥያቄዎች ናቸው ስለዚህ መርሀ ትምህርቱን በተገቢ ሁኔታ አልዳሰሱም፡፡(**በተጨማሪ ሠንጠረዥ 2.የ2013 እና 2014 ዓ.ም ፈተና ውስጥ መናገርና ማዳመጥ ፈተና ዝርዝር ይዘቶችን ተመልከቱ)**

ከመርሀትምህርት በፈተናው ያልተካተቱትን ወይም ያልተነኩትን ለአብነት ያህል የሚከተሉትን እንይ፡-

ቃለ መጠይቅ ያካሂዳሉ፤ይመልሳሉ፤ምልልስ በግል አዘጋጅተው ከአገላለጽ ጋር ለክፍል ያቀርባሉ፤ አስተያየቶችን በምክንያት ይገልፃሉ፤የጊዜና የቦታ ተውሳከ ግሶችን እንዲሁም የተለመዱ አመልካቾችንና መስተፃምሮችን የሚያመለክቱ ምዕላዶችን ወይም ቃላትን ከንግግር መለየት ይጀምራሉ፤በንግግር ጊዜ ዕውቀት ለማግኘትና ለማበልጸግ እንዲሁም ግልጽ ማብራሪያ ለመስጠት አዲስ ያወቁትን የቃላት እውቀት ይጠቀማሉ፤ በቃላት መካከል ያሉትን ግንኙነቶችበሚገባ ይረዳሉ(ለምሳሌ አንድ ቃል ከቀደመው ሀረግ ጋር ያለውን ዝምድና) የደራሲውን የቃላት ምርጫ ይተነትናሉ፤በምልልስና በድራማ አዲስ የገበዩትን የቃላት ዕውቀት ይጠቀማሉ፤ ድምፅ በማሰማት ከተነበቡ ገላጭና ተራኪ ፅሁፍ ከተማሯቸውን ቃላት መካከል ያሉትን ግንኙነቶችበሚገባ ይረዳሉ፤(ለምሳሌ አንድ ቃል ከቀደመው ሀረግ ጋር ያለውን ዝምድና)፤ የደራሲውን የቃላትምርጫ ይተነትናሉ፤ በምልልስና በድራማ አዲስ የገበዩትን የቃላት ዕውቀት ይጠቀማሉ፡፡ (በተጨማሪ **ሠንጠረዥ አንድ ለ7ኛና 8ኛ ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመርሀ ትምህርቱ የተዘጋጁ ማዳመጥና መናገር ዝርዝር ይዘቶች ተመልከቱ**

### 4.2.2..በማንበብ ክሂል ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ እና በክልላዊ ፈተናዎች መካካል ያለው ግንኙነት (ዝምድና)

በሠንጠረዥ 12 በመርሀ ትምህርቶቹ እና በፈተናዎቹ መካከል ያለውን ግንኙነት ጥቅል መረጃ አይተናል፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱ ክሂል እና የእውቀት ዘርፎች ከመርሀትምህርት አንጻር ፈተናዎቹ ያላቸውን ሽፋን ማየቱ አስፈላጊ በመሆኑ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡-

የማንበብ ክሂል በመርሀ ትምህርቱ አማካይነት ለመማር ማስተማሩ በዓመት ከተመደቡት ከ90ክፍለጊዜያት 33ቱን(36.7% )ይሸፍናል፡፡ከመርሀትምህርቱ አንፃር በ2013 ዓመተምህረት በፈተናው ያገኘው ውክልና ከ60 ጥያቄ 11 ጥያቄዎችን(18.3% ) መሆኑ ከክፍለጊዜው እና ከመርሀትምህርቱ አንጻር ተጨለፈ እንጂ ክፍለጊዜውንና መርሀ ትምህርቱን አይመጥነውም፡፡የጥያቄዎቹን ይዘት ከመርሀ ትምህርት ይዘት አንፃር ስንፈትሽ ሁለት አጫጭርምንባቦች (አንቀፆች)እና ሰንጠረዥተነቦ የሚመለሱ ጥያቄዎች ቀርበዋል፤እነኚህን ምንባቦች መሠረት አድርገው የቀረቡት አስራአንዱም ጥያቄዎች ወይም የፈተናው (18.3%) ከመርሀ ትምህርቱ ይዘቶች የወከሉት አራት ዓይነቶችን ብቻ ነው፤እነርሱም ስለ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ፣ከአንቀጽውስጥ ዋና ሀሳቦችን መለየት፣ስለአያያዦችና ከሠንጠረዥ ለንፅፅር የቀረቡ ጥያቄዎች ናቸው፡፡(**በተጨማሪ ሠንጠረዥ 4 ለ8ኛ ክፍል አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ ፈተና ውስጥ የማንበብ ክሂል ፈተና ዝርዝር ይዘቶችን ይመልከቱ)**

በአንጻሩ መርሀ ትምህርቱ ላይ የሚገኙትን የማንበብመርሀ ትምህርቶችን በፈተናው ያልተካተቱትን እንደው ለአብነት የተወሰኑትን እንኳ ብናይ፡- ቃላትን ለማንበብ እስርና ነፃ ምዕላዶችን ማጣመርና መነጣጠል ይችላሉ፤ የታሰበውን ውጤት ሊያመጣ የሚችል ለቋንቋው በሚጠቀም ውስብስብ መዋቅር ያላቸውን ቃላት ያነብባሉ፤ አዳዲስ ቃላትን ለማንበብ የምዕላድ ትርጉም ዕውቀት (ቃል መስራች እና/ወይም የእርባታምዕላዶችን)ይጠቀማሉ፤ቃ ላን ለማንበብ የምዕላዶችን ውስብስብ ዐውዳዊ ፍቺ ይጠቀማሉ፤ ለክፍል ደረጃቸው የተዘጋጀውን ገላጭ ፅሁፍያነባሉ፤ለክፍል ደረጃቸው

የተዘጋጀውን የፈጠራ ፅሁፍ ያነባሉ፤ንግግር ወይም ፅሁፍና ግጥም በትክክል ማንበብን ለመ ለማመድ ያነባሉ፤ግጥምን አብራርተው ያነባሉ፤በጣም የተለመዱ አዎንታዊ፣ አሉታዊና መጠይቃዊ ምዕላዶችን ወይም ቃላትን እና በንግግር በጣም የተለመዱ ግስ መስራቾችን በጽሁፍ ውስጥ ይለያሉ፤ (መደብ፣ሙያ፣ቁጥርናፆታአመልካች ቅጥያዎችን ያስተውሏል)፤ጊዜ አመልካች ምዕላዶችን ወይም ቃላትን በፀሁፍ ውስጥ ይለያሉ፤ (የመደብ፣የሙያ፣የቁጥርና የፆታ ምዕላዶችን መለየትና መበየን ይጀምራሉ፤ጥገኛሀረጎችን በፅሁፍ ውስጥ ይለያሉ፤ ቀስበቀስ ውስብስብ ዐረፍተነገሮችን ድርብ መዋቅሮችንና መጠይቃዊ አረፍተነገሮችን በጽሁፍ ውስጥ ይለያሉ፤ አፈ ታሪክ አንብበው ምላሽ ይሰጣሉ፤ የፈሊጦችን፣ የተለዋጭና የተነፃፃሪ ዘይቤዎችን ትርጉም ተረድተው ያብራራሉ፤ከነዚህ ለአብነት እንኳ ከተጠቀሱት ከ11ዱ ጥያቄ በአንድ አንኳ ውክልና አለመኖር መርሀትምህርቱን ተጠቅመውታል ሳይሆን ነክተውታል ነው የሚያሰኘው፡፡ (**በተጨማሪ ሠንጠረዥ ሶስት ለ7ኛና 8ኛ ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት**

**በመርሀ ትምህርቱ የተዘጋጁ የማንበብ ክሂል ዝርዝር ይዘቶችን ይመልከቱ)**

ሌላው ቀርቶ ከክፍለጊዜ ስርጭት አንጻር እንኳ ብናይ ከ90ው ክፍለጊዜ 33 (36.7%)በመሸፈን አብዛኛውን ክፍለጊዜ የወሰድው (የተመደበው)ለንባብ ክሂል ነበር፡፡

የ2014 ዓመተምህረት ፈተና ከ60 ጥያቄዎች የማንበብ ክሂል የ10 (16.7% )ጥያቄዎች ሽፋን አግኝቷል፡፡ከመርሀ ትምህርቱ አንጻር የተካተቱትን ጥያቄዎች ስናይ ሰባቱ ጥያቄዎች ምንባብን መሠረት አድርገው ስለአንድ ገፀባህርይ ምንነት እና አካላዊ ገለጻ ሲሆን ቀሪዎቹ ሶስቱ ሠንጠረዥን መሰረት አድርገው የቀረቡ የንፅፅር ጥያቄዎች ናቸው፡፡ስለዚህ የ2014ቱም ፈተና ባጭሩ ከመርሀ ትምህርቱ አንጻር የማንበብ ክሂል ውክልና በጣም አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እንዲያውም መርሀትምህርትን መሠረት በማድረግ በተደለደለው ከ90 ክፍለ ጊዜ 33 (36.7%)የሸፈነው የንባብ ክሂል ነው፡፡ በጠቅላላ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከተመደበው ክፍለጊዜ ከአንድ ሶስተኛ በላይ በመሸፈን ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው የማንበብ ክሂል ነው ከዚህም አንጻር ስናይ የፈተናው ውክልና ከ60 ጥያቄ 10 (16.7%) (አንድ ስድስተኛ) ብቻ መሆኑ ዝቅተኛ ውክልና መሆኑን እንረዳለን፡፡**(በተጨማሪ ሠንጠረዥ4 (ለ8ኛ ክፍል)አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ ፈተና ውስጥ የማንበብ ክሂል ፈተና ዝርዝር ይዘቶችን ተመልከቱ)**

ያልተካተቱትን መርሀትምህርቶችን ለመረዳት ከላይ በ2013 ዓ.ም ፈተና እና መርሀ ትምህርት ላይ የተዘረዘሩትን የመርሀ ትምህርት ይዘቶች ተመልከቱ፡፡ ወይም (**ሠንጠረዥ ሶስት ለ7ኛና 8ኛ ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመርሀ ትምህርቱ የተዘጋጁ የማንበብ ክሂል ዝርዝር ይዘቶችን ተመልከቱ)**

### 4.2.3.በመፃፍ ክሂል ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ እና በክልላዊ ፈተናዎች መካካል ያለው ግንኙነት (ዝምድና)

በሠንጠረዥ አስራሁለት በመጻፍ ክሂል መርሀ ትምህርቶች እና በመጻፍ ክሂል ፈተናዎች መካከል ያለውን ዝምድና ጥቅል በሆነ መንገድ አይተናል፡፡ ነገርግን ጥቅሉ ገላጭነት ስለሌለው መተንተኑ አስፈላጊ ነው በመሆኑም የመጻፍ ክሂል በመርሀ ትምህርቱ መሠረትየተሰጠው ከ90 ክፍለ ጊዜ 24(26.7%)ሲሆን በቅድሚያ የ2013ን የፈተና ይዘት ከመርሀ ትምህርቱ አንጻር ምንምን እንዳካተተ ማየቱ ተገቢ ነው፡፡በ2013 ዓ.ም በቀረበው ፈተና ውስጥ ከ60 ጥያቄዎች በ16(26.7%)ተወክሏል፡፡ እነኚህ ጥያቄዎች ከመርሀትምህርቱ ምን እንዳካተቱ እና ምን እንዳላካተቱ አንድ በአንድ ስናይ 16(26.7%) ጥያቄዎች መርሀ ትምህርትን መሠረት አድርገው የተዘጋጁት እንደሚከተለው ነው፡-

ሱሰኝነት በሚለው ርዕስ የጭብጥ ጥያቄ፣ሥርዓተነጥብ፣ሥነቃል፣የድርሰት ክፍሎች፣ማስታወሻ

መጻፍ፣ የደብዳቤ ዓይነቶች፣ የጽኑፍዓይነቶች፣ግጥም፣የአንቀጽአጻጻፍ፣ ሀይለቃል እና መሠረታዊ ሀሳብ፣ዓረፍተነገር ፣ሀረጎች፣ የዓረፍተነገር መዋቅር፣እና የድርሰት አጻጻፍ እነኚህን በፈተና ውስጥ ማካተቱ ከቀሩት ክሂሎች እና የእውቀት ዘርፎች የተሻለ ውክልና እና ከ60 ጥያቄዎች በ16(26.7%) ጥያቄ መወከሉ ከሌሎቹ በተሸለ አብዛኛውን የፈተና ክፍል የሸፈነ በመሆኑ ለመጽሀፍ ክሂል የተሰጠውን ትኩረት ከመርሀ ትምህርቱም አንጻር የተሰጠው አፅንኦት እጅግ የተዛመደ መሆኑን እንረዳለን ።**በተጨማሪ ሠንጠረዥ አምስት ለ7ኛና 8ኛ ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመርሀ ትምህርቱ የተዘጋጁ የመፃፍ ክሂል ዝርዝር ይዘቶችን እና ሠንጠረዥ 6 አማርኛእንደሁለተኛቋንቋፈተና ውስጥ የመጻፍ ክሂል ፈተና ዝርዝር ይዘቶችን ይመልከቱ)**

የ2014 ዓ.ም የመጻፍ ክሂል የፈተና ይዘት ከመርሀ ትምህርቱ አንጻር ያላቸውን ግንኙነት ወይም ዝምድና ስንፈትሽ ከ60 ጥያቄዎች በ6(10%)ብቻ ነው የተወከለው ስድስቱም ጥያቄዎች ከመርሀ ትምህርቱ አንጻር ያላቸውን ውክልና ቀጥሎ እናያለን፦

ስድስቱም ጥያቄዎች ከመርሀ ትምህርቱ የወከሉት ሥርዓተ ነጥቦች፣ አንቀጽ፣ ዓረፍተ ነገር፣ ደብዳቤ፣ቃላትን እና ፈሊጣዊ አነጋገርን አካተው ይገኛሉ።ከመርሀትምህርቱ አንጻር ያለው ውክልና ዝቅተኛመሆኑን የመጻፍ ክሂል መርሀ ምህርቶችን ያልተካተቱትን ለአብነት ቀጥሎ እንመለከታለን፦ ውስብስብ ምዕላዶች ያሏቸውን ቃላት መፈደል ይችላሉ፤ፅሁፍን ከመምህር ያገኙትን ምጋቤ ምላሽ መሰረት በማድረግና በማመሳከሪያ ቅጾች በመታገዝ ጽሁፎቻቸውን ይከልሳሉ፤ ከተማሪዎች ጋርና ብቻቸውን ይሰራሉ፤የተለያዩ የመፃፍ ልምምዶችን (ሁነቶችን በጥንቃቄ መግለፅ፣ ስሜቶችን ጥሩ አድርጎ መግለፅ፣ መተረክ፣ መመሪያ መስጠት) ይለማመዳሉ፤ ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀው ታሪክ ውስጥ የገፀባህርያትን ድርጊቶች የሚያነፃፅሩ ወይም የሚመዝኑ ሶስት አንቀፆችን ይፅፋሉ፤ስለተነበበው ታሪክ ሶስት አንቀፆችን በመፃፍ ያሳጥራሉ፤ማመዛዘንን ለሚጠይቁ ጥያቄዎች አንቀፅ በመፃፍ መልስ ይሰጣሉ፤ሁለትየ የተለያዩ ፅሁፎችን የሚያነፃፅሩ ሶስት አንቀፆችን ይፅፋሉ፤ ለፅሁፍ ተገቢ አጨራረስ (መመርያ፤ ዐረፍተ ነገር ወይም አንቀፅ ሊሆን ይችላል)፤ የተሰጠውን መመሪያ በመጠቀም ስለሳቢያና ውጤት የሚገልፅ ፅሁፍ ይፅፋሉ፤ ስዕላዊ የሀሳብ አደረጃጀትን ስልት በመጠቀም በፅሁፍ የቀረበን ሃሳብ ያደራጃሉ፤ድምፅ በማሰማት የተነበበን ወይም የተደመጠን ፅሁፍ ሀሳቦች አሳጥረው ይፅፋሉ፤ሳቢያ እና ውጤት የሚገልጽ ጽሁፍ ይጽፋሉ።

ከነኚህ ከተጠቀሱት ብቻ እንኳ ብናይ ለመርሀ ትምህርቱም ሆነ ለክሂሉ ፈተና ትኩረት አልተሰጠም።**በተጨማሪ ሠንጠረዥ አምስት ለ7ኛና 8ኛ ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት**

**በመርሀ ትምህርቱ የተዘጋጁ የመፃፍ ክሂል ዝርዝር ይዘቶችን ይመልከቱ)**

ከላይ ለክሂሉ ፈተና ትኩረት አልተሰጠም የተባለበት ምክንያት በመርሀ ትምህርቱ የመጻፍ ክሂል ካለው የይዘት ስፋት አንጻር እና መርሀ ትምህርቱን መሰረት አድርጎ ለቋንቋ ትምህርቱ ከተደለደለው 90 ክፍለ ጊዜ ውስጥ 24 (26.7%) ሽፋን አንጻር በመርሀ ትምህርቱም ክሂሉም ላይ ትኩረት እንዳልተደረገና በጣም ዝቅተኛ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡(**በተጨማሪ ሠንጠረዥ 6 አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ፈተና ውስጥ የመጻፍ ክሂል ፈተና ዝርዝር ይዘቶችን ይመልከቱ)**

### 4.2.4.በሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ እና በክልላዊ ፈተናዎች መካካል ያለው ግንኙነት (ዝምድና)

ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመርሀ ትምህርቱ የተዘጋጁ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን በሠንጠረዥ ሰባት አይተናል፤በሠንጠረዥ ስምንት ደግሞ መርሀ ትምህርቱን በመወከል የቀረቡትን ፈተናዎች አይተናል፤በመሆኑም የፈተናውን ውክልናና ለመርሀ ትምህርቱ የተሰጠውን ሽፋን እንደሚከተለው እናያለን፡-

የሰዋስው ትምህርት በመርሀ ትምህርቱ አማካይነት የተደለደለለት የክፍለ ጊዜ ሽፋን በዓመት ከ90 ክፍለጊዜ 9(10%) ነው፡፡በ2013 ዓ.ም በቀረቡት የሰዋስው ፈተናዎች ውስጥ ከመርሀ ትምህርቱ ምን እንዳካተቱ ከጥያቄዎቹ አንፃር ቀጥሎ እናያለን፣

እንዲያው ለየት አድርጎ ለማቅረብ ጥያቄ ቁጥር 32፣33፣34 እና 39የርባታና የምስረታ ምዕላዶችን ወይም ቅጥያዎችን የሚጠይቁ ሲሆኑ 35፣36፣37፣38፣ 40 እና41 የቃል ክፍሎችን መሠረት ያደረጉ ጥያቄዎች ናቸው፡፡በመሆኑም ይህ ፈተና ከመርሀ ትምህርቱ ያካተተው ሶስት ነገሮችን ብቻ ነው እነርሱም የርባታና የምስረታ ምዕላዶችን እና የቃል ክፍሎችን ነው፤ይህ ብቻ ከሆነ ደግሞ ከመርሀ ትምህርት ምን ቀረ የሚለውን እስቲ ለአብነት እንመልከት፡-

በጣም የተለመዱ አዎንታዊ፣አሉታዊና መጠይቃዊ ምዕላዶችንወይምቃላትንእና በንግግር በጣም የተለመዱግስ መስራቾችን ይበይናሉ፣ይለያሉ(መደብ፣ሙያ፣ቁጥርናፆታአመልካች ቅጥያዎችን ያስተውሏል)፤ የጊዜናየቦታ የድግግሞሽ እና የሁኔታ ተውሳከ ግሶችን እንዲሁም የተለመዱ አመልካቾችንና መስተፃምሮችን የሚያመለክቱ ምዕላዶችን ወይም ቃላትን ከንግግር መለየት ይጀምራሉ፤(የመደብ፣የሙያ፣የቁጥርና የፆታ ምዕላዶችንያስተውሏል)፤

ይበይናሉ፤ ጥገኛ ሀረጎችንና እንደ መሙያ የሚያገለግሉ ስሞችን (በጥንታዊው ብያኔ ከ'የመሆን ግሶች' ጋር የሚመጡ) ይለያሉ፣ይበይናሉ፤እንግዲህ እነኚህ ከመርሀ ትምህርቱ ሳይካተቱ የቀሩ ናቸው፡፡ሆኖም ለሰዋስው ከተሰጠው ክፍለጊዜ እና ከመርሀ ትምህርቱ ስፋትና ጥልቀት አንጻር

የፈተናው ውክልና ለመርሀ ትምህርቱ ከተሰጠው ሽፋን አንፃር ተመጣጣኝ ይሆናሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡(**በተጨማሪ ሠንጠረዥ ሰባት ለ7ኛና 8ኛ ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመርሀ ትምህርቱ የተዘጋጁ የሰዋሰው ዝርዝር ይዘቶችን እና ሠንጠረዥ ሰባት አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ ፈተና ውስጥ የሰዋሰው ፈተና ይዘቶችን ይመልከቱ**)

የ2014ን ደግሞ ስናይ ከ60 ጥያቄዎች በ 9(15%)ጥያቄዎች ተወክሏል፤ዘጠኙም ጥያቄ ከመርሀ ትምህርት አንጻር በምን በምን እንደተወከዘርዝሩን እንመለከታለን፡፡ጥያቄ ቁጥር 15፣16፣17፣19 እና25 የቃል ክፍሎች ጥያቄ ሲሆኑ ጥያቄ ቁጥር 18፣26፣31 እና 32 የቃል እና የዓረፍተነገር ጥያቄዎች ናቸው ከክፍለጊዜ ድልደላ እና ከመርሀ ትምህርቱ ይዘት አንጻር ለፈተናው የተሰጠው ውክልናና ለመርሀ ትምህርቱ የተሰጠው ሽፋን ተገቢ ነው ማለት ይቻላል፡፡ስለዚህ ስለመርሀ ትምህርት ውክልና ስንተነትን መርሀ ትምህርቱ ውስጥ ያለው ይዘት ሁሉ በፈተናው ላይ ይገኛል ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ሊሆን ይገባል፡፡(**በተጨማሪ በ2013ቱ ትንታኔ ላይ በተጨማሪ ተመልከቱ የተባለውን በዚህኛውም መመልከት ይቻላል**)

### 4.2.5.በአፍልቆት፣መተርጎም እና ቃላትን የማጥናት ፈተና ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ እና በክልላዊ ፈተናዎች መካካል ያለው ግንኙነት (ዝምድና)

በመርሀ ትምህርቱ አማካይነት ወይም መሠረት ለመማር ማስተማሩ ሂደት በመጽሀፉ ውስጥ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከተመደበው 90 ክፍለጊዜ ውስጥ አፍልቆት፣መተርጎም እና ቃላትን ለማጥናት በ15 (16.6% )ክፍለጊዜያት የተደለደለ ሲሆን በ2013 ዓ.ም በአፍልቆት፣ መተርጎም እና ቃላትን የማጥናትፈተና ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ እና በክልላዊ ፈተናዎች መካካል ያለው ግንኙነት(ዝምድና) ለማወቅ በቅድሚያ ከክፍለጊዜውና ከመርሀ ትምህርቱ አንፃር ከ60 ጥያቄዎች በስንት ጥያቄዎች እንደተወከለ መፈተሽ ተገቢ ነው፡፡በመሆኑም በሠንጠረዥ 12 እንደተገለጸው በ8(13.3% )ተወክሏል፡፡ቢሆንም ቃላትን ከማጥናት አኳያ በመርሀ ትምህርቱ ከተዘረዘሩት ውስጥ በምን በምን እንደተወከለ ማየቱ አስፈላጊ ነው፡፡ጥያቄ ቁጥር 24፣30 እና 31 ፍደላና ቅደም ተከተል ማስተካከል ጥያቄ ቁጥር 25፣26 እና27 እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ፣28 እና 29 ሥነፍቺናቸው፡፡ከመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ያላካተቱት የትኞቹን እንደሆነ ለአብነት እንደሚከተለው እንመለከታለን፡-

ቃላትን ለማንበብ እስርና ነፃ ምዕላዶችን ማጣመርና መነጣጠል ይችላሉ፤ የታሰበውን ውጤት ሊያመጣ የሚችል ስልት ለቋንቋው በመጠቀም ውስብስብ መዋቅር ያላቸውን ቃላት ማንበብ እናመጠቀም ይችላሉ፡፡ አዳዲስ ቃላትን ለማንበብ የምዕላድ ትርጉም ዕውቀት (ቃል መስራች እና /ወይም የእርባታ ምዕላዶችን) ይጠቀማሉ፡፡ ቃላትን ለማንበብ የምእላዶችን ውስብስብ

አውዳዊ ፍቺ ይጠቀማሉ፡፡ከክፍለ ጊዜ እና ከመርሀ ትምህርቱ አንጻር የፈተናው ጥያቄ ብዛትም ከመርሀ ትምህርቱ ሽፋን አኳያም ዝቅተኛ ሆኖ ነው የተገኘው በንፅፅር ከቃላዊ ክሂል እና ከሰዋሰው አንጻር እንኳ ብናይ ዝቅተኛ ውክልናና ሽፋን ነው የተሰጠው፡፡(**በተጨማሪ ሠንጠረዥ አሥር ለ7ኛና 8ኛ ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመርሀ ትምህርቱ የተዘጋጁ የአፍልቆት፣መተርጎም እና ቃላትን ማጥናት ዝርዝር ይዘቶችን እና ሠንጠረዥአስራአንድ ለ8ኛ ክፍልአማርኛእንደሁለተኛቋንቋፈተና ውስጥ**

**የአፍልቆት፣መተርጎም እና ቃላትን የማጥናትፈተና ይዘቶችን ይመልከቱ)**

የ2014ዓ.ምፈተና ውስጥ የአፍልቆት፣መተርጎም እና ቃላትን የማጥናትፈተና ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ እና በክልላዊ ፈተናዎች መካካል ያለው ግንኙነት(ዝምድና) ከክፍለ ጊዜውና ከመርሀ ትምህርቱ ስፋት እና ጥልቀት አንፃር የተሰጠው ውክልናና ሽፋን እንደሚከተለው እናያለን፡-
በዓመቱ ውስጥ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከተመደበው 90 ክፍለጊዜ በ15(16.6)
ተደልድሏል፤ከዚህ ክፍለጊዜ እና ከመርሀ ትምህርቱ አንፃር በ15 (25%)ጥያቄ
ተወክሏል፡፡15ቱም ጥያቄ ከመርሀ ትምህርቱ አኳያ በምን በምን እንደተወከሉ ዘርዝር አርገን
እናያለን፡-ጥያቄ ቁጥር 13፣14እና 27 ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ፤21፣22 እና 23
ሥነፍቺ(ትርጉም)፤20 እና 28 አባባል፤ 24 መንስዔና ውጤት፤29ና 30እርባታና ምስረታ
32፣.33 እና 59 የቃላት ቅደምተከተል ፤51 ቅጥያ ምዕላድ ተወክለዋል፡፡ከመርሀ ትምህርት
ውሰጥ ሳይወከሉ የቀሩት የሚከተሉት ናቸው፡-

የፊደላን ስደራ ህግጋት ዕውቀት ውስብስብ በሆኑቃላት ይተገብራሉ፡፡የፊደላት ህግጋት ምን እንደሆኑና እንዴት እንደሚሰሩ ያብራራሉ፤ ቃላትን ለማንበብ እስርና ነፃ ምዕላዶችን ማጣመርና መነጣጠል ይችላሉ፤የታሰበውን ውጤት ሊያመጣ የሚችል ስልት በቋንቋው በመጠቀም ውስብስብ መዋቅር ያላቸውን ቃላት ማንበብ እና መጠቀም ይችላሉ፡፡መቼስ ሁሉም በፈተና አይወከሉም፡፡ ቢሆንም ግን አብዛኛው በመርሀ ትምህርቱ ክፍል ስለተወከለ ከሌሎቹ አንፃር በጣም የተሻለ ውክልና ነው፡፡ እንዲያውም በንፅፅር ብናይ ከ60 ጥያቄዎች የ15 (25%) ሽፋን በመስጠት ከሌሎቹ የክሂልና የዕውቀት ዘርፎች ሁሉ አብላጫውን ክፍል (የፈተናውን 25%) እንደሸፈነ እንገነዘባለን፡፡

### 4.2.6.የዘውግ እና ሥነ ጽሁፍ አላባውያን ፈተና ይዘቶች በመርሀ ትምህርቱ እና በክልላዊ ፈተናዎች መካካል ያለው ግንኙነት (ዝምድና)

በሠንጠረዥ አሥራሁለት ላይ እንደተመለከትነው የዘውግ እና ሥነጽሁፍ አላባውያን እንደሌሎቹ የክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች ለአማርኛ ቋንቋ ከተመደበው 90 ክፍለ ጊዜ ለብቻው

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ የለም ከሌሎቹ ጋር ተዳብሎ ወይም ለሌሎቹ ማስተማሪያ ሆኖ ነው የቀረበው፤ ለአብነት በመምህሩ መምሪያ እና በመማሪያ መጽሀፍ ላይ ምዕራፍ አራት ባህላዊ ግጥሞች፣ምዕራፍ አሥር ተውኔትን ብቻ ማየቱ በቂ ነው። የማስተማሪያ መጽሀፉ እና የመምህሩ መምሪያ ከመርሀ ትምህርቱ ሲዘጋጁ እያንዳንዱ ምዕራፍ በክሂሎች ጀምረው በሰዋስው ነው የሚጨርሱት ስለዚህ በዝግጅቱ እንደሰዋስውም ሥነፅሁፍ የሚል ርዕስ ለብቻው ባለመኖሩ ክፍለጊዜም ለብቻው የለውም።ሆኖም ግን በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ሥነጽሁፍን በተመለከተ መማር የሚገባቸው ይዘቶች በመኖራቸው ወይም በመዘጋጀታቸው ፈተናዎች ውስጥ መገኘት ግድ ይላል።በመሆኑም በ2013 ዓ.ም ለ8ኛ ክፍልአማርኛእንደሁለተኛቋንቋፈተና ውስጥ የዘውግ(ድርሳናት) እና ሥነጽሁፍ አላባውያን ፈተና ይዘቶች ከመርሀትምህርቱ ይዘት አኳያ ያላቸውን ዝምድና እና ውክልና እንደሚከተለው እናያለን፡-

ከ60 ጥያቄዎች በሶስት ጥያቄ ነው የተወከሉት፤ሶስቱ ጥያቄዎች በመርሀ ትምህርቱ የወከሉት፣ጥያቄ58 ምሳሌያዊ ንግግር፣59 እና 60 ቃላዊ ግጥም ነው።ይህ ብቻ ከሆነ ደግሞ በመርሀ ትምህርቱ ውክልና ሳያገኙ የቀሩትን መጥቀሱ ተገቢ ነው። ስለዚህ ውክልና ያላገኙት አፈታሪክ አንብበው ምላሽ ይሰጣሉ። የፈሊጦችን፣ የተለዋጭ ዘይቤና የተነፃፃሪ ዘይቤን ትርጉም ተረድተው ያብራራሉ፤ ዘይቤያዊ የቋንቋ አጠቃቀሞችን ማለትም ምናባዊና ስሜት ገላጭ ቃላትን ይረዳሉ፤ ገጸባህሪያትንና የግጥም መዋቅር መሠረታውያንን ይለያሉ።ለምሳሌ ምናባዊ ምስስሎሽ፣ስንኝ፣ዜማ፣ምት፤የግጥም ዓይነቶችን ይለያሉ፤የመጽሄት መጣጥፎችንና የአንድን ነገር አሰራር የሚገልፁ ፅሁፎችንአንብበው ሃሳብ ይሰጣሉ።ከፈተና እና ከመርሀ ትምህርት ውክልና እና ሽፋን አንፃር በጣም ዝቅተኛ ነው። **(በተጨማሪ ሠንጠረዥ ስምንት ለ7ኛና 8ኛ ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመርሀ ትምህርቱ የተዘጋጁ የዘውግ እና ሥነጽሁፍ አላባውያንዝርዝር ይዘቶችን እና ሠንጠረዥ ዘጠኝ የዘውግ (ድርሳናት) እና ሥነጽሁፍ አላባውያን ፈተና ይዘቶችን ይመልከቱ)**

በአጠቃላይ በመርሀ ትምህርቱ እና በ2013 ዓ.ም እና በ2014 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ ማጠናቀቂያ (ለ8ኛ ክፍል) አማርኛእንደሁለተኛ ቋንቋ ፈተና ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ክሂሎች እና የዕውቀት ዘርፎች ያገኙት ውክልና እና ሽፋን በሠንጠረዥ እና በማብራሪያ ወይም በገለጻ የተቀመጡት የሁለቱንም ዓመት ሰናጠቃልላቸው የሚከተሉትን ይመስላሉ።

መናገርና ማዳመጥ የተሰጠው የክፍለጊዜ ሽፋን 18(20 )የፈተና ውክልና23(38.3)

የማናበብ ክሂል=የክፍለጊዜ ሽፋን 66 (73.4) የፈተና ውክልና 21 (35)

የመጻፍ ክሂል=የክፍለጊዜ ሽፋን 48 (53.4) የፈተና ውክልና 22 (36.7 )

ሰዋስው=የክፍለ ጊዜ ሽፋን 18 (20 )የፈተና ውክልና 19 (31.7 )

አፍልቆተ /መተርጎም/ቃላት ማጥናት=የክፍለ ጊዜ ሽፋን 30 (33.2 )የፈተና ውክልና 23(38.3) የዘውግ(ድርሳናት)ሥነጽሁፍ አላባውያን=የፈተና ውክልና 12(20 )አግኝተዋል፡፡ከጥቅል ውክልናና ሽፋን አንፃር ቃላዊ ክሂል (መናገርና ማዳመጥ) ከአፍልቆተ /መተርጎም/ቃላትን ማጥናት ጋር እኩል የፈተና ውክልና ይዘው የፈተናውን 46 (76 )በመያዝ ከፍተኛ ድርሻ ወስደዋል፡፡ነገርግን ከክፍለ ጊዜ አንፃር ስናይ ሁለቱም አይመጣጠኑም አፍልቆተ /መተርጎም/ቃላትን ማጥናት በ12 ክፍለ ጊዜ ቃላዊ ክሂልን ይበልጣል፡፡በመቀጠል የመጻፍ ክሂል በ48 (53.4) ክፍለጊዜ ሽፋን የ22 (36.7)ጥያቄ ውክልና በማግኘት ሁለተኛ ይሆናል፡፡ከመጻፍ በመቀጠል ማናበብ የ66 ክፍለ ጊዜ ሽፋን በመያዝ የ21 (35 )ጥያቄ ውክልና በማግኘት 3ኛ ደረጃ ይሆናል፡፡ሰዋስው በ18(20 ) ክፍለ ጊዜ ሽፋን የ19(31.7 )ጥያቄ ውክልና በማግኘት አራተኛ ሲሆን የመጨረሻውን ጥያቄ ውክልና ያገኘው በ12 (20) የዘውግ(ድርሳናት) ሥነጽሁፍ አላባውያን ሆኗል፡፡

**የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ከመርሀ ትምህርቱ አንጻር በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ያላቸው የይዘት ድግግሞሽ መጠን እና ድግግሞሹ የተተገበረበት ክፍለጊዜ መጠን**

| | የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ከመርሀ ትምህርቱ አንጻር በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ | የይዘትድግግሞሽ መጠን | | ድግግሞሹ የተካሄደበት የመማር ማስተማር ክንውን የክፍለ ጊዜ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | የንባብ ክሂል | 55 | 26.44% | 33 | 36.7% |
| 2 | የጽህፈት ክሂል | 31 | 14.9% | 24 | 26.7% |
| 3 | የንግግር ክሂል | 19 | 9.13% | 5 | 5.6% |
| 4 | የማዳመጥ ክሂል | 11 | 5.29% | 4 | 4.4% |
| 5. | የሰዋስውዕውቀት | 31 | 14.9% | 9 | 10% |
| 6 | አፍልቆተ/መተርጎም/ቃላትንማጥና ት | 61 | 29.34% | 15 | 16.6% |
| | ድምር | 208 | 100% | 90 | 100% |

የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ከመርሀ ትምህርቱ አንጻር በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ያላቸው የይዘት ድግግሞሽ መጠን እና ድግግሞሹ የተተገበረበት ክፍለጊዜ መጠንን በደረጃ ለማሳየት ወይም ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ከክሂሎቶቹ እና ከዕውቀት ዘርፎቹ በአስሩም ምዕራፍ የበለጠ ትኩረት የተደረገባቸውን በቅደም ተከተል እንደሚከተለው እንመለከታለን ፡-

ካሉት ክሂል ዘርፎችና የዕውቀት ዘርፎች ቀዳሚውን ስፍራ ይዞ የሚገኘው በ61 ድግግሞሽ አፍልቆተ/መተርጎም/ቃላትን ማጥናትሲሆን በ15 ክፍለጊዜ ሽፋን ነው ይህ ሁሉ ድግግሞሽ

የተተገበረው፤በመቀጠል የንባብ ክሂል 55 ጊዜ ተደጋግሞ የቀረበ ሲሆን 33 የክፍለ ጊዜ ሽፋን በማግኘትም ቀጥሎ ካሉት ይበልጣል፤በሶስተኛ ደረጃ የክፍለጊዜ ልዩነት ቢኖራቸውም በድግግሞሹ ግን እኩል ቁጥር ያላቸው የጽህፈት ክሂል እና የሰዋሰው ዕውቀት ትምህርቶች ናቸው፤በአራተኛነት ደረጃ የሚገኘው በ5 ክፍለጊዜ ሽፋን 19 ጊዜ የተደጋገመው የንግግር ክሂል ነው፡፡ በመጨረሻም በ4 ክፍለ ጊዜ ሽፋን 11 ጊዜ ተደጋግሞ የቀረበው የማዳመጥ ክሂል ነው፡፡ ከሁሉም ለየት የሚለው ግን የዘውግ እና የሥነጽሁፍ አላባውያን ነው ይህ የዕውቀት ዘርፍ በመርሀ ትምህርቱ ላይ የተዘጋጀ ሲሆን በግል እንደሌሎቹ በክፍለ ጊዜ አልተሸነሸነም ወይም አልተደለደለም፤ይህ የሆነበት ምክንያት ከሌሎች ክሂሎች እና ከሰዋሰው ጋር ተቀላቅሎ ነው በትምህርትነት የተሰጠው፡፡

## 4.3.በሁለቱም ፈተናዎች የቀረቡ የፈተና ጥያቄዎች ከፈተና መርሆች አንጻር ያላቸው ጠንካራና ደካማ ጎን

በምዕራፍ ሁለት 2.1.5.4.2. ላይ በችሎታ መለኪያ ፈተና ዝግጅት ጊዜ የሚዘጋጁ ጥያቄዎች ተማሪዎች የተማሩትን የትምህርት ልምድ ወይም ይዘት ያካተተ መሆን እንዳለበት Madsen(1983) እንደሚከተለው ገልጾ ነበር፤የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች የብዙ ጊዜ የክፍል ውስጥ ክንውኖች መከሰቻዎች በመሆናቸው መርሀ ትምህርቱን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ በሌላ አገላለጽ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች መርሀ ትምህርቱን ተመርኩዘው መሰናዳታቸው በመርሀ ትምህርቱ የቀረቡ ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ባለቤትነት እንዲላበሱ ከማድረጉም በላይ የሚፈለገውን እውቀት ለመፈተሽ ያግዛል፤በመሆኑም የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች የተነሱበትን አላማ ከግብ እንዲያደርሱ በቀረበው መርሀ ትምህርት ላይ መመስረት አለባቸው በማለት ጠቁሞናል፡፡ በመሆኑምየዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሲዳማ ክልላዊ መንግስት ከ2013 እስከ 2014ዓ.ምየስምንተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት እና ለዚህ ክፍል የተሰጡ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ያላቸውን የይዘት ተዛምዶ ወይም ተገቢነት መፈተሽ ሲሆን የሁለቱም ዓመት 120 ጥያቄዎች የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች በመሆናቸው ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን እንደሚከተለው እንመለከታለን፡-

### 4.3.1.ደካማ ጎኖች

I. **ክሂሎችንና የዕውቀት ዘርፎችን በትክክል አድራሻ አድርጎ ከመፈተን አንፃር**

በፈተና ወቅት ተማሪዎችን ለፈተናው የሚመራ መመሪያ ነው፤ተማሪዎቹ መመሪያን መሰረት አድርገው የሚሰሩ ሲሆን መመሪያው የተዛባ ወይም ጥያቄውን በትክክል አድራሻ አድርጎ ካልተዘጋጀ እና የሚያሻማ ከሆነ ተማሪዎቹ ለመስራት ይቸገራሉ፡፡በመሆኑም በ2014 ዓ.ም ፈተና ላይ ከጥያቄ ቁጥር 12 እስከ 33 ቃላትን እና ዐረፍተነገርን በሚመለከት ሊጠየቅ

የተዘጋጁ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን በነዚህ ጥያቄዎች ውስጥ ከጥያቄ ቁጥር15 እስከ 19 ድረስ ያሉት የሚጠይቁት ሰዋሰውን ነው፡፡ መመሪያውን እና ጥያቄዎቹን እስቲ እንመልከት፡-

***መመሪያ፣ ከተራቁጥር 12 እስከ 33 ያሉ ጥያቄዎች ቃላትንና አረፍተ ነገሮችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ለእያንዳንዳቸው መልሶች ይሆናሉ ተብለው ከተሰጡት አማራጮች መካከል ይበልጥ ትክክል የሆነውን በመምረጥ በመልስ መስጫው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልሱ፡፡***

15.ከሚከተሉት ውስጥ ስም የሆነው የቱ ነው? A.አጠገብ B. ላይ C. አጠና D. በር

16. በግስ የቃል ክፍል የሚመደበው የትኛው ነው? A. ጎበዝ C. ጀግናB. ጻፈ D. እኩል

17.‹‹አለሚቱ ከአባቷ ደብተሯን ወሰደች›› በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ መስተዋድዱ የትኛው ነው? A.ከአባቷ B.አባቷ C.ከ D.ን

18.ከሚከተሉት ውስጥ ውስብስብ አረፍተ ነገር የሆነው የቱ ነው? A. እንግዶቹ ቡና ጠጥተው ሄዱ B.እናቴ በጠዋት ቁርስ ሰራች C. አጎቴ ትናንት ወደ ሀዋሳ መጣ D.አባቴ ታታሪ ገበሬ ነው፡፡

19.አገባባዊ (ሰዋስዋዊ) ስህተት የሌለበት አረፍተ ነገር የትኛው ነው? A. ብዙ ተማሪዎች ቀርቷል፡፡ B.አንቺ ቶሎ ድረሽ፡፡ C.እሷ መጣን፡፡ D.ትናንት እየሄዱ ነው፡፡

ከዚህ በታች የምናየው ደግሞ የፈተናው መመሪያ የሚያዘው ወይም የሚያመለክተው የሚጠይቀው ጥያቄ ድርሰትንና ስነ ጽሁፍን የሚመለከቱ እንደሆነ ነው ነገር ግን ጥያቄ ቁጥር ‹‹51›› የሚያመለክተን የሰዋሰው ወይም የሥነልሳን ጥያቄ ነው፤መመሪያው እና ጥያቄው ስላልተገናኙ (ስህተት) በመሆኑ ተማሪዎቹ ትክክለኛውን ምላሽ ለመመለስ ይቸገሩ ይሆናል፡፡

***መመሪያ፣ከተራ ቁጥር 44 እስከ 60 ያሉ ጥያቄዎች ድርሰትንና ስነጽሁፍን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ይበልጥ ትክክል የሆነውን በመምረጥ በመልስ መስጫው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልሱ፡፡***

51.ከሚከተሉት ቃላት መካከል የመነሻ ቅጥያ ያለው የትኛው ነው? A.ስለተከናወነ B.ቸርነት C.ስብሰባው D. ሰበረው በዚሁ መመሪያ ቀጥሎ የምናየው ጥያቄ ቁጥር /55/ ድርሰትንና ስነ ጽሁፍን የሚመለከት

ሳይሆን ስለ ደብዳቤ አጻጻፍ ነው ባጭሩ ይህም ስህተት ነው፡፡

55. በማመልከቻ ደብዳቤ ውስጥ ሊካተት <u>**የማይችለው**</u> የትኛው ነው? A.የአመልካች ስም B.የወዳጅ ሰላምታ C. ጉዳዩ የሚል አጭርመግለጫ D.ፊርማ

ቀጥሎ ጥያቄ ቁጥር/59/ የቃላት ጥያቄ እንጂ ድርሰትንና ስነ ጽሁፍን የሚመለከት አይደለም

59.ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት በፊደል ገበታ ቅድም ተከተል መሰረት መጀመሪያ ላይ የሚመጣው የትኛው ው?A. ተቸገረB. ረሳ ና የአማራጮች አሻሚነት C. ትምህርት.D.ወሰነ

ከላይ የተጠቀሱት የፈተና ጥያቄ እና መመሪያው ያለመጣጣም (መለያየት) ፈተናውን (ጥያቄውን አሻሚ ያደርገዋል፤በመሆኑም ለተጠያቂዎቹ (ተፈታኞቹ)ግልጽ መመሪያ እና ግልጽ

የተጣጣመ ጥያቄ ሊቀርብ (ሊዘጋጅ)ይገባ ነበር።(**በተጨማሪ አባሪ 2 ይመልከቱ**)

## II. የፈተና ጥያቄዎች እና የአማራጮች አሻሚነት

የፈተና ጥያቄዎችለተፈታኞች ከፈተና መርሆዎች አንፃር ምንም አሻሚነት ሳይኖራቸው ግልጽ

ሆነው ሊቀርቡ ይገባል።ነገር ግን በሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ማጠናቀቂያ (ለ8ኛ ክፍል) አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የ2013 እና 2014 ዓ.ም ፈተና ውስጥ የጥቄዎችና የአማርጮች አሻሚነት ተገኝተዋል።ቀደም ብለን የ2013 ዓ.ም እንደሚከተለው እናያለን፦

8.ውይይት ምንድ ነው? A.የንግግር ችሎታ B.የሀሳብ ልውውጥ C.ሀሳብ ድምዳሜ D.የንግግር አይነት

ጥያቄው የውይይት ምንነትን የሚጠይቅ የጽንሰ ሀሳብ ጥያቄ ነበር፤ሁለት አማራጮች አሻሚነት ያላቸው አማራጭ B.**<u>የሀሳብ ልውውጥ</u>**የሚለውን ስንተረጉመው በመሠረቱ ውይይት የሃሳብ ልውውጥ ነው የሀሳብ ልውጥ ካልሆነ ምኑን ውይይት ይሆናል? ስለዚህ ምንም ጥርጥር የሌለው ውይይት የሀሳብ ልውውጥ ነው፤አማራጭ D.**<u>የንግግር አይነት</u>** የሚለውን ስናይ

ውይይት፣ጭውውት እና ክርክር የተለያየ ዓላማ ያላቸው የንግግር ዓይነቶች ናቸው፤በተለይ ጭውውት የሀሳብ ልውውጥ ነው፤ውይይትም የየሀሳብ ልውውጥ ያለበት የንግግር ዓይነት በመሆኑ ተፈታኞች የትኛውን ይምረጡ?

24.ከሚከተሉት ቃላት በፊደል ቅደም ተከተል የሚቀድመው የትኛው ነው?A.ሀኪም B.ልማት C.ለማን D.ሃገር

የዚህ ጥያቄ ዓላማ ከሆሄያት(ፊደላት)የሀ ቀዳሚነትን ለመግለጽ ነው፤ግን በምርጫዎቹ ውስጥ ከተጠቀሱት ሞክሼ<u>/ሀ/እና/ሐ/</u>የትኛውን?ይህ ጥያቄ ተጠንቶ በዓላማ የተጠየቀ አይደለም፤ይህን ጥያቄ ለመጠየቅ ስለሞክሼ ፊደላት አጠቃቀም በደምብ ሊማሩ ወይም ሊረዱ ይገባል። ስለዚህ ተፈታኞች የየትኛውን /ሀ/ ዝርያ መመለስ እንዳለባቸው ግልጽ ላይሆን ይችላል።

30.መፅሀፋችሁን ነገ እንድትመጡ ይዛችሁ።እነዚህ ቃላት በቅደም ተከተል ሲቀመጡ የተሸለ አረፍተነገር የሚሆነው የትኛው ነው? A.መጽሀፋችሁን እንድታመጡነገ ይዛችሁ B.እንድትመጡ ነገ መጽሀፍ ይዛችሁ C.ነገ መጽሀፋችሁን ይዛችሁ እንድትመጡ D.መጽሀፋችሁን ይዛችሁ ነገ እንድትመጡ።የዚህን ጥያቄ አማራጭ C.**<u>ነገ መጽሀፋችሁን</u>** ይዛችሁ እንድትመጡ የሚለውን እና **<u>D.መጽሀፋችሁን</u>** ይዛችሁ ነገ እንድትመጡ የሚለው ይሆናል። በሁለቱም አማራጮች መጽሀፍ የአረፍተነገሩ ተሳቢ ነው ፤የዚህ አረፍተነገር ባለቤት

3ኛ መደብ ብዙ ቁጥር ነው የጊዜ ገላጭ የሆነው ተውሳከ ግሱ በሁለቱም ቦታ ጊዜን በአግባቡ እየገለጸ ነው፡፡ስለዚህ በሁለቱም አማራጮች ስህተት ያለ መስሎ ስለማይታይ ለመምረጥ ይቸገራሉ፡፡

**በ2014 ዓ.ም ፈተና ላይ ደግሞ ስናይ ጥያቄ ታታሪሆነ D. እንጀራተጋገረለት**

23.‹‹አለሚቱቤ<u>ቷን</u>ትወዳለች፡፡››የተሰመረበትቃልየገባውበምንፍቺውነው?

A.በእማሬያዊB.በቀጥተኛ C.በመዝገበቃላዊD.በፍካሬያዊ፡፡ይህ ጥያቄ መጠየቅ የነበረበት አማራጮቹን መሠረት በማድረግ ነበር የተሰመረበት ቃል እማሬያዊ ፍቺ፣ፍካሬያዊ

ፍቺ፣መዝገበቃላዊ (ቀጥተኛ ፍቺ) የሚሆነው የትኛው አማራጭ ነው ተብሎ ነበር መዋቀር የነበረበት፤ስለዚህ ተፈታኞቹ የትኛውን አማራጭ ይምረጡ እንደአጠያየቁ ሁሉም መልስ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው፤በመሆኑም ጥያቄው ከነአማራጮቹ አሻሚ ነው፡፡

**III. የመርሀ ትምህርትን ሽፋን ከመጠበቅ አንጻር የጥያቄዎቹ ፍትሀዊነት ወይም ተደራሽነት**

በምዕራፍ ሁለት ላይWeir (1990-25) ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቶች ላይ ለሚዘጋጁ ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች አጽንኦት ይሳጣሉ፡፡የችሎታ ማረጋገጫ ፈተናዎች በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ያሉ ይዘቶችን የሚያንጸባርቁና ስለተማሪዎች ብቃት ተገቢውን ውሳኔና መረጃ የሚሰጡ ናቸው:: ማንኛውም ፈተና ይዘታዊ ተገቢነት ከሌለው በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ ፈተናው በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ለሚገኙት ይዘቶች አስፈላጊውን አጽንኦት በመስጠት የፈተናውን መስፈርቶች ማሟላቱን ይገመግማል በማለት ገልጸውነበር፡፡ ከዚህ አንፃር የሲዳማብሄራዊክልላዊመንግስትየመጀመሪያደረጃ

ማጠናቀቂያ(ለ8ኛ ክፍል)አማርኛእንደሁለተኛቋንቋ**የ2013 እና 2014** ዓ.ም ፈተና ውስጥ የመሪሀ ትምህርት ዝርዝር ይዘቶች ውስጥ በተለይ የቃላዊ ክሂል ፈተና ከመርሀ ትምህርቱ አንፃር ተደራሽነቱ ውስን ነው ይህንን እንደሚከተለው እናያለን፡-

በ2013 ዓ.ም ፈተና ውስጥ ጥያቄ ቁጥር**4.በአንድ ክፍል** ውስጥ ተማሪዎች <u>**ውይይት**</u>

<u>**የማድረግ**</u> ጠቀሜታ ምንድነው? A.የማዳመጥና የመቃወም ችሎታ ለማሳደግB.የማንበብ ክሂልን ለማሳደግ C ጽሁፍ ሲነበብላቸው እንዲያደምጡ ለማስቻልD የመናገር ክሂልን ለማሳደግ

**5.**ወላጆች ለልጆቻቸው ስላሉባቸው ችግሮች ከትምህርት ቤቱ የስራ ሀላፊዎች አካላት ጋር ተነጋገሩ፣ከዚያ በኋላ ተማሪዎቹ የባህርይ ለውጥ አሳዩ? A.የክርክርን ጠቀሜት B.የጭውውት ጠቀሜታ C የውይይትን ጠቀሜታ D. የዘገባን ጠቀሜታ

**6.ከሚከተሉት** አማራጮች መካከል<u>**የውይይት አዘገጃጀት መመሪያ ሊሆን የሚችለው**</u>?A.ችግርን ለመፍታት በጋራ ሀሳብ ላይ መስማማት ማቀድ B.ተቃራኒ ሀሳቦችን ይዞ መቅረብ C.የራስን

ሀሳብ አግባብቶ ለማሳመን በቂ ማስረጃ ማዘጋጀት D.ተወያዮችን እኩል ባልሆነ ሁለት ቡድኖች መክፈል.

7.ከሚከተሉት ውስጥ**የውይይት መመሪያ የሆነው**:-A.በቅደም ተከተል ማደራጀት B.ከጽሁፍ ፍሬማውጣት C.የክርክርን ጠቃሚነት ማስረዳት D.በርእሱ ዙሪያ ግንዛቤ ማግኘት

8.**ውይይት ምንድነው?** A.የንግግር ችሎታ B.የሀሳብ ልውውጥ C.ሀሳብ ድምዳሜ D.የንግግር አይነት

9.**ከሚከተሉት** አንዱ **የውይይት አቀራረብ መመሪያ** የማያመለክተው:-A.ተራን ጠብቆ መናገር፣ B.ርዕሰ ጉዳዩን መረዳት C.ስለርእሱ ሀሳብ ማግኘት D.ተራን ሳይጠብቁ መናገር

10**በመማሪያ** ክፍልውስጥ በመምህር እገዛ **ክርክር ማድረግ** ለምን ይጠቅማል?A.ምክንያታዊ በሆነ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ሀሳብ የማቅረብ ችሎታ ለማሳደግ B.ከሌሎች ሰዎች ጋር ሀገራዊ ሀሳብ ለመለዋወጥ C.ለክርክር የተሰጠውን ጊዜ በአግባቡ ለመጠቀም D.ለመምህር ሀሳብን ለማቅረብ

11.**የክርክር አዘገጃጀት** መመሪያ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?A.ሀሳብ በቅደም ተከተል ላይሆን ይችላል B.ሃሳብ ቅደምተከተል ባይኖረው ይመከራል C.ሃሳብን በቅደም ተከተል ማቅረብ D.ሃሳብን ለተቃራኒ ወገን ቀድሞ አለማካፈል

12.**ከሚከተሉት** መካከል ስለ **ክርክር አዘገጃጀት** እውነት የሆነውየትኛው ነው?

A.የራስ መከራከሪያ ሀሳብን ለማንም አለመናገር B.በክርክር ወቅት ሀሳብን ለማሳመን የሚረዱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ C.የሌሎችን ሀሳብ ለመጫን መሞከር D.ረዘም ያለ ጊዜ ወስዶ መናገር C.የውይይት ጠቀሜታ D.የዘገባን ጠቀሜታ

እነኚህን የቃላዊ ክሂል ፈተና ጥያቄዎች ስናይ **ከ12ቱ ጥያቄ 9ኙ** የውይይትና የክርክር ጥያቄዎች ናቸው፤ከውይይትና ክርክር ደግሞ አብላጫውን የያዘው **ከ9ኙ 6ቱ** (ከ4ኛው ጥያቄ እስከ 7ኛ) ድረስ ያለው የውይይት ጥያቄዎች ናቸው፤ቀሪዎቹ 3ቱ (ከ9ኛ እስከ 12ኛ)ጥያቄ ድረስ ክርክር ነው፡፡በተለይ አብዛኛዎቹ ጥያቄዎቹ ስለውይይት መመሪያ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ እነኚህን ጥያቄዎች ስናይ ቃላዊ መርሀ ትምህርቶቹ ውይይትና ክርክር ብቻ አይደሉም **ሠንጠረዥ አንድንለ7ኛና 8ኛ ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመርሀ ትምህርቱ የተዘጋጁ የቃላዊ ክሂል (ማዳመጥና መናገር) ዝርዝር ይዘቶችን መመልከት ይቻላል፡፡**

የ2014 ዓ.ም ደግሞ እንደሚከተለው እናያለን፡-

4.**በክርክር** ዝግጅት ወቅት በቅድሚያ ትኩረት የሚሠጠውየቱ ነው?A.ርእሱንለአድማጭ ማስተዋወቅ B.የማጠቃልያ ሀሳብማቅረብC. ክርክሩን በወጉ መቋጨት D.የመከራከሪያ ርእስ መምረጥ

6.**<u>በክርክር</u>** አዘገጃጀት ወቅት በመጨረሻ የሚከናወነው የትኛው ነው? A. ለክርክሩ አጋዥ መረጃዎችን ማሰባሰብB.የማጠቃለያ ሐሳብ ማዘጋጀትC.መረጃውን በቅደም ተከተል ማደራጀትD.ርእስ መፈለግና መምረጥ

7.**የክርክር** አዘገጃጀት መመሪያ ትክክለኛው ቅደም ተከተልየትኛውነው?A.መግቢያ ሐሳብ ማዘጋጀት B.ርእስ መምረጥ C.ቅደም ተከተልማስያዝ D.መረጃዎችንመሰብሰብ

A. 3፣ 4፣ 2፣1 C. 4፣ 3፣ 2፣ 1B. 3፣ 1፣ 2፣ 4 D.2፣1፣3፣4

8.**<u>ክርክር ምንድ ነ</u>**ው?

A. በሰዎች መካከል የሚደረግ የሐሳብ ልውውጥ ነው፡፡B.ለችግሮችየመፍትሔ ሐሳብ መጠቆሚያ ነው፡፡C.በሁለት ቡድኖች መካከል የሚደረግ ሙግት ነው፡፡D.የውሳኔ ሐሳብ ማንሸራሸሪያ ነው፡፡

9.ከሚከተሉት መካከል **<u>ከክርክር</u>**የሚገኘው ጥቅም የትኛውነው?A.አሸናፊ የሆነውን ለመሸለም ነው፡፡

B.ግንዛቤ ጨብጦ ሌሎችን የማሳመን አቅም ለመፍጠር ነው፡፡C. ታዋቂነትን በማትረፍ ዝናን ለማጎናጸፍነው፡፡D.በሰው ዘንድ የበላይነትን ለማትረፍ ነው፡፡ከ11ቃላዊ ክሂል 5ቱ ስለክርክር ብቻ ነው፡፡ይህ የጥያቄ አዘገጃጀት የመርህ ትምህርቱን ሽፋን አይወክልም ቢያንስ ለ11ዱ ጥያቄ መዳረስ ነበረበት፡፡ምንምን ሳይካተት ቀረ ለማለት (**ሠንጠረዥ አንድን ለ7ኛና 8ኛ ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመርህ ትምህርቱ የተዘጋጁ የቃላዊ ክሂል(ማዳመጥና መናገር) ይዘቶችን መመልከትይቻላል፡፡**)

**4.3.2.በፈተናዎቹውስጥየተገኙጠንካራጎኖች**

- ፈተናዎቹ የቀረቡበት መንገድ ወይም ቅደም ተከተል ቃላዊ ክሂልን በማስቀደም ንባብን ከዚያም መጻፍን እያሉ የተዘጋጁበት መንገድ ከቀላል ወደ ከባድ በመሆኑ የፈተናን መርህ የተከተለ ነው፡፡
- በፈተናዎቹ (በጥያቄዎቹ) አማራጮች ውስጥ ሀእናለ ወይም ሁሉም መልስ ናቸው
- ካልሆነም መልስ የለም የሚሉትን አማራጮች ባለማካተታቸው ጥሩ ፈተና ነው ያስብላል፡፡
- ከመርህ ትምህርት አንፃር የተወሰኑ ክፍተቶችማለትም የጥያቄዎቹ ውክልና መጠን የመርህ ትምህርትን ሽፋን ከማዳረስ አንፃር ተመጣጣኝ አይሁን እንጂ በሁሉም ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች መርህ ትምህርቱን ለማዳረስ ጥረት ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ እና አስተያየት

### 5.1.ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሲዳማ ክልላዊ መንግስት ከ2013 እስከ 2014ዓ.ም የስምንተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት እና ለዚህ ክፍል የተሰጡ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ያላቸውን የይዘት ተዛምዶ ወይም ተገቢነት መፈተሽ ነው፤ይህን ዋና ዓላማ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ ያሉት ንዑሳን ዓላማዎች በጥናቱ ምላሽ አግኝተዋል፡፡እነርሱም የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች በክልሉ መርሀ- ግብር መሰረት መደበኛ በሆነ ጊዜ የሚቀርቡ ወይም የችሎታ መለኪያ ፈተና የሚባሉ የፈተና አይነቶችን ፈትሿል፤ፈተናው ሲዘጋጅ መርሀ ትምህርትን መሰረት በማድረግ የቋንቋ ትምህርትን ዓላማ ከግብ የሚያደርሱ ይዘቶች እንዳሉት ተገምግሟል፤በሁለቱም ዓመተምህረቶች የተዘጋጁት ፈተናዎቹ ከፈተና ባህሪያት እና መርህዎች አንፃር ማስገኘት ያለባቸውን ግብ ለመድረስ የሚያስችሉ መሆናቸውን የጥያቄዎቹን አቀራረብ ከክሂሎች፣ ከሰዋሰውና ከሥነጽሁፍ አንጻር ተፈትሸዋል፡፡

በምዕራፍ አራት ወይም መረጃዎችን አሰባስቦ ለመተንተን እና ለመበየን በቅድሚያ በምሁራን ጽንሰሀሳብ እና በተዛማጅ ጥናቶች መደገፍ ስላለባቸውበክለሳ ድርሳናት ጥናቱ ተጠናክሯል ወይም ፍንጭ ተገኝቶበታል፡፡

የጥናቱ ዘዴ ከጥናቱ ዓላማ አንፃር ዓይነታዊ እና መጠናዊ የምርምር ዘዴ በሥራ ላይ በማዋልፈተናዎቹ ውስጥ የተዘጋጁትን የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች አራቱ ክሂሎች እና ሁለቱ የዕውቀት ዘርፎች (መናገር፣ማዳመጥ፣መጻፍ እና ማንበብ እንዲሁም ሥነጽሁፍና ሥነልሣን)ከመርሀ ትምህርት ጋር ያላቸውን ተዛምዶ ከፈተና አዘገጃጀት ባህርይ እና መርሆዎች አንጻር ከፈተናዎቹ በሚገኙ መረጃዎች መሠረት በቁጥርና በመቶኛ ተሰልተው በገላጭ ስልት ቀርበዋል፡፡

የጥናቱ ዋና ትኩረት ከ2013 እስከ 2014 ዓ.ም በሲዳማ ክልላዊ መንግስት ለ8ኛ ክፍል የተሰጡ ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ከመርሀ ትምህርት ጋር ያላቸው የይዘት ተዛምዶ መፈተሽ ወይም መገምገም ስለሆነ ከስምንተኛ ክፍል ትምህርት መሸጋገሪያ ወይም ለማጠናቀቂያ በሁለቱም ዓመተ ምህረት የተሰጡ ክልላዊ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች እና የሰባተኛ እና የስምንተኛ ክፍል መርሀ ትምህርቶች ዋና ምንጭ ሲሆኑ የመማሪያ እና ማስተማሪያ መጽሀፍት ረዳት የመረጃ ምንጭ ሆነዋል፡፡

የመረጃ አተናተን ዘዴው በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተገኙትን መረጃዎች ዓይነታዊ እና መጠናዊ የመረጃ አተናተን ስልትንበመጠቀም ግምገማው ተከናውኗል፡፡ ጥናቱ በፈተናዎቹ ውስጥ የተዘጋጁትን የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች አራቱ ክሂሎች እና ሁለቱ የዕውቀት ዘርፎች ከመርሀ ትምህርት ጋር ያላቸውን ተዛምዶ ከፈተና አዘገጃጀት ባህርይ እና መርሆዎች አንጻር ከፈተናዎቹ በሚገኙ መረጃዎች መሠረት በቁጥርና በመቶኛ ተሰልተው በገላጭ ስልት ተተንትነዋል፡፡

የመረጃ ትንተናየጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ እንዲያስችላት ከሰነዶቹ ያገኘችውን መረጃዎች አቅርባለች፡፡የዚህ ጥናት ትኩረት እና ዓላማ በሲዳማ ክልላዊ መንግስት ከ2013 እስከ 2014ዓ.ም የስምንተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርትእና ለዚህ ክፍል የተሰጡ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ያላቸውን የይዘት ተዛምዶ ወይም ተገቢነት መፈተሽ በመሆኑ በዚህ ክፍል ሁለት ነገሮች ታይተዋል፡፡የመጀመሪያው የፈተናውን እና የመርሀ ትምህርቱን ግንኙነት በመቀጠል የፈተናውን ተገቢነት ፡፡በጥናቱ የተዳሰሱት ዐብይ ጉዳዮች(የመረጃ ምንጮች አጭር ቅኝት)የሚከተሉት ናቸው፡-.

የመርሀ ትምህርቶች እና የመማሪያ መጽሀፍት ቅኝት፣ለ7ኛና 8ኛክፍል አማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀ የመርሀ ትምህርት ይዘቶች፣የፈተናዎች ቅኝት፣ለ7ኛና 8ኛ ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመርሀ ትምህርቱ የተዘጋጁ አራቱ ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች ዝርዝር ይዘቶች፣ በሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የመጀመሪያ ደረጃ ማጠናቀቂያ (ለ8ኛ ክፍል) አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ፈተና ውስጥ የአራቱ ክሂሎች እና የዕውቀት ዘርፎች ፈተና ዝርዝር ይዘቶች፣ በመርሀትምህርቶቹ እና በፈተናዎቹ መካከል ያለው ግንኙነት፣ በሁለቱም ፈተናዎች የቀረቡ የፈተና ጥያቄዎች ከፈተና መርሆች አንጻር ያላቸው ጠንካራና ደካማ ጎን እና በመጨረሻም የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ከመርሀ ትምህርቱ አንጻር በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ያላቸው የይዘት ድግግሞሽ መጠን እና ድግግሞሹ የተተገበረበት ክፍለጊዜ መጠን በጥናቱ ሂደት ተፈትሸውየተገኙ ግኝቶችም ጭምር ናቸው፡፡

**በዚህ ጥናት የተስተዋሉ ግኝቶች ባጭሩ ጠቅለል አርገን ስናይ እንደሚከተለው ይሆናሉ፡-**

- ከዚህ በላይ የተጠቀሱት እንዳሉ ሆኖ በሁለቱም ዓ.ም የቀረቡ የፈተና ይዘቶችከመርሀ ትምህርት አንፃር የተወሰኑ ክፍተቶች ማለትም የጥያቄዎቹ ውክልና መጠን የመርሀ ትምህርትን ሽፋን ከማዳረስ አንፃር ተመጣጣኝ አይሁን እንጂ በሁሉም ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች መርሀ ትምህርቱን ለማዳረስ ጥረት ተደርጓል፡፡
- ፈተናዎቹ የቀረቡበት መንገድ ወይም ቅደም ተከተል የተዘጋጁበት መንገድ ከቀላል ወደ

ከባድ በመሆኑ የፈተናን መርህ የተከተለ ነው፡፡

- በፈተናዎቹ (በጥያቄዎቹ) አማራጮች ውስጥ ሀእናለ ወይም ሁሉም መልስ ናቸው ካልሆነም መልስ የለም የሚሉትን አማራጮች ባለማካተታቸው የአንድን ፈተና ተገቢነት ለሚሚላት የተደረገ ጥረት ነው ያስብላል፡፡
- በፈተና ወቅት ተማሪዎችን ለፈተናው የሚመራ መመሪያ ነው፤ተማሪዎቹመመሪያን መሰረት አድርገው የሚሰሩ ሲሆን መመሪያው የተዛባ ወይም ጥያቄውን በትክክል አድሬስ አድርጎ ካልተዘጋጀ እና የሚያሻማ ከሆነ ተማሪዎቹ ለመስራት ይቸገራሉ በመሆኑም ክሂሎችንና የዕውቀት ዘርፎችን በትክክል አድራሻ አድርጎ ከመፈተን አንፃር የመመሪያ ግልፀኝነት ጉድለት ታይቶበታል፡፡
- የ2013 እና 2014 ዓ.ም ፈተና ውስጥ የመርሀ ትምህርት ዝርዝር ይዘቶችበተለይ የቃላዊ ክሂል ፈተና ከመርሀትምህርቱ አንፃር ተደራሽነቱ ውስን ነው በመሆኑም

የመርሀ ትምህርትን ሽፋን ከመጠበቅ አንጻር የጥያቄዎቹ ፍትሀዊነት ወይም ተደራሽነት ጉድለት ተስተውለዋል፡፡

## 5.2.አስተያየት

ይህ ጥናት በዋናነት በሲዳማ ክልል በ2013 ዓ/ም እና በ2014 ዓ/ም በተሰጡት የ8ኛ ክፍል ክልል አቀፍ ፈተናዎች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ እነዚህ ፈተናዎች ደግሞ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች በመሆናቸው የሚዘጋጁት ፈተናዎች የተማሪዎችን ዕውቀትና ችሎታ የሚለኩ መሆን አለባቸው፡፡

ከላይ የቀረበውን የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን የመፍትሄ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

- በፈተናዎቹ ላይ ተገቢውን ውክልና ያላገኙ የቋንቋ ክሂሎች እንደ ማዳመጥና መነገር ያሉ በመርሀ ትምህርቶቹ ውስጥ የተሰጣቸውን ሽፍን ተመጣጣኝ ውክልና እንዲያገኙ ቢደረግ የተሻለ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል በፈተናዎቹ ውስጥ ማግኘት ከሚገባቸው በላይ ከፍተኛ ሽፋን ያገኙ የእውቀት ዘርፎች እንዳሉበት በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በመሆኑም አንድ ይዘት ላይ ብዙ ጥያቄ ከማብዛት ይልቅ ለሁሉም ይዘቶች እንደየሽፋናቸው ውክልና ቢሰጣቸው፡፡
- በፈተና ወቅት ተማሪዎችን ለፈተና የሚመራ መመሪያ ነው፤ተማሪዎችም መመሪያን መሰረት አድርገው የሚሰሩ ሲሆን መመሪያው የተዛባ ወይም ጥያቄውን በትክክል አድራሻ አደርጎ ካልተዘጋጁ እና የሚያሻማ ከሆነ ተማሪዎቹ ለመስራት ይቸገራሉ፡፡

በመሆኑም እነዚህን መሰል ችግሮች ለማረምና ወደፍት እንዳይፈጠሩ ለፈተና አዘጋጆች ሙያዊ ስልጠና ቢሰጥ የተሻለ ይሆናል፡፡

- የ2013 እና የ2014 ዓ/ም ፈተና ውስጥ የመርሀ ትምህርት ዝርዝር ይዘቶች በተለያ የመናገርና የማዳመጥ ክሂል ፈተና ከመርሀ ትምህርቱ አንፃር የጥያቄዎቹ ፍትሀዊነት ወይም ተደራሽነት ጉድለቶች ተስተውለውባቸዋል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ለፈተና አዘጋጆች ልዩ ትኩረትና ስልጠና ቢሰጥ የተሻለ ይሆናል፡፡
- ፈተናዎች ተገቢ የአዘገጃጀት መርሆችን ተከትለው መዘጋጀት አለመዘጋጀታቸውን በተደረገ ምርመራ ጠንካራ ጎኖች ጎልተው ቢታይም አንድንድ የፈተና ጥያቄዎች ችግር እንዳለባቸው ለማየት ተችሏል፡፡ ከነዚህም ችግሮች ውስጥ የጥያቄውን ማዕከላዊ ሀሳብ በግልፅና ነጠላ ሀሳብ ከማዘጋጀት አንፃር የመመሪያ ግፀኝነት ጉድለት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በቋንቋ ፈተና የሚነሱ ችግሮችን ለመቀነስና ለማስወገድ የፈተና አዘጋጅ ባለሙያዎቹ በፈተና ላይ የሚደረጉትን ጥናትና ምርምሮች በማየትና ግምገማ በማድረግ የተሸለውን ወይም ጠንካራ ጎኖችን ወስደው በግብዓትነት ቢጠቀሙ የተሸለ ፈተና ለማዘጋጀት ይጠቅማል የሚል እምነት አሏት፡፡

## ዋቢ ጽሁፎች


ራሄል ወርቁ (2001)ከ1993 — 2000 ዓ.ም ድረስ በቀረቡት የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መልቀቂያ ፈተናዎች የመድብለ ቃላት አፈታተን ፣አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)

ተስፋዬ ሸዋዬ (1982)፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አማርኛን የማስተማሪያ ዓላማዎች ትንታኔ፣ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ (ያልታተመ)

ታረቀኝ ተፈራ(1993)፣ሀገር አቀፍ የ8ኛ ክፍል ፈተና ከ5- 8ኛ ክፍልየአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ጋር ያለው ዝምድና፣አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ።(ያልታተመ)

አበበች ገብሩ (2004)፣ከ1998 እስከ 200 በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች ተዘጋጅተው የቀረቡ አማርኛ ቋንቋክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ጥያቄዎች ግምገማ ፣ለኤም .ኤ ዲግሪማሟያነት የቀረበ ጥናት፣አዲስ አበባዩንቨርሲቲ።(ያልታተመ)

ያለው እንዳወቀ (2009)፣ የምርምር መሰረታዊ መርሆች እና አተገባበር፣ ሦስተኛ እትም፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስአበባ

Alderson.Charles (1995).Language Test Construction and Evaluation.Cambrige Universit Combrige University press.Alderson,Charles(2003).*Assesing Reading*.Combridge፡ Cambri UnvivesrityPress.

Bachmann.(1990).fundamental consideration in language testing .London.Oxford university press.University Press.

Baker, D. (1989). Language Testing. Ariticla Survey and Practical Guide London: Divison of Hodder and Stoughton.

Brown, H. (1994). Principles of language learning and teaching .san Francisco state university prentice .

Carol B,J (1980). Testing communicative performance.an intering study, oxford, pergamon press LTD.

Dubin, F and E, Olishtain (1986). Course design: Developing programs and materials forlanguage learning. Cambridge cug.

Finocchiaro, M. and Brumfit, C. 1986. The Fundamental National ApproachFrom Theory to Practice. Oxford: Oxford University Press

Gronlund, E, N. 1981. Measurement and Evaluation in Teaching.Macmillan Pulishing. Co.INC, New York

Harrison, D. (1983). Language testing hand book. New York: Cambridge university press.

Heaton(1975). Writing English language tests.London, longman.

Heaton,J.B.(1988). *Writing English Language Tests*.Singapore: Longman Limited.

Hughes, A. (1989). Testing for language teachers Cambridge; Cambridge university press.

Hughes, A. (2003) *Testing For Language Teachers.*(3rd ed.) . Cambridge: Cambridge University Press.

Madson, H. (1983).Techniques in testing.Hong Kong; Oxford university press.

Nunan D. (1994).Teaching and Reading Foreign Language.London: Clays Ltd.Richards, J.e. (1990). The language Teaching Matrix. Cambridge university press.

Richards, J.e. and T.5.Rodgers (1996). Aproaches and Methods in Language Teaching: A Description and Analysis. Cambridge :Cambridge University press.

Rivers, W. M. (1968) .*Teaching foreign Language skills.*Chicago: university of Chicago Press.

Tomlinson, B. (2008). Language Acquisition and Language Learning Materials. InTomlinson, B. (ed.) *English Language Learning Materials*.A Critical Review. London/New York, NY: Continuum.

Ur, P. (1996). *A course in Language Teaching*.Cambridge: Cambridge University Press.Ur. P. (1991).Grammer Practice Activites; Aprctical Guide for Teachers.cambridge Cambridge University press.

Weir C,J.(1990). Communicative language testing.Newyork, printice hall.

# አባሪዎች

# አባሪ 1

## ሠንጠረዥ አንድ ለ7ኛና 8ኛ ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመርሀ ትምህርቱ የተዘጋጁ የቃላዊ ክሂል(ማዳመጥና መናገር) ዝርዝር ይዘቶች

| የ7ኛ ክፍል ቃላዊ ክሂሎች(ማዳመጥና መናገር) ዝርዝር ይዘቶች | የ8ኛ ክፍል ቃላዊ ክሂሎች(ማዳመጥና መናገር) ዝርዝር ይዘቶች |
|---|---|
| የፍደላን ስደራ ህግጋትዕውቀትውስብስብ ለሆኑ በርካታ ቃላትመጠቀም፡፡<br>•ቃለመጠይቅ ይጠይቃሉ፤ይመልሳሉ፡፡ገፀባህርያትንና ሁነቶችን መረዳትን በሚያሳይ መልኩ ምልልስን በሀረግና በአገላለጽ እየለዩ ያጠናሉ፡፡ አስተያየቶችን በምክንያትይገልፃሉ፡<br>•የጊዜና የቦታ ተውሳከ ግሶችን እንዲሁም የተለመዱአመልካቾችንና መስተፃምሮችን የሚያመለክቱ ምዕላዶችን ወይም ቃላትን ከንግግር መለየት ይጀምራሉ፤(የመደብ፣የሙያ፣የቁጥርና የፆ ምዕላዶችን ያስተውሏል)፡፡<br>•ጊዜአመልካች ምዕላዶችን ወይም ቃላትንመለየትናመበየንይጀምራሉ(የመደብየሙያ፣የቁጥርና የፆታአመልካቾችን ያስተውሏል)፡፡<br>•እንደመሙያየሚያገለግሉትንስሞች(በጥንታዊውብያኔከ'የመሆንግሶች'ጋርየሚመጡ) መለየትና መበየን ይጀምራሉ፡፡<br>•የተለመዱ ቀላል ዐረፍተነገሮችንና የተለመዱ ድርብ ዐረፍተነገሮችን መዋቅር በንግግር ይለያሉ፡፡•የተለመዱ መጠይቃዊ ዐረፍተነገሮችን ሆን ግስ ጋርመዋቅሮችንና በጣምየተለመዱ ጥገኛ ሀረጎችን በንግግር ይለያሉ፡፡<br>•ከአፈ ታሪክና ከቃላዊ ግጥም አዳዲስ ቃላት ለማወቅየማጣቀሻና የግምትፍንጮችን መጠቀም ይለማመዳሉ፡፡<br>•በንግግር ጊዜ ዕውቀት ለማግኘትና ለማበልፀግ እንዲሁ ምግልፅ ማብራሪያእንደ መሙያ የሚያገለግሉትን ይጠቀማሉ፡፡<br>በቃላት መካከል ያሉትን ግንኙነቶችበሚገባ ይረዳሉ(ለምሳሌ አንድ ቃልከቀደመው ሀረግጋር ያለውን ዝምድ)፡፡<br>•የደራሲውንየቃላትምርጫይተነትናሉ፡፡በምልልስና በድራማአዲስ የገበዩትን የቃላት ዕውቀት ይጠቀማሉ፡፡ | የፍደላን ስደራ ህግጋትዕውቀትውስብስብ ለሆኑ ይተገበራሉ ቃላትመጠቀም፡፡<br>(የፍደላ ህግጋት ምን እንደሆኑ እና እንዴት እነደሚሰሩ ያብራራሉ)፡፡<br>•ቃለመጠይቅ ያካሂዳሉ፤ይመልሳሉ፡፡<br>.ምልልስ በግል አዘጋጅተው ከአገላለጽ ጋር ለክፍል ያቀርባሉ፡፡<br>አስተያየቶችን በምክንያትይገልፃሉ፡፡<br>•የጊዜና የቦታ ተውሳከ ግሶችን እንዲሁም የተለመዱአመልካቾችንና መስተፃምሮችን የሚያመለክቱ ምዕላዶችን ወይም ቃላትን ከንግግር መለየት ይጀምራሉ፤(የመደብ፣የሙያ፣የቁጥርና የስምዕላዶችን ያስተውሏል)፡፡<br>•ጊዜአመልካች ምዕላዶችን ወይም ቃላትንመለየትና መበየን ይጀምራሉ(የመደብየሙያ፣የቁጥርናየፆታ አመልካቾችን ያስተውሏል)፡፡<br>•ጊዜአመልካች ምዕላዶችን ወይም ቃላትንመለየትናመበየን ይጀምራሉ(የመደብየሙያ፣የቁጥርናየፆታአመልካቾችን ያስተውሏል)፡፡የጊዜ እና የቦታ ድግግሞሽየሁኔታ ተውሳካ ግሶችን ያስተውላሉ ሰርተው ያሳያሉ፡፡<br>• ጥገኛ ዓረፍተ ነገሮችን<br>• እንደመሙያ የሚያገለግሉትን ስሞች ከየመሆን ግሶችጋርየሚመጡ ይለያሉ ይወስናሉ፡፡<br>• በንግግር ጊዜ ዕውቀት ለማግኘትና<br>• ለማበልጸግ እንዲሁም ግልጽማብራሪያ<br>• ለመስጠት አዲስ ያወቁትን የቃላ እውቀት ይጠቀማሉ፣በቃላት መካከል ያሉትንግንኙነቶችበሚገባይለያሉ፡፡ |

**ሠንጠረዥ2.በሲዳማብሄራዊክልላዊመንግስትትምህርትቢሮየመጀመሪያደረጃማጠናቀቂያ(ለ8ኛ ክፍል)አማርኛእንደሁለተኛቋንቋየ2013 እና 2014 ዓ.ም ፈተና ውስጥየቃላዊ ክሂል/መናገር ማዳመጥ/ ፈተና ዝርዝር ይዘቶች**

| ሲዳማብሄራዊክልላዊመንግስትትምህርት<br>ቢሮአማርኛእንደሁለተኛቋንቋ 2013 የቃላዊ ክሂል<br>(መናገር እና ማዳመጥ) ፈተና ይዘቶች | ሲዳማብሄራዊክልላዊመንግስትትምህርት<br>ቢሮአማርኛእንደሁለተኛቋንቋ 2014<br>የቃላዊ ክሂል (መናገር እና ማዳመጥ)ፈተና ይዘቶች |
|---|---|
| 1.አንድ መምህር‹‹የጎበዝተማሪ ባህርይ››<br>የሚልጽሁፍለማስደመጥ<br>እየተዘጋጁ፣‹‹የጎበዝ ተማሪ ባህርይ ምንድነው››<br>ብለው ቢጠይቁ ከሚከተለው የትኛውን ሂደት<br>ተግባራዊ አደረጉ?<br>A.ሂደተ ማዳመጥ B.ድህረ ማዳመጥ<br>C.ቅድመማዳመጥ D.ሂደተ ማዳመጥና<br>ድህረ ማዳመጥ<br>2.አንድ መምህር ለተማሪዎቻቸው<br>ሊያነቡላቸው ከፈለጉት የታሪክ<br>ጽሁፍ ውስጥ የታሪኩን ባለቤት ስም<br>ጠርተው፣ስለርሱ የሚያውቁትን<br>እንዲነግሯቸው ቢጠይቁከዚያ በከሚከተለው<br>የትኛውን የማዳመጥ ተግባር እያከናወኑ ነው?<br>Aሂደተ ማዳመጥ B ድህረ ማዳመጥ<br>C.ቅድመማዳመጥ D.ሂደተማዳመጥና ድህረ<br>ማዳመጥ<br>3.አንድ መምህር ‹‹በዚህ ታሪክ ውስጥ ስንት ገጸ<br>ባህሪያት ይገኛሉ?A.ሂደተ ማዳመጥ B ድህረ<br>ማዳመጥ C.ቅድመማዳመጥ D.ሂደተማዳመጥና<br>ማዳመጥ<br>4.በአንድ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች ውይይት<br>የማድረግ ጠቀሜታ ምንድነው?<br>Aየማዳመጥና የመቃወም ችሎታ ለማሳደግ<br>Cጽሑፍ ሲያነቡላቸው እንዲያደምጡ ለማስቻል<br>D.የመናገርክሂልን ለማሳደግ<br>B.የማንበብ ክሂልን ለማሳደግ<br>5.ወላጆች ለልጆቻቸው ስላሉባቸው ችግሮች<br>ከትምህርት ቤቱ የስራ ሀላፊዎች<br>አካላት ጋር ተነጋገሩ፣ከዚያ በኋላ ተማሪዎቹ<br>የባህርይ ለውጥ አሳዩ?A.የክርክርን ጠቀሜት<br>B.የጭውውት ጠቀሜታ C.የውይይት ጠቀሜታ<br>D.የዘገባን ጠቀሜታ<br>6.ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የውይይት<br>አዘገጃጀት መመሪያ ሊሆን የሚችለው?<br>A.ችግርን ለመፍታት በጋራ ሀሳብ ላይ<br>መስማማት ማቀድ Bተቃራኒ ሀሳቦችን | 1. አንድ በአማርኛ ተረት የሚናገር ሰው ተረቱን<br>ካጠናቀቀ በኋላ ምን በማለትይጨርሳል?A. ተረት<br>ተረት፣ የላም በረት። B. አገር ስጠኝ።C. ተረቴን<br>መልሱ፣ አፌን በዳቦ አብሱ። D. እንቆቅልህ።<br>2. ከንግግር አዳምጦ ማስታወሻ ለመውሰድ ተገቢ<br>ያልሆነው ነጥብ የቱ ነው?A. ታሪኩን በራስ ቋንቋ<br>መተረክ B. ለመቼቱ ትኩረት መስጠትC. የታሪኩን<br>ጭብጥ መረዳት D. የግጭት አፈታቱ ላይአለማተኮር<br>3. ቀጥሎ ከቀረቡት ውስጥ መረጃን የመቀበያ ክሂሎች<br>የትኞቹ ናቸው?<br>A.ማዳመጥና ማንበብ B. መናገርና መጻፍ<br>C. መጻፍና ማዳመጥD. ማንበብና መናገር<br>4.በክርክር ዝግጅት ወቅት በቅድሚያ ትኩረት<br>የሚሠጠው የቱ ነው?A.ርእሱንለአድማጭ<br>ማስተዋወቅ B.የማጠቃልያ ሀሳብማቅረብC.ክርክሩን<br>በወጉ መቋጨት D. የመከራከሪያ ርእስ<br>መምረጥ<br>5.አንድ የሚደመጥ ምንባብ ከመቅረቡ በፊት<br>ለቀረቡ ጥያቄዎችግምት የሚሰጥበት ደረጃ የትኛው<br>ነው?A. ድህረ ማዳመጥ B.ቅድመ ማዳመጥ<br>C.የማዳመጥጊዜ D.ቅድመ ማንበብ<br>6.በክርክር አዘገጃጀት ወቅት በመጨረሻ የሚከናወነው<br>የትኛው ነው?A. ለክርክሩ<br>አጋዥ መረጃዎችን ማሰባሰብ<br>B.የማጠቃለያ ሐሳብ ማዘጋጀትC.መረጃውን በቅደም<br>ተከተል ማደራጀትD.ርእስመፈለግና መምረጥ<br>7. የክርክር አዘገጃጀት መመሪያ ትክክለኛው ቅደም<br>ተከተልየትኛውነው? 1.መግቢያ ሐሳብ ማዘጋጀት3.<br>ርእስ መምረጥ2.ቅደም ተከተልማስያዝ4.መረጃዎችን<br>መሰብሰብ<br>A. 3፣ 4፣ 2፣1 C. 4፣ 3፣ 2፣1<br>B. 3፣ 1፣ 2፣ 4 D. 2፣ 1፣ 3፣4<br>8.ክርክርምንድነው?A. በሰዎች መካከል<br>የሚደረግ የሐሳብ ልውውጥ ነው።B.ለችግሮች |

ይዞ መቅረብ C.የራስን ሀሳብ አግባብቶ ለማሳመን በቂ ማስረጃ ማዘጋጀት D.ተወያዮችን ባልሆነ ሁለት ቡድኖች መክፈል.

7.ከሚከተሉት ውስጥ የውይይት መመሪያ የሆነው፡-A.በቅደም ተከተል ማደራጀት B.ከጽሁፍ ፍሬማውጣት C.የክርክርን ጠቃሚነት ማስረዳት D.በርእሱ ዙሪያ ግንዛቤ ማግኘት

8.ውይይት ምንድነው?A.የንግግር ችሎታ B.የሀሳብ ልውውጥ C.ሀሳብ ድምዳሜ D.የንግግር አይነት

9.ከሚከተሉት አንዱ የውይይት አቀራረብ መመሪያ የሚያመለክተው፡-A.ተራን ጠብቆ መናገር፣B.ርዕስ ጉዳዩን መረዳት C.ስለርእሱ ሀሳብ ማግኘት D.ተራን ሳይጠብቁ መናገር

10በመማሪያ ክፍል ውስጥ በመምህር እገዛ ክርክር ማድረግ ለምን ይጠቅማል? A.ምክንያታዊ በሆነ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ሀሳብ የማቅረብ ችሎታ ለማሳደግ B.ከሌሎች ሰዎች ጋር ሀገራዊ ሀሳብ ለመለዋወጥC.ለክርክር የተሰጠውን ጊዜ በአግባቡ ለመጠቀም D.ለመምህር ሀሳብን ለማቅረብ

11.የክርክር አዘገጃጀት መመሪያ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው? A.ሀሳብ በቅደም ተከተል ላይሆን ይችላል B.ሃሳብ ቅደምተከተል ባይኖረው ይመከራል C.ሃሳብን በቅደም ተከተል ማቅረብ D.ሃሳብን ለተቃራኒ ወገን ቀድሞ አለማካፈል

12.ከሚከተሉት መካከል ስለ ክርክር አዘገጃጀት እውነት የሆነውየትኛው ነው?A.የራስ መከራከሪያ ሀሳብን ለማንም አለመናገርB.በክርክር ወቅት ሀሳብን ለማሳመን የሚረዱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ D.የሌሎችን ሀሳብ ለመጫን መሞከር D.ረዘም ያለ ጊዜ ወስዶመናገር

የመፍትሔ ሐሳብ መጠቆሚያ ነው፡፡C.በሁለት ቡድኖች መካከል የሚደረግ ሙግት ነው፡፡D.የውሳኔ ሐሳብ ማንሸራሸሪያ

9.ከሚከተሉት መካከል ከክርክር የሚገኘው ጥቅም የትኛውነው?A.አሸናፊ የሆነውን ለመሸለም B.ግንዛቤ ጨብጦ ሌሎችን የማሳመን አቅም ለመፍጠር ነ C. ታዋቂነትን በማትረፍ ዝናን ለማጎናጸፍነው፡፡D.በሰው የበላይነትን ለማትረፍ ነው፡፡

10. ትምህርቱ በሬድዮ ተላልፎ ካበቃ በኋላ መምህሩ በቃልየ ጥያቄዎችን ምላሽ ቢቀበሉ የትኛው ተግባር ተከናውኗል?A. ድህረ ማዳመጥ C. ቅድመና ድህረ ማዳመጥB. ቅድመ ማዳመጥ D. ሂደታዊ ማዳመጥ

11.መምህሩ የሚደመጥ ነገር በሬዲዮ እያቀረቡ በመካከል ቆይታ በማድረግየቃል ጥያቄ ቢጠይቁ የትኛውን ተግባር እያከናወኑ ነው?A. ቅድመ ማዳመጥ B. ቅድመና ድህረ ማዳመጥC. ድህረ ማዳመጥ D.ሂደታዊ ማዳመጥ

## ሠንጠረዥ ሶስት ለ7ኛና 8ኛ ክፍል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመርሀ ትምህርቱ የተዘጋጁ የማንበብ ክሂል ዝርዝር ይዘቶች

| | |
|---|---|
| በመርሀ ትምህርቱ የተዘጋጁየ7ኛ ክፍል<br>የማናበብ ክሂል ዝርዝር ይዘቶች<br>•ቃላትን ለማንበብ እስርና ነፃ ምዕላዶችን ማጣመርና መነጣጠል ይችላሉ፡፡የታሰበውን ውጤ<br>ት<br>ሊያመጣ የሚችል ስልት ለቋንቋውበመጠቀምው ስብ<br>ስብ መዋቅር ያላቸውን ቃላትያነብባሉ<br>፤አዳዲስ ቃላትን ለማንበብ የምዕላድ ትርጉም ዕውቀት (ቃል መስራች እና/ወይምየእርባታምዕላዶችን)<br>ይጠቀማ፤•ገፀባህርያትንና ሁነቶችን መረዳትን በሚያሳይመልኩ ምልልስንበሀረግናበአገላለፅ ለይተውይፅፋሉ፡፡<br>•ለማግባባት ንግግሮችን ያነባሉ፤ግጥምአብራርተው ያነባሉ፡፡<br>•ለክፍል ደረጃቸው የተዘጋጀውን ፅሁፍ95%በትክክል ያነባሉ፡፡<br>•ለክፍል ደረጃቸው የተዘጋጀውን ገላጭ ፅሁፍ ያነባሉ<br>፡፡<br>•ለክፍል ደረጃቸው የተዘጋጀውን የፈጠራ ፅሁፍ ያነባሉ፡፡<br>•ንግግር ወይም ፅሁፍና ግጥም በትክክል ማንበብን ለመለማመድያነባሉ፡፡<br>•ጨዉናለደረጃውየሚመጥንናከፍተኛየማንበብ ፍጥነትይኖራቸዋል፡፡<br>•የማንበብንፍጥነትየመሻሻልሂደትይቆጣጠራሉ፡፡<br>•ቃለመጠይቅይጠይቃሉ፤ይመልሳሉ፡፡ገፀባህርያትንና ሁነቶችንመረዳትንበሚያሳይመልኩምልልስንበሀረግና በአገላለጽ እየለዩያጠናሉ፡፡አስተያየቶችን በምክንያትይገልፃሉ፡፡<br>•የተለመዱአዎንታዊ፣አሉታዊናመጠይቃዊ ምዕላዶችንወይምቃላትንእና በንግግርበጣም የተለመዱግስመስራቾችንመበየንናመለየት ይጀምራሉ(መደብ፣ሙያ፣ቁጥርናፆታአመልካች ቅጥያዎችንያስተውሏል)፡፡<br>•የጊዜናየቦታተውሳከግሶችንእንዲሁም የተለመዱአመልካቾችንናመስተፃምሮችን የሚያመለክቱምዕላዶችንወይምቃላትንከፀሁፍ ውስጥመለየትይጀምራሉ፤(የመደብ፣የሙያ፣የቁጥርና የፆታምዕላዶችንያስተውሏል)፡፡ጊዜአመልካች ምዕላዶችንወይምቃላትንመለየትናመበየን ይጀምራሉ(የመደብ፣የሙያ፣የቁጥርና የፆታአመልካቾችንያስተውሏል)፡፡<br>እንደመሙያየሚያገለግሉትንስሞች | በመርሀ ትምህርቱ የተዘጋጁየ8ኛ ክፍል የማንበብ ክሂል ዝርዝር ይዘቶች<br>•ቃላትን ለማንበብእስርና ነፃ ምዕላዶችን ማጣመርናመነጣጠል ይችላሉ፡፡<br>•የታሰበውን ውጤት ሊያመጣ የሚችል ለቋንቋውበመጠቀምው ስብስብ መዋቅር ያላቸውን ቃላትያነብባሉ፡፡<br>•አዳዲስ ቃላትን ለማንበብ የምዕላድ ትርጉም ዕውቀት (ቃል መስራች እና/ወይምየእርባታምዕላዶ ችን)ይጠቀማሉ፡፡<br>•ቃላን ለማንበብ የምዕላዶችን ውስብስብ ዐውዳዊ ፍቺ ይጠቀማሉ፡፡<br>•ለክፍል ደረጃቸው የተዘጋጀውን ፅሁፍ95% በትክክል ያነባሉ፡፡<br>•ለክፍል ደረጃቸው የተዘጋጀውን ገላጭ ፅሁፍ ያነባሉ፡፡<br>•ለክፍል ደረጃቸው የተዘጋጀውን የፈጠራ ፅሁፍ ያነባሉ፡፡<br>•ንግግር ወይም ፅሁፍና ግጥም በትክክል ማንበብን ለመለማመድያነባሉ፡፡<br>•ለክፍል ደረጃቸው የተዘጋጀውን ገላጭ ፅሁፍ ያነባሉ፡፡<br>•ግጥም አብራርተው ያነባሉ፡<br>•ለክፍል ደረጃቸው የተዘጋጀውን የፈጠራ ፅሁፍ ያነባሉ፡፡<br>•ንግግር ወይም ፅሁፍና ግጥም በትክክል ማንበብን በመለማመድያነባሉ፡፡<br>•በጣም የተለመዱአዎንታዊ፣አሉታዊና መጠይቃዊ ምዕላዶችንወይምቃላትን እና በንግግር በጣምየተለመዱግስመስራቾችን በጽሁፍ ውስጥ ይለያሉ፡፡(መደብ፣ሙያ፣ቁጥርና ፆታአመልካች ቅጥያዎችንያስተውሏል)፡፡<br>•ጊዜ አመልካች ምዕላዶችንወይምቃላትን በፀሁፍ ውስጥ ይለያሉ፡፡ (የመደብ፣የሙያ፣የቁጥርናየፆታምዕላዶችንያስተ ውሏል)፡፡<br>•የሚመጡ)መለየትናመበየንይጀምራሉ፡፡<br>•ጥገኛሀረጎችን በፅሁፍ ውስጥ ይለያሉ፡፡<br>•ቀስበቀስ ውስብስብ ዐረፍተነገሮችን ድርብ መዋቅሮችንና መጠይቃዊ አረፍተነገሮችን በጽሁፍ<br>ውስጥ ይለያሉ፡፡<br>•አፈ-ታሪክአንብበውምላሽይሰጣሉ፡፡<br>•የፈሊጦችን፣የተለዋጭናየተነፃፃሪዘይቤዎችን |

| | |
|---|---|
| (በጥንታዊውብያኔከ‘የመሆንግሶች’ ጋርየሚመጡ)መለየትናመበየንይጀምራሉ፡፡ የተለመዱቀላልዐረፍተነገሮችንና የተለመዱድርብዐረፍተነገሮችንመዋቅርበፅሁፍውስ ጥይለያሉ፡፡የተለመዱ መጠይቃዊ ዐረፍተነገሮችንመዋቅሮችንናበጣም የተለመዱጥገኛሀረጎችንበፅሁፍ ውስጥ ይለያሉ፡፡<br>•የቃላትንትርጉምበደረጃውከተሰጠውፅሁፍ አውድይረዳሉ፡፡በጽሁፍውስጥፍንጮችን በመጠቀምቃላትንያውቃሉ፤ለማመሳከርና አዳዲስቃላትንለመማርዋቢዎችንይጠቀማሉ (ለምሳሌ፣መዝገበቃላት፣ሰዎች፣መጣጥፍ)፡፡አዳዲስ ቃላትንለማወቅየቃልንስሜቶችአጠቃላይ/ዝርዝር/ ሙሉ/ክፍልይጠቀማሉ፡፡<br>•አዳዲስቃላትንበግልንባብለማወቅየፅሁፉን ፍንጮችይጠቀማሉ፡፡የዲስኩርምልክቶችንበሚገባበ መገንዘብ(ቃላትንወይምሀረጋትንበማዛመድ) አዳዲስቃላትንለመረዳትእንደፍንጮችይጠቀሙባቸ ዋል፡፡ለማመሳከርና አዳዲስቃላትንለመማርዋቢዎችንይጠቀማሉ (ለምሳሌ፣መዝገበቃላት፣ሰዎች፣መጣጥፍ)፡፡ ለደረጃውበቀረበታሪክውስጥያሉትንቃላትይገነዘባሉ፡፡<br>•2.5 ገፅያለውንፅሁፍአንብበውያሳጥራሉ፡፡<br>2.5<br>ገፅያለውንፅሁፍአንብበውይገመግማሉ፡፡ለከፍሉደረጃ ለቀረበውፅሁፍከቀደመዕውቀትና ልምድእንዲሁምከሌላፅሁፍያዛምዳሉ፡፡ለፅሁፉየሚስ ማማየመረዳት ስልትናየንባብዘዴ መርጠውበስራላይማዋልይችላሉ፡፡<br>•ለከፍሉደረጃበቻርት፣በሰንጠረዥ፣በግራፍ፣ወዘተ.የ ተሰጠንመረጃተረጉማሉ፣ይገልፃሉ፡፡ስለርዕሰጉዳዩለ መረዳትከቀላልሰንጠረዥ፣ካርታ፣ቻርት፣መረጃ፣ይ ጠቀማሉ፡፡• በቻርት፣በሰንጠረዥ፣በግራፍ፣ወዘተ. የተሰጠንመረጃይገልፃሉ፡፡ፅሁፍለመረዳትናይዘት ለመገመትአርዕስት፣የግርጌመግለጫዎችና (ካፕሽን)ሰንጠረዥያነባሉ፡፡በክፍልደረጃውየተሰጠው ንፅሁፍለመረዳትየፅሁፉንመዋቅር ይጠቀማሉ፡፡የክፍልደረጃውየቀረቡትንሁለት የተለያዩሀሳቦችያነፃፅራሉ፡፡ምዕላዶችን፣ቃላትንናሀረ ጎችንይጠቀማሉ፡፡<br>•ለክፍልደረጃውየተዘጋጀንአጭር ልቦለድ ባህርያትይለያሉ፡፡ለክፍልደረጃውየተዘጋጀንየሴራአላ ባውያንይረዳሉ፤መጀመሪያ፣መሀከል፣መጨረሻ፡፡ ለክፍልደረጃውይመዝናሉ፡፡ድምፅበማሰማት ከተነበበውፅሁፍዳራዊዕውቀትመረጃንየሚሹ ማመዛዘንንየሚጠይቁጥያቄዎችንይመልሳሉ፡፡<br>• ለደረጃውየተዘጋጀንሁለትገፅ ገላጭፅሁፍ ያነብባሉ፡፡ | ትርጉምተረድተውያብራራሉ፡፡<br>•የዘይቤያዊቋንቋአጠቃቀሞችንማለትም ምናባዊና<br>•ስሜትገላጭቃላትንይረዳሉ፡፡<br>•የግጥምዓይነቶችንይለያሉ፡፡<br>•የመጽሄት መጣጥፎችንና የአንድንነገር<br>•አሰራርየሚገልፁፅሁፎችን አንብበው ሀሳብ ይሰጣሉ፡፡ |

| | |
|---|---|
| •ለደረጃውየተዘጋጁሁለትዕሁፎችንያነፃፅራሉ (ምንባቦቹ የተለያዩሲሆኑየክፍልደረጃው አንድ ነው)፡፡ምክንያትና ውጤት የሚገልፅ ለክፍልደረጃው የተዘጋጀን ፅሁፍ ያነብባሉ፡፡ •አፈታሪክአንብበውምላሽይሰጣሉ፡፡የፈሊጦችን፣የተ ለዋጭናየተነፃፃሪዘይቤዎችንትርጉምተረድተውያብ ራራሉ፡፡የዘይቤያዊቋንቋአጠቃቀሞችንማለትምምናባ ዊናስሜትገላጭቃላትንይረዳሉ፡፡የግጥምዓይነቶችን ይለያሉ፡፡የአንድንነገርአሰራርየሚገልፁፅሁፎችን አንብበውይሰራሉ፡፡ | |

**ሠንጠረዥ4 በሲዳማብሄራዊክልላዊመንግስትትምህርትቢሮየመጀመሪያደረጃማጠናቀቂያ(ለ8ኛ ክፍል)አማርኛእንደሁለተኛቋንቋፈተና ውስጥ የማንበብ ክሂል ፈተና ዝርዝር ይዘቶች**

| ሲዳማብሄራዊክልላዊመንግስትትምህርትቢሮ አማርኛእንደሁለተኛቋንቋ 2013 የማንበብ ክሂል ፈተና ይዘቶች | ሲዳማብሄራዊክልላዊመንግስትትምህርትቢሮ አማርኛእንደሁለተኛቋንቋ 2014 የማንበብ ክሂል ፈተና ይዘቶች |
|---|---|
| 13.በዚህ ምንባብ ውስጥ‹‹ከጉብኝታቸው በአንደኛው ጊዜ››የሚለው ሀረግ ምንን ያሳያል?<br>A.ንጉሱ መጎብኘት ማቆማቸውን<br>Bጉብኝት ዋና ስራቸው መሆኑን<br>C.ከዚህ በፊት ይጎበኙ እንደነነበር<br>D.ግንቦት 20 ቀን1951 ዓ.ም.መሄዳቸውን<br>14.የዚህ ምንባብ ዝርዝር ሀሳቦች ሊሆኑ የሚችሉት፡-<br>A.የተራራው ገጽታ፣የተራራው ስያሜ<br>B.ሆጎባ ቀበሌ፣ጥልቴ ቀበሌ<br>C.የሃዋሳ ውበት፣ንጉስ ሀለስላሴ<br>D.የደን መብዛት፣የእስራል ታቦር<br>15.‹‹ተራራው አሁን በሚታየው ገጽታው ሳርና ዛፍ <u>ከመልበሱ</u> በፊት...››በሚለው ውስጥ የ‹‹መልበስ ››እማሬያዊ ፍቺ፡-<br>A.ሰዎች ሳርና ዛፍ ተከሉበት<br>B.ገላጣው ቦታ በሳርና በዛፍ ተሸፈነ ማለት ነው<br>Cሳርናዛፍ የለውም<br>D.የእሳተጎሞራ ፍሳሽ ሸፈነው፡፡<br>16.በዚህ ምንባብ ውስጥ አንደኛውንና ሁለተኛውን አንቀጽ የያዘውየትኛው ነው?<br>A.ወደዚያ Bአሁን C.ከዚህ የተነሳ D.ይህ<br>17.የሚከተለው አጭር ጽሁፍ አንብባችሁ ዋናውን ሀሳብ ለዩ ‹‹አጭርጽሁፍ አለ...››A.ወጣት | 34.በአንቀጽአንድ፣‹‹በባልደረባዎችእጅ›› የሚለው በምንባቡመሰረትምንትርጉም አለው?A. ዘመዶች B. ወላጆችC. አሳዳጊዎች D. አጎቶች<br>35. በምንባቡ መሰረት ዲሞስቴን ወደ ንግግር ጥበብ የገባበት ዋነኛ ምክንያትምንድነው?<br>A. የንግግር ጥበብ አዋቂ ለመሆን ስለፈለገ ነው፡፡<br>B. ምላሱ ኮልታፋና ድምጹ ደካማ ስለሆነበት ነው፡፡<br>C. ያባቱን ሀብት ተከራክሮ ለማስመለስ ሲል ነው ፡፡<br>D. አባቱ በህጻንነቱ ስለሞተበት ነው፡፡<br>36. ዲሞስቴንከሰው ተለይቶ በዋሻ በቆየባቸው ያከናወነው ተግባርምንድነው?<br>A. አእምሮውን በእውቀት መገንባት B. ዘመዶቹን C.መፈለግB. ተማሪዎችንበእውቀትመኮትኮት<br>D. ንግግሮችን ማዳመጥ<br>37. በአራተኛው አንቀጽ፣‹‹አንደበቱን ገራው›› የሚለው በምንባቡ መሰረት ምንፍቺ አለው?A. ዘጋው B. ያዘው C. አሳመረው D. አሰለጠነው<br>38. ዲሞስቴን ግማሽ የራስ ቅሉን ጸጉር የተላጨው ለምንድነው?A. ስለተናደደ ነውB.አዲስ ባህልን ለማስተ ማር ነውC. የተነሳበትን አላማ ለማሳካት ነው<br>D.አእምሮው ትክክል ስላልሆነ ነው፡፡<br>39. ዲሞስቴን በዋሻ ውስጥ የቆየበት አመት ምን ያህል ነው?A. 8 B.6C.7 D. 5<br>40. አራተኛውንና አምስተኛውን አንቀጽ ያያያዘው ሀረግ የ |

በዘመኑ ብዙ
ታላላቅ ተግባራትን ያከናውናል B.የተስፋ ጭላንጭል ይታየዋል C.አንድ ሰው በዕድሜው ላይሳኩ የሚችሉ ብዙ ተስፋዎች ይኖሩታል D.ሰው በወጣትነቱታላላቅ ተግባራትን የማከናወንችሎታ ይኖረዋል፤‹‹አጭር አንቀጽ ጽሁፍ አለ…››
18.በዚህ አንቀጽ ውስጥ የሚገኙ አረፍተነገርን ከአረፍተ ነገር ጋር ያጣመሩ አያያገሮች የትኞቹ ናቸው ?A.ናአልፎ ተርፎ ይሁን እንጂ
B. አልፎ ተርፎ፣ይሁን እንጂ ፣በመሆኑም
Cአልፎ ተርፎ ና፣ በመሆኑም
D ይሁን እንጂ አልነበረውም፣በመሆኑም
‹‹ሠንጠረዥ ከማህደረ ደቡብ መጽሄት ቅጽ1አለ…››
2.ይህ ሰንጠረዥ ማሳየት የፈለገው ዋና ጉዳይ ምንድን ነው A.የከተሞች የቤት ብዛትና የግንባታ እቅድ B.የከተሞች የኢኮኖሚ እድገት ንጽጽር C.የከተሞችን ስም ማስተዋወቅ D.የከተሞች እድገት በዓመተምህረት
19.በአንደኛው ዐረፍተነገር ውስጥ የሚገኘው አያያዥ ---ነው፡፡A.በመሆኑም B.አልፎ አልፎ C.ይሁን እንጂD.ና‹‹ሠንጠረዥ አለ››
20.ይህ ሠንጠረዥ ማሳየት የፈለገው ዋና ጉዳይ ምንድነው?A.የከተሞች የቤት ብዛትና የግንባታ እቅድ B.የከተሞች የኢኮኖሚ እድገትን ጽጽር C.የከተሞችን ስም ማስተዋወቅ D.የከተሞች እድገት በዓመተምህረት
21.በሁለት ዓመታት የግንባታ እቅድ ከሁሉም የበለጠው ከተማ ---ነው፡፡A.ሃዋሳ B.ይርጋለም C.ዲላ D.ወላይታ ሶዶ
